# መላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ - መኢሶን -

# ALL ETHIOPIA SOCIALIST MOVEMENT (MEˊSONE)

## ቃለ መጠይቅ ከዶ/ር ነገደ ጎበዜ ጋር

### <u>ያለፈውና መጪው ትግል</u>

፩ኛ. የወቅቱ የፖለቲካ ሂደት

፪ኛ. ቀይ ሽብር

፫ኛ. መኢሶን፤ ሶቭየቶችና ኢትዮጵያ በ 1969

፬ኛ. መኢሶን ተሸንፏል ? ከኢሕአፓ በምን ይለያል ?

ለ አንባቢዎች፡- ይህ ቃለ መጠይቅ ቀደም ሲል በጦቢያ መጽሄት በቅጽ 2 ከቁጥር 11 እስከ 12 1986፤ በቅጽ 3 ከቁጥር 1 እስከ 3 1986 በተከታታይ የወጣ ሲሆን፤ ብዙ በውጭ የሚገኙ አምስቱንም ቁጥሮች ተሟልተው ያላገኙ አንባቢዎች ድርጅታችንን በየጊዜው ከመጠየቃቸውም በላይ፤ በበኩላችንም ይህ የቃለ መጠይቅ ጽሑፍ ለአንዳንድ ጉዳዮች የውይይት መነሻ የሚሆኑ ነጥቦችን ያስጨብጣል ብለን ስለገመትን፤ ጽሁፉን አሰባስበን በዚህ መልክ አቅርበነዋል።

መልካም ንባብ

1987

# ያለፈውና መጪው ትግል

ዶክተር ነገደ ጎበዜ ደባላቁ። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ሕይወት በተለይም በግራ ኃይሎች እንቅስቃሴና በ17ዓመቱ የአብዮት ዘመን ስማቸው ከማይጠቀሱ ሰዎች አንዱ ናቸው። ከመኢሶን አመራር አባሎች አንዱ ሲሆኑ፣ የፓርቲው አርቅና ሰላም ጉባኤ ሲተመሠረት ናቸው። ባለፈው ሰሞን የወቅቱን የአገራችንን የፖለቲካ ሂደትና ያለፈውንም ትግል በተመለከተ ለተደረገላቸው ቃለመጠይቅ ምላሽ ሰጥተው ነበር። ለወቅቱ የፖለቲካ ሂደት ለነመፍትሔው ለማየት፣ ያለፈውን ለመቃኘት ጠቃሚ ነው። ወደውይይቱ እንግባ።



## የወቅቱ የፖለቲካ ሂደት

**ጥያቄ፣** የፖለቲካ እንቅስቃሴ የጀመሩት መቼ ነው?

**መልስ፣** እንደተወለድ ቀን ጀምሮ እለት በዚህ ሰዓት የፖለቲካ ትግል ጀመርኩ ማለት አይቻልም። በጃንሆይ መንግሥት ሥር የነበረው ግፍ በተለይ ደግሞ የመሬት ስሪት ጉዳይ አስቀይሞኝ በሆዶ የሸፈትሁበትን ጊዜ ዛሬ አላስታውስም። በጣም ረዥም ጊዜ ሳይሆነው አይቀርም።

ለመጀመሪያ ጊዜ ግን በፖለቲካ ጉዳይ ሰልፍ የወጣሁት አይረሳኝም። በእነጀኔራል መንግሥቱ ነዋይ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ነበር፣ የዛሬ ሰላሳ ሦስት ዓመት። ያን ጊዜ ገና የ17 ዓመት ወጣት ሆኜ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ይባል የነበረው የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ነበርኩ። ከዚያች ቀን ጀምሮ ሌት ተቀን ታግያለሁ ወይም በፖለቲካው ዓለም ውስጥ ስትራመስ ኖሬያለሁ ማለት አይደለም። ከዚህ ጊዜ አንስቶ ፊውዳሊዝምን ለመዋጋት ከተነሳው የያኔው ትውልድ ጋር ቀስ በቀስ አብሬ ወደፖለቲካው ዓለም ውስጥ ገብቻለሁ። የሆነ ሆኖ በጣም ረዥም ጊዜ ነው።

እንዳንዶ ለራሴም ይገርመኛል። ያኔ በፖለቲካው ዓለም ውስጥ ዛሬ ካሉት ዜጎች ከመንግሥት በኩል ይሁን ከተቃዋሚው አብዛኞቹ ገና ልጆች ነበሩ። ጥሩ ቁምጣም የታጠቁ አይመስለኝም።

**ጥያቄ፣** በዚህን ጊዜ ሁሉ አንድ አቋም ይዘው ታግለዋል ወይስ. . .?

**መልስ፣** በእውነቱ ከዳር እስከዳር አንድ አቋም ማለት ያስቸግራል። አንድ ዓላማ ግን አለኝ። «ኢትዮጵያ» የሚለው ሃሳብና ከዚያ ተያይዞ የሚመጣው የሀገር ፍቅር፣ ከዚህም የሚወለደው ይቺ አገር የበለጸገች ሀገር እንድትሆን፣ኩሩ አገር እንድትሆን፣ የተከበረች አገር እንድትሆን ሌት ተቀን መመኘት። ከኢትዮጵያ ውጭ ስኖር እንግዲህ ወደ ሰላሳ ዓመት ሊሆነኝ ነው። ግን እንደኔ ውጭ ብዙ የቆዩ ዜጎች የማያውቁት ስሜት አለ። የሀገር ፍቅር ስሜት እንደሚገለሰብ ፍቅር፣ ፈረንሳዮች እንደሚሉት «ከዓይን የራቀ ከልብ ይርቃል» አይመስለኝም። እንዲያውም ተቃራኒው ይመስለኛል።

ሀገር ፍቅር ግን ብቻውን ወደፖለቲካ ትግል አያስገባም። አገሬ ትበልጽግ፣ አገሬ ኩሩ ትሁን፣ የተከበረች ትሁን የሚል ዜጋ ሁሉ ከብሩስ፣ ብልጽግናውስ እንዴት ነው? ብሎ ራሱን እስካልጠየቀ ድረስ ከሰው ሳይደርስ በሰላም በሆዱ አገሩን እየወደደ ሊኖር ይችላል። ትግልና ችግር የሚመጣው ለዚህ አገር ፍቅር ተጨባጭ ይዘትና ትርጉም ለመስጠትና ለዚህም እውንነት መታገል ሲጀመር ነው። ያን ጊዜ በሀገር ፍቅራቸው የማይተናነሱ ዜጎች ወይም ቡድኖች ለዚህ ዓላማቸው የተለያየ ይዘት ለሰጡና ሊፋጠጡ፣ ሊታገሉ ይችላሉ።

እኔ ለሀገር ፍቅር የምሰጠው ትርጉምና ይዘት የህዝብ ፍቅር ነው። የሕዝብ ፍቅሬ ደግሞ ወገናዊ ነው። ለሕዝብ እድገት፣ ለሕዝብ ብልጽግና፣ ለማኅበራዊ ፍትህና ለእኩልነት መታገል ነው ለኔ ሀገር ፍቅር ማለት። በዚህ በኩል ምንም ለውጥ አላደረግሁም። ይህ እንዴት ከሥራ ላይ ይውላል በሚለው ጥያቄ ግን ብዙ ለውጦች አድርጌያለሁ። የአቋም ለውጥ ሊባል ይቻላል።

እኔ ብቻ ሳልሆን አንድ ትውልድ እንዳለ ለኢትዮጵያ ችግሮች መፍትሔ የሶሻሊስት አብዮት ብቻ ነው ብሎ ከልቡ አምኖበት ታግሏል፣ ተሰውቷል። ለተራበው፣ ለተጨቆነው ፍትህ ለተነሳው ሕዝብ ማለትም ለገበሬው፣ ለወዛደሩ ወገናዊነቱን እየገለጸ ለዚህ አብዮት መሳካት ያለ የሌለ ኃይሉ፣ ሕይወቱን ጭምር የከሰከሰ ትውልድ ነው። በወዝ አደሩ የበላይነት በአርሶ አደሩ ተባባሪነት. . . እያልን ታግለናል። ዛሬ ደግሞ የሕግ የበላይነት፣ የብዙ ፓርቲዎች ዲሞክራሲ፣ እንላለን። በኔ በኩል ይህ የአቋም ለውጥ «የሶሻሊስቱ አብዮት ካልተሳካ እስኪ ጽድቁ ይቅርና በወንድ ይኩንነን፣ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓትን እንሞክር» ከሚል አስተሳሰብ የፈለቀ ለውጥ አይደለም። ወይም ደግሞ እስኪ ለጊዜው፣ ለታክቲክ ዲሞክራሲ እንበልና በዚህ ተጠቅመን ሶሻሊስት ሥርዓት እንገንባ ከሚል ስትራቴጂ ተነስቼም አይደለም።

ዓለም ውስብስብ ነች:: ለአንድ ህብረተሰብ ነጻነት ብለው የሚነሱ ኃይሉች በዚህ በእኩልነት ስም ነጻነትን ሲያወድሙ፣ የኢኮኖሚ እድገት እየተባለ ማኅበራዊ ፍትህ ደብዛው ሲጠፋ፣ በዚህ ተመርተው ሕዝብ መርተው ሥልጣን የሚይዙ ኃይሉች ደግሞ ማኅበራዊ ፍትህ እናመጣለን ብለው፣ እኩልነት እናሰፍናለን ብለው ተነስተው በተግባር ግን እድገት ሲገታና ሁሉም በእኩልነት ሲቆረቆዝ አይተናል:: ነጻነት፣ እኩልነት፣ እድገት፣ ማኅበራዊ ፍትህ ሁሉም የሚፈለጉ ጸጋዎች ናቸው:: ግን ችግሩ ብዙ ጊዜ ሲታረኑ እናያቸዋለን:: እንዳመጣጣቸው፣ እንደተጨባጩ የሕብረተሰብ ሁኔታ በተቻለ እነሱን ለማጣጣም መሞከር እንጂ እዚህን ሁሉ በአንድነት የሚያነግስ ሥርዓት አመጣለሁ ማለት አይቻልም:: ለዚህ ነው ከወዲሁ አንድ ያለቀለት«ንድፈ ሥርዓት» ይዞ መታገል አስቸጋሪ የሚሆነው:: ከዚህ ይልቅ አስቀድሞ ለዲሞክራሲ፣ ምንም ዓይነት «ከፍተኛ ዓላማ» ለማይሸርፈው የሕግ የበላይነት መታገልና በዚህ ክልል ውስጥ እንደ ህዝቡ ምርጫ፣ እንደብዙሃኑ ፍላጐት፣ እንደሀገሪቱ ተጨባጭ የኢኮኖሚ እድገት ሁኔታ ምንጊዜም ወደተሻለ ማኅበራዊ ፍትህ የሚወስድን ፖሊሲ መቀየስና ለሱ መታገል የሚያስፈልገው::

ጥያቄ፣ ለምን አዲስ አበባው ጉባዔ ላይ አልተገኙም?

መልስ፣ የአስተባባሪው ኮሚቴ ሰብሳቢ እንደመሆኔ መጠን በዚህ ጉባዔ ላይ አለመገኘቴ እንግዳ ነገር ሊመስል ይችላል:: እንዳልሄድ ከመወሰኑ በፊት ከትግል ጓደኞቼ ጋር ብዙ ተነጋግረናል:: ይህ የጠነሰስነው የሰላም ጉባዔ የማይዋጥ የማይተፋ ነገር የሆነበት ኢህአዴግ ጉባዔውን መከልከል ባይቻለው አንዳንድ መሰናከሉችን በመፍጠር ሊያሰናክል ይችላል የሚል ስጋት ነበረን:: በመሆኑም ምንም ዓይነት ሰበብ ላለመስጠት ተስማማን:: ከነዚህ ሰበቦች አንዱ እኔን በማይመለከተኝ ቀይ ሽብር ወንጅሉ ለማሰር የነበረው ፍላጐት ነው:: «የሰላምና እርቅ ጉባዔው አስተባባሪ ተወንጅለው ታሠሩ» ብሉ ውዥንብር ለመፍጠር:: ይህንን እድል ለኢህአዴግ ለመስጠት አልፈለግንም:: በነበሩን መረጃዎች እኔን እንደሚያስሩኝ እርግጠኛ ነበርን:: ግን አንድ ነገር ግልጽ መሆን ይኖርበታል:: በዚህ ምክንያት አዲስ አበባ አለመግባቴ ወንጀለኛነትን መቀበል አይደለም:: የሰዎቹን ዴሞክራትነት በመጠራጠር እንጂ::

ይህ ስለተባለ ትንጅቱም ሆነ መኢሶን ለዚህ ጉባዔ መጠንሰስና መሳካት፣ በሃገራችን ሰላም እንዲወርድ ያላቸውን ከፍተኛ ጉጉት ለመግለጽ ሲሉ ወደ አዲስ አበባ የላኩት ከፍተኛ ቡድን ነበር:: ከኔ የተሻለ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ታጋዮች ናቸው:: ይህን ስናደርግ ባወጣ ያውጣቸው ብለን አይደለም:: ሰላምና እርቅ ብለው የመጡ ልኡካንን በስመ ትንጅት አፋፍሶ ያስራል ብለን አልጠበቅንም ነበር:: ሰዎቹ ባይገባቸው ነው እንጂ ይህንን ርምጃ ስንወስድ ርዝራዥም ብትሆን ትንሽ ዲሞክራትነት አያጡም፣ ለመድኃኒት ታህልም ብትሆን አንዳንድ የሞራል መርሆዎች ተርፏቸዋል፣ ጠብታም ትሁን የፖለቲካ ብስለት አላቸው ብለን ማመናችን ነበር:: ሳየው ከሁሉም አንጻር ተሳስተናል:: ምርጥ ታጋዮቻችንን እነገነትን፣ አበራን፣ ገነነውን፣ መስፍንን ለእስር እንድንዳርግ ያደረገን ስህተት ነው:: የመኢሶን ዋና ጸሐፊና የትንጅቱ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ ጓድ አበራ የማነአብ ገና በኢህአዴገ እጅ ለብዙ ጊዜ ተንገላቷል:: በትግል ዓላማና በሀገር ፍቅር መንፈስ የተገነባውን የትንጅቱን አንድነት እናላለን ብለው አስበው እንደሆነ ተሳስታችኋል እንላቸዋለን:: ጓድ አበራ በሐቀኝነቱና በሕዝብ ፍቅሩ ምንም የማይወጣለት ቆራጥ ታጋይ እነደሆነ እንኳን እኛና እነሱም አሳምረው ያውቁታል:: ለኢትዮጵያ ሕዝብ ገና ከለጋ ወጣትነቱ ጀምሮ ባስመዘገበው የትግል ታሪክ የምናፍርበት አንዲትም የፈጸመው ወንጀል የለውም:: በምን ተጨባጭ ነገር እንደሚወነጅሉት ጨንቋቸው ነው ነጋ ጠባ ፍርድ ቤት አመላልሰውታል:: ከዚህ መሠረታዊ ችግር የሚወጡበት መንገድ በማጣታቸው እንደሆነ ግልጽ ነው::

ጥያቄ፣ ለኢትዮጵያ ችግር መፍትሔው ምን ይመስልዎታል?

መልስ፣ ለኢትዮጵያ ውስብስብ ችግሮች ቀላልና አንድ ወጥ መፍትሔ የለም:: ከዚህ በፊት እንዳልኩት ቢኖር እስከዛሬ ይሰማ ነበር:: እንኳን መፍትሔው ላይ ችግሩ ምን እንደሆነም መግባባት የለም:: በበኩሌ መፍትሔውን ከመትጠይቁኝ ችግራችንን ስለምንፈታበት ዘዴ ብትጠይቁኝ ይሻለኛል:: ዘዴው ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ውይይት ነው:: እንዲህ ዓይነቱ ውይይት ደግሞ ለዚህ ወይ ለዚያ ትግር መፍትሔ ለመስጠት አይደለም:: ዘላለማችንን ብንወያይ ለሀገራችን ችግሮች ድፍን ኢትዮጵያ የሚስማማበት አንድ መፍትሔ አናገኝም:: የውይይቱ ዓላማ አንድ ብቻ ነው:: ሁሉም የበኩሉን መፍትሔ ይዞ ለዚያ በሰላምና በዲሞክራሲ የሚታገልበትን መድረክና ክልል በጋራ ስምምነት ለመገንባት ነው:: ይህ የጎራ መድረክና ክልል (ፍሬምወርክ) የህጐች ሁሉ የበላይ የሆነው ሕገ መንግሥት ነው:: ዛሬ የዚህ የህገመንግሥት ጥያቄ የሀገራችን ቁልፍ ጥያቄ እንደሆነ ለሁሉም ግልጽ ይመስለኛል:: ግን ደግሞ የኔ የግል አስተያየቴ/ ምናልባት አስር ዓመት ያህል ሕግ ስማር ወደመጨረሻው ላይ ያተኮርኩት ሕገመንግሥት ትምህርት ላይ በመሆኑ ይሆናል/ ለዚህ ቁልፍ ጥያቄ ገና በቂ ትኩረት አልተሰጠውም:: ይህንን የሰጣችሁኝን አጋጣሚ ተጠቅሜ በዚህ ጉዳይ ላይ ትንሽ ዘርዘር አድርጌ ሃሳቤን ልግለጽ::

የሚረቀቀው ህገ መንግሥት የሀገሪቱ የበላይ ሕግ እንደሚሆንና ለረዥም ዘመን ሊያገለግል ሆና መነደፍ እንዳለበት ስምምነት አለ:: ይህ ሕግ በአንዲት የታሪክ አጋጣሚ ከሕዝቡ 51 ከመቶ ያገኘ የፖለቲካ ኃይል በተቀረው 49 ከመቶ ላይ የሚጭነው ሳይሆን በሁብረተሰቡ ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካም ሆነ የጥቅም ቡድኖች በሙሉ ተደራድረው በተቻለ መጠን በጋራ ስምምነት የሚያጸድቁት መሆን እንዳለበት የህገ መንግሥት ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ ያለ አስተሳሰብ ነው:: እንደተራ ሕግ በተራ ድምፅ ብልጫ የማይሻር፣ የማይሻሻል ሰነድ ነው:: ለዚህም ነው ከወዲሁ ሲረቀቅና ሲጸድቅ በተቻለ በጋራ ስምምነት እንጂ በተራ ድምፅ ብልጫ መሆን የሌለበት::

እንደዚህም በመሆኑ አንድ ህገ መንግሥት ይዘቱ ብቻ ሳይሆን የሚረቅበትና የሚጸድቅበት ሂደት በጣም ትልቅ ቁም ነገር ያዘለ ነገር ነው:: እንዲያውም ዛሬ ስለሚጭው ህገመንግሥት ይዘት መከራከር ጊዜው አይመስለኝም:: ማን የመጀመሪያውን ንድፍ ያርቅቀው የሚለውም ጥያቄ እስከዚህ አንገብጋቢ ጥያቄ አይደለም:: ፕሬዚዳንት መለስ ቤት ዘግተው የህገመንግሥት ንድፍ ይኸውላችሁ ቢሉን እኔ ግድ የለኝም:: ከሁሉ ቁልፍ ጥያቄ ግን ይህንን ህገመንግሥት ማን ያርቅቀው ሳይሆን ማንና እንዴት ያጽድቀው የሚለው ጥያቄ ነው:: ኢህአድግ የራሱን ረቂቅ ማቅረብ ይችላል:: አማራጭ አለን የሚሉ ኃይሉች ደግሞ የራሳቸው አማራጭ ረቂቅ አቅርበው በዚያ ላይ በሕዝብ ፊት ክርክሮች ሊካሄዱ ይችላሉ::

ዋናው ጥያቄ ይህ ህገ መንግሥት በህዝብ ነጻና ርትአዊ ምርጫ

በተስየመ የሕ፤መንግሥት ጉባዔ እንዲጸድቅ ማድረጉ ላይ ነው። ዋናው ጥያቄ ብዙሃን ይሁኑ እናሳ፣ ከህብረተሰቡ 40 ከመቶ ይወክሉ፣ 15 ከመቶ የተለያዩ ኃይሎች ሕዝቡ በምርጫው እንደሚሰጣቸው ከብደት እየታየ የሚወከሉበት ጉባዔ ማቋቋሙ ላይ ነው። ከፍ ብዬ የሀገራችን ችግር የሚፈታው በውይይት ነው ስል ይህ ውይይት ሁሉንም አሉ የሚባሉትን ኃይሎች የሚያሳትፍ መሆን እንዳለበት ተተብዬ ነው። ለዚህ ውይይት አማካይ መድረክ ደግሞ ይኸው የህገ መንግሥት ጉባዔ ሆኖ ይታየኛል።

እንግዲህ ሁለት ነጥቦች አሉ። አንደኛ ነጻና ርትአዊ መርጫ። ሁለተኛ ሁሉንም የሀገሪቱን የፖለቲካና የጥቅም ቡድኖች ያካተተ፣ በነጭና ጥቁር ብቻ ሳይሆን እንደባለተም ፎቶግራፍ የሀገሪቱን የፖለቲካ፣ የርዕዮተ ዓለም፣ የባህል ስብስቦች የሚያንጸባርቅ የሕገ መንግሥት አውጭ ጉባዔ መሰየም። ከሁለቱ አንዱ ከጉደለ ውሃ ትዳ ውሃ መልስ ነው። ዘላቂ ህገመንግሥት ዘበት ነው።

ችግሩ የኢህአዴግ ሂደት ከምንም የለበትም። ለነጻ ምርጫ ብሎ ያቀረበው የምርጫ ሕግ ዛሬ መላው ዓለም ከተቀበላቸው የነጻና ርትአዊ ምርጫ መለኪያዎች ጋር ሲገናዘብ ከምንም የሌለ ሕግ ነው። አማራጭ ኃይሎችም ሆኑ በጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ዓለም አቀፍ ተጽዕና አድርገው ነፃና ርትአዊ ምርጫ የሚካሄድበት ሁኔታ ቢፈጠርም ደግሞ ሌላም መጠየቅ ያለብን ነጥብ አለ። የሚመረጠው የሕገ መንግሥት ጉባዔ የረባ የውይይት ጉባዔ እንዲሆንና ሁሉን ያካተተ እንዲሆን ከተፈለገ ኢህአዴግ የመረጠው የምርጫ ሥርዓት /ኢሌክትራል ሲስተም/ ጨርሶ መለወጥ ይኖርበታል።

የመጀመሪያው ነጥብ ላይ ትንሽ ላብራራ። በኢህ፤ዴግ ሂደት ነጻና ርትአዊ ምርጫ አይገኝም። በዚህ ጉዳይ ላይ የኢህአዴግን የምርጫ ሕግ ጉድለቶች ለመጠቆም ብቻ ሳይሆን አንድ ሌላ አማራጭ ሂደት ለመጠቆም እንዲቻል አማራጭ ኃይሎች አንድ ግብረ ኃይል መሰየም ይኖርባቸዋል። የምርጫውን ሕግ ጠልቄ ገና አላጠናሁትም። እንዲሁ ገረፍ ገረፍ ሳደረገውና በተለይ ደግሞ እንዲሁ እንደኛው ከረዥም ጊዜ ጦርነት ወጥታ ምርጫ ካካሄደችው ከካምቦጅ ሁኔታ ጋር ሳነጻጽረው እጅግ ዓይን ያወጡ ጉድለቶች አሉበት።

*መጀመሪያ* ነገር ከወዲሁ መጠየቅ ያለበት የኢህአዴግ ህግ እንደሚለው ታዛቢዎች እንዲኖሩ ሳይሆን ሂደቱንም ሆነ ምርጫውን የሚቆጣጠሩ የዓለም አቀፍ ኮሙኒቲ ተወካዮች ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊ ነው። በካምቦድያ የተደረገው እንደዚህ ነው።

*ሁለተኛ* ለመወዳደር የሚሹ ፓርቲዎች ሁሉ በነጻነት መወዳደር መቻል አለባቸው። የኢህአዴግ ሕግ ይህንን አያረጋግጥም። በተለይ የፓርቲዎች ሕግ የተባለው የሚያስቀምጣቸው መስፈርቶች /ጸረ ሰላም የሆኑ፣ ኢትዮጵያ የተፈራ ረመቻቸውን ዓለም አቀፍ ውሉች የሚቃወሙ. . . /እያለ ብዙ ይደረድራል። ችግሩ መስፈርት ማስቀመጡ ላይ አይደለም። አንድ ድርጅት የተባሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለማሟላቱን የሚወስነው ራሱ ኢህአዴግ መሆኑ ነው። በካምቦድያ ይህ ኃላፊነት የተሰጠው ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ለተመድ) ነው።

*ሦስተኛ* የማስ ሚዲያው ጥያቄ አለ። ሁሉም ተወዳዳሪዎች በእኩልነት እንዲጠቀሙ ከተፈለገ ወይ አንድ ገለልተኛ ኮሚሽን ወይ ደግሞ ከሁሉም ፓርቲዎች የተውጣጣ አካል መፈጠር ይኖርበታል። በካምቦድያ አሁንም ይህ ኃላፊነት የተሰጠው ለተመድ ነበር። እኛ አገር ግን ለማስታወቂያ ሚኒስትሩ ነው።

*አራተኛ* ገለልተኛ የሆነ የምርጫ ቦርድ ያስፈልጋል። ይህም ከፓርቲዎች የተውጣጣ ሊሆን ይችላል። ወይ እንደ ካመቦድያ በዓለም አቀፍ ኤክስፐርቶች፣ በተመድ ቁጥጥር ሥር የሆነ። እኛ አገር ቦርዱን የሚሰይመው የተወካዮች ምክር ቤት ነው። ሊቀመንበሩን የሚሾመው ፕሬዚዳንቱ ነው።

*አምስተኛ* ሁሉም የተስማማበት የምርጫ ሕግ። ይህ ካልሆነ አንዱ ቡድን ብቻ ባወጣው ደንብ መሠረት ኳስ ግጥሚያ እንደማሄድ ነው። አይሰራም። አሁንም ካምቦድያ ይህ ተግባር በተመድ ተሳትፎ የተካሄደ ነው። እኛ አገር ኢህአዴግ በመሰለው በሚያመቸው ነው የሠራው።

*ስድስተኛ* ነጻና ርትአዊ ምርጫ ስንል ዜጎችን በሙሉ የሚያሳትፍ መሆን አለበት። የኢህአግ ሕግ እስከናካቴው ባለሦስት ማዕረግ ኢትዮጵያውያን ፈጥሯል። አንደኛ ማእረግ ኢትዮጵያው ያን የመምረጥም የመመረጥም መብት ያላቸው። ሁለተኛ ማእረግ ኢትዮጵያው ያን የመምረጥ እንጂ የመመረጥ መብት የሌላቸው። ሦስተኛ ማዕረግ ኢትዮጵያው ያን የመምረጥም የመመረጥም መብት የሌላቸው። ይኸ ሦስተኛው ማእረግ እኛን በውጭ የምንገኘውን ስደተኞች የሚጠቀልል ነው። በኢትዮጵያ ጉዳይ ምንም መብት የለንም ማለት ነው።

*ሰባተኛ* በምዝገባ ጣቢያዎች የተወዳዳሪ ፓርቲዎች ተወካዮች የሉም። በድምጽ ቆጠራውም ጊዜ እንደዚሁ ሰዝገ ችሉት ነው። ይህ በየትም ምርጫ ያልታየ ጉድ ነው። እንደገና ወደመቦድያ ብንመለስ ተመድ ተደም ብሉ ባካሄደው የሲቪክ ትምህርት ፕሮግራም ላይ ምዝገባና ቆጠራ ሰዎች ሲያሰለጥን ተወዳዳሪ ፓርቲዎችም በዚህ ተግባር የሚወከሏቸውን በሺህ የሚቆጠሩ አባላት ሰይመው ለእነሱም ስለምዝገባና ስለቆጠራ ልዩ ኮርስ ተሰጥቷል።

*ስምንተኛ* በመርጫው ጊዜ የጸጥታን ጉዳይ በሚመለከት የኢህአዴግ ህግ የሚለው በምርጫው ጊዜ የታጠቁ ሰዎች ከግማሽ ኪሎሜትር በላይ እንዳይጠጉ ብቻ ነው የሚያዘው። በዚያን ሰሞን የታጠቁ ኃይሎች ሁሉ በየጦር ሰፈራቸው ስለመካተታቸው፣ ይህ ደግሞ ከሥራ ላይ እንዲውል ስለሚያስፈልገው ቁጥጥር አያነሳም። አሁንም በካምቦድያ ይህ ተግባር የተሰጠው ለተመድ ነበር።

ከፍ ብየ እንዳልኩት ይህ ሁሉ የኢህአዴግን የምርጫ ህግ እንዲያው ገረፍ ገረፍ ሲያደረጉት የሚታይ ጉድለት ነው። አማራጭ ኃይሎች በርግጥ ለነጻና ርትአዊ ምርጫ የቆሙ ስለሆኑ በዚህ በኩል ያላቸውን አስተሳሰብ በተቀናበረ መልክ ለማቅረብና ሕዝቡን ለመቀስቀስ አንድ የጋራ የሆነ ግብረኃይል አቋቁመው መሥራት ይኖርባቸዋል። ግን ደገሞ የምናወራው ስለመንግሥት መመረጥ ወይም ደግሞ ስለተራ ህግ ሳይሆን ስለህገመንግሥት መጽደቅ እስከሆነ ድረስ በኔ ግምት ነጻና ርትአዊ ምርጫም በቂ አይደለም። ለታህሳሱ ጉባዔ ባቀረብነው ሰነድ ላይ ይኸ በግልጽ ተቀምጧል። መጀመሪያ ለማንኛውም ምርጫ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሟሉ መታገል። ከዚያ ተያይዞ ደግሞ ለሕገ መንግሥት ጉባዔ ተስማሚ የሆነ የምርጫ ሥርዓት ያስፈልጋል።ይኸውም በዚያው ሰነድ ላይ እንደተገለጸውና በጉባዔው እንደተጠየቀው የምርጫው ሥርዓት ተመጣጣኝ ውክልና (ፕሮፓርሽናል ሪፕሬዘንቴሽን) መሆን አለበት ማለት ነው። በኔ ግምት ይህ

የሚመሪ ጠው የሕገ-መንግሥት ሸንጐ ሁሉን አቀፍ እንዲሆን፣በኢትዮጵያችን የሚገኙ ኃይሎች ሁሉ የሚወከሉበት እንዲሆን፣ ከዚህም ሸንጐ የሚወጣው ሕገመንግሥት በርግጥ የሀገሪቱ የበላይ ብቻ ሳይሆን የሁላችንም የጋራሰነድ እንዲሆን ከተፈለገ ይህ የምርጫ ሥርዓት የማይታለፍ ነው። እዚህም ላይ ነገሩ ቢረዝምም ትንሽ ላብራራ እፈልጋለሁ ።

በመሠረቱ ሁለት ዋና ዋና የምርጫ ሥርዓቶች (ኢሌክቶራል ሲስተሞች)አሉ። የብዙሃን ምርጫ ሥርዓት (ማጆሪቲ ሲስ ተም)የተመጣጣኝ ውክልና ሥርዓት(ፕሮ ፓርሽናል ሪፕሬዘንቴሽን) እነዚህ ራሳቸው በውስጣቸው ንዑስ ሥርዓቶች አሏቸው። ብዙ ዝርዝር ውስጥ አልገባም።

አንደኛው የብዙሃን ምርጫ ሥርዓት ነው። በዚህ ሥርዓት መሠረት ሀገሪቱ ፓርላማ ውስጥ ባለው ወንበር ልክ በምርጫ ቀበሌዎች ትሸነሸናለች። በፓርላማው ውስጥ አንድ ሺህ ወንበር ካለ በሀገሪቱ አንድ ሺህ የምርጫ ቀበሌዎች ይኖራሉ። አንድ ሺህ ተወካዮች ተመርጠው ወደ ፓርላማ ይመጣሉ። ካየቀበሌ አብዛኛውን ድምፅ ያገኙት ከየምርጫ ያገኙት ግን እንግዲህ የአብዛኛው ድምፅ ሲባል ሁለት ዓይነት ሊሆን ይችላል። ብዙውን ጊዜ አንድ ተመራጭ ከአንድ የምርጫ ክልል ተመርጦ ወደ ፓርላማው እንዲመጣ ከጠቅላላው ድምጽ ከ50 ከመቶ በላይ ማግኘት አለበት። ብዙ ተወዳዳሪዎች ሲኖሩ ማገኛቸውም በመጀመሪያው ዙር ከግማሽ በላይ እያገኙ ይሆናል። ስለዚህ ሁለተኛ ዙር ይዘጋጃል። ከሁሉ ከፍተኛ ድምጽ ያገኙት ሁለት ወይም ሦስት ተወዳዳሪዎች ይቀሩና ሌሉቹ ከውድድሩ ይወጣሉ። ብዙውን ጊዜ ደግሞ በዚህ መልክ ከውድድሩ የሚወጣት «ለኔ ድምጽ የሰጣችሁ ሁሉ ለእገሌ ድምጽ ስጡ» እያሉ ጥሪ ያደርጋሉ። ኢህአዲግ የመረጠው ይህንን እንኳን አይደለም። ፈልፍሉ እንዳመቸው ያወጣው ሥርዓት የዚህ የብዙሃን ምርጫ ሥርዓት ንዑስ ክፍል የሆነውን «ከፍተኛ ድምፅ» ሥርዓት ልንለው የምንችለውን ነው። አንድ እጩ ከአንድ የምርጫ ቀበሌ «ተመረጠ» ተብሉ ለመምጣት የግድ ከ50 ከመቶ በላይ ማግኘት የለበትም። 20ም 30ም ከመቶ ድምጽ ቢያገኝ ከሌሉቹ ተወዳዳሪዎች ሁሉ ከፍተኛውን ድምጽ ካገኘ ይበቃዋል። ይህን ንዑስ ስርዓት ኢህአዴግ ለምን እንደመረጠ ዝቅ ብየ ለመጠቆም እሞክራለሁ።

ሁለተኛው የምርጫ ሥርዓት ተመጣ ጣኝ ውክልና (ፕሮፓርሽናል ሪፕሬዘንቴሽን) ሥርዓት ነው። በዚህ ሥርዓት መሠረት ለምርጫ የሚቀርቡት በአብዛኛው ግለሰቦች ሳይሆኑ ድርጅቶች ናቸው። በፓርላማው ውስጥ አንድ ሺህ ወንበር ስላለ ሀገሪቱ አንድ ሺህ የምርጫ ቀበሌዎች ተደርጋ አትሸነሸንም። ወይም እንዳለ ሀገሪቱ አንድ የምርጫ ቀበሌ ትሆናለች። ወይም ደግሞ በተወሰኑ ታላላቅ የምርጫ ክልሎች ማለትም አምስት ወይም አስር ወዘተ ቦታ ትሸነሸናለች። ፓርቲዎች በሀገር ደረጃ የቻሉትን ያህል የዜጎች ድምጽ ለማግኘት ይወዳደራሉ። አንድ ፓርቲ በፓርላማው ውስጥ የሚያገኘው ወንበር በጠቅላላ እንዳገኘው ድምጽ ይወሰናል ማለት ነው። ለምሳሌ አንድ ሺህ ወንበር ላለበት ፓርላማ 20 ሚሊዮን መራጭ ካለ አንድ ወንበር ለማግኘት 20ሺህ ድምጽ ማግኘት ያስፈልጋል ማለት ነው። እርግጥ ትርፍራፊ ድምጾች ይኖራሉ እነሱንም የማከፋፈያ ሥርዓት አለ። ዋናው ቁም ነገር ግን በዚህ ሥርዓት መሠረት ፓርቲዎች በህብረተሰቡ ውስጥ እንዳላቸው ክብደት እየታየ በፓርላማው ውስጥ ወንበር ይሰጣቸዋል። 20ሺህ ድምጽ ያገኘ ፓርቲ አንድ ወንበር፣ መቶ ሺህ ድምጽ ያገኘ ፓርቲ 5 ወንበር ወዘተ - - -

ሁለቱም የምርጫ ሥርዓትቶች የየራሳቸው ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሏቸው። የብዙሃን ምርጫ ሥርዓት በፓርላማው ውስጥ ግልጽ የሆነ ብልጫ ስለሚያስገኝ ለተወሰነ ጊዜ ለተመረጠ መንግሥት ትልጥፍናንና መረጋጋትን ያስገኛል። ግን ደግሞ እስከሚቀጥለው ምርጫ ድረስ «ከግማሽ በላይ አንዲት ድምጽ ያመጣ ሁሉም ነገር ሲኖረው ከግማሽ በታች አንዲት ድምፅ የወረዳ ምንም ነገር የለውም። የኢሕአዴግ ንዑስ ሥርዓት ደግሞ ይህ አግጦና አፍጦ የሚታይ ነው።ከየምርጫ ቀበሌው 20ም 30ም ከመቶ እያመጡ ፓርላማ የሚደረሱት ተወካዮች በያለበት 80ም 70ም ከመቶ መራጮችን በየቀበሌው እያራገፉ የመጡ ተወካዮች ይኖራሉ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ አሠራር ለተራ የመንግሥት ምርጫ ምንም ችግር ላይኖረው ይችላል። ይህ መንግሥት እንዲሁ በተራ ምርጫ ከአራትም ከአምስትም ዓመት በኋላ ቦታውን ለሌላ ይለቃልና። እንደ ህገ መንግሥት ላለ ዘላቂና የሁሉንም አግባብ ያገኘ ሰነድ ለማጽደቅ ግን ሌላ ጥያቄ ነው።

ተመጣጣኝ ውክልና ከዚህ አንጻር ሲታይ ማገኛውም የህመንግሥት ኤክስፐርት የማይክደው አወንታዊ ገጽታ አለው። ይበልጥ ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ ነው። በጠቅላላው በሀገሪቱ አንድም ሁለትም ከመቶ ብቻ ከሚያመጡ ድንክ ፓርቲዎች በስተቀር በህብረተሰቡ ውስጥ አለሁ የሚል ኃይል ሁሉ እንደአቅሙ በፓርላማው ውስጥ ይወከላል። ይህ የምርጫ ሥርዓት እንደ ባለቀለም ፎቶግራፍ ነው የምለው ለዚህ ነው። ይህ መልካም ገጽታው ሲሆን በዚህ መልክ የተቋቋመ መንግሥት ትልጥፍና ያንሰዋል። ፓርቲላማው «የጨረባ ተዝካር» የሚሆንበት አደጋ አለ። የፈረንሳይ ፓርላማ ከደጉል በፊት፣ የጣልያን ፓርላማ እስከዛሬ ይህ ሁኔታ ይታይባቸዋል። በዚህ የተነሳ ለአራት አምስት ዓመት ለሚመረጥ መንግሥት ይህ የምርጫ ሥርዓት እምብዛም አይፈለግም። ለህገመንግሥት አውጭ ጉባዔ ምርጫ ግን እስከዛሬ ከሱ የተሻለ የምርጫ ሥርዓት አልተገኘም። በቅርቡ በካምቦድያ የተካሄደው ምርጫ አሁን ደግሞ በደቡብ አፍሪካ በመዘጋጀት ላይ ያለው ምርጫ የተቀበሉት ሥርዓት ይኸው ነው።

የኢህአዴግ የምርጫ ሥርዓት ለሀገራችን እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ሁሉን አቀፍ የሆነ ውይይትና ድርድር የሚያስችል አይደለም። ከዚህ አልፎ በየቀበሌው ሲደመሩ ሰባም ሰማንያም ከመቶ የሚሆኑ ዜጎች ያልመከሩበት ወይም የተቃወሙት የአንድ ንዑስ ኃይል ሕገ መንግሥት የሚጸድቅበት ሁኔታ ይፈጠራል። ለምንፈልገው ሰላምና ዲሞክራሲ፣ ሀገራችንና ህዝባችን ለሚያስፈልጋቸው መረጋጋት በጣም አደገኛ ሁኔታ ይፈጥራል። ምክንያቱ ግልጽ ነው። ህገ መንግሥት ተራ ሕግ አይደለም። ሲጸድቅ ከፍተኛ ስምምነት (ኮንሲንስ) ያስፈልገዋል የሚባለውን ያህል እንዲሻሻል፣ እንዲለወጥ፣ አንዱ አንቀጹ እንድትነካ እንደ ተራ ህግ ተራ ድምጽ ብልጫ አይበቃውም። ሁለት ሶስተኛ፣ ሶስት አራተኛ እየተባለ የተጠናከረ የብዙሃን ድምፅ ያስፈልገዋል።

<u>ጥያቄ</u>፣ ኢህአዴግ ለምን ይህንን ንዑስ ሥርዓት መረጠ?

<u>መልስ</u>፣ ተመጣጣኝ ውክልናን ያልመረ ጡበት ምክንያት ከሰዎቹ አስተሳሰብ ጋር የተያያዘ ይመስለኛል። ተመጣጣኝ ውክልና ራሱ ጽንሰ ሃሳቡ ውይይት፣ መግባባት፣ የሌላውን ሃሳብ ከፍት በሆነ አእምሮ ማዳመጥ፣ ከሌላው አስተሳሰብ ጠቃሚ ነገር ሊኖር ይችላል ብሎ ከወዲሁ መዘጋጀት፣. . . እነዚህን ሁሉ የሚጠይቅ ሥርዓት ነው። የኢህአ ዴግ መሪዎች የተማከለ (ቶታሊታሪያን) አስተሳሰብ ለዚህ የተመቸ አይደለም።

እናሱ ጠቅልለው የማይቆጣጠሩት ማንኛውም ተቋም ውስጥ ተሳትፈው ዲሞክራሲያዊ ትግል ለማካሄድ ይህ አስተሳሰባቸው አይፈቅድላቸውም።

ከብዙሃን የምርጫ ሥርዓት እንኳን 51 ከመቶ በሁለት ዙር የሚለውን ሥርዓት ያልተቀበሉበትና ነገሩን በአንድ ዙር በከፍተኛ ድምጽ ለመጨረስ የሞከሩ በትም ምክንያት ግልጽ ይመስለኛል። ይኸ ደግሞ የፖለቲካ ስሌት ነው።በህብረተሰቡ ውስጥ አለን የሚሉት የብዙሃኑ ድጋፍ ጨርሶ እንደሌላቸው ያውቃሉ። በተጭበረበረ የምርጫ ሂደት በመጀመሪያ ዙር ከሚወዳደሩት ተወካዮች 20ም ሰላሳም ከመቶ እያመጡ «ከፍተኛ ድምጽ ተገኝቷል» ብለው የማለፍ ተስፋ አላቸው። በሁለት ዙር ከ50 ከመቶ ቢባል ግን ስእሉ ጨርሶ ይለያል። ሁለተኛው ዙር ላይ ተቃዋሚዎቻቸው አብረው እንዳይገጥሟቸው ይፈራሉ። ቀላል ምሳሌ ልስጥ። በአንድ አካባቢ ወይም የምርጫ ቀበሌ አንድ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ህብረት እጩ ከድምጹ 35 ከመቶ፣ የኢዴሃት እጩ 20 ከመቶ፣ የኢህአዴግ እጩ 40 ከመቶ የቀረውን 5 ከመቶ ደግሞ ሌሎች ትናንሽ ፓርቲዎች ይካፈሉት እንበል። እንደ ኢህአዴግ ሥርዓት ከሄድን 40 ከመቶ ያመጣው የኢህአዴግ እጩ ተመረጠ ይባላል። በሁለት ዙር ከ50 ከመቶ በላይ ከተባለ ግን ሁለተኛው ዙር ላይ ቅንጅቱና ሌሎቹ ተቃዋሚ ኃይሎች ከመሃከላቸው ከፍተኛ ድምጽ ላመጣው ለደኢህዴህ እጩ ቦታቸውን ለቀው የነሱ መራጮች ለሱ እንዲመርጡ ጥሪ ሊያደርጉ ይችላሉ። ኢህአዴግ በተቃዋሚ ኃይሎች ህብረት ተሸነፈ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቶቹ ግንባሮች በየቀበሌው ሊያጋጥሟቸው ይችላሉ። በአጭሩ የነሱ ስሌት በየአካባቢው ኢህአዴግ በየምርጫ ቀበሌው እያንዳንዱ ተቃዋሚ ድርጅት ለየብቻው ቆሞ እስከገጠመው ድረስ ከፍተኛውን ድምጽ የማግኘት አነስተኛም ብትሆን እድል አለችኝ ብሎ ያምናል። ሁለትም ሶስትም ድርጅቶች ግን የምርጫ ግንባር ከሠሩበት ነገሩ ጨርሶ ተስፋ እንደሌለው ያውቃል። በህብረተሰቡ ውስጥ የበዙኃኑ ድጋፍ እንደሌለው አናሳ ኃይል እንደሆነ ከኛ በተሻለ ተረድቶታልና።

ፕያቄ፣ የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ኰሉኔል ጉሹ«ነገደ ጉበዜ አመራር ላይ መውጣት የለባቸውም» ብለዋል ብለው ያስተጋባሉ። ልዩነታችሁ ምን ላይ ነው?

መልስ፣ የትኛው አመራር ቦታ? እኔ ለአመራር ቦታ ታግዬም አላውቅም። በሀገራችን የእርቅና ሰላም ጉባዔ እንደሚያስፈልግ፣ ይህ ጉባዔ ምን ይዘት እንደሚኖረው ከመኢሶን እንዲሁም ከቅንጅት አመራሮች ጋር ለረዥምም ጊዜ ተወያይተን፣ በዚህ ጉዳይ ሥራዬ ብዬ እንድገፋበት ከቅንጅቱ አመራር ተልእኮ ከተሰጠኝ በኋላ በተቻለኝ የተለያዩ ድርጅቶችን አማክሬ፣ እነሱም በጉዳዩ ቀደም ብለው አስበውበት ስለነበረ በቀላሉ ማስተባበር ስለተቻለ የፓሪሱን ጉባዔ ግልጽና ዲሞክራሲያዊ በሆነ፣ ሁሉንም ድርጅቶች በአረካ ሁኔታ አዘጋጀሁ። ይህን ጉባዔ እንኳን ልመራ ቀርቶ አልተሳተፍኩበትም። አስተባባሪው ኮሚቴ ሲቋቋም ቅንጅቱ በዚህ ኮሚቴ ውስጥ እንድወክለው መረጠኝ። የኮሚቴው አባላት ደግሞ በሙሉ ድምጽ አስተባባሪ እንድሆን መረጡኝ። ከባድ ሥራና ኃላፊነት ነበር። የተቻለኝን ሠርቼለሁ። ይህ ጉባዔ እንዴት እንደሚታየኝ ከመጀመሪያው ስብሰባ ላይ ግልጥልጥ አድርጌ ለአባላቱ ተናግሬያለሁ። የትም ቦታ ሳይሆን አዲስ አበባ መደረግ አለበት። ስብሰባው የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ መሆን የለበትም ሲቪል ሶሳይቲውም መወከል አለበት፣ ያገባኛል ብሎ ለመገኘት የጠየቀን ሁሉ በከፍት ልቦና መቀበል መቻል አለብን፣ የጉባዔው ዝግጅት በጣም ግልጽና ዲሞክራሲያዊ መሆን አለበት፣ በጉባዔው ላይ የሀገር ሽማግሌዎች መገኘት አለባቸው፣አጀንዳው ቀደም ብሎ ለህዝብም ለተሳታፊ ድርጅቶችም ይፋ መሆን አለበት፣ በዚህ ጉባዔ ዞሮ ዞሮ ኢህአዴግ ስለማይገኝበት አንድ አማራጭ አካል መውጣት ይኖርበታል . . . እነዚህን ሁሉ ለአባላቱ በጽሁፍ አቅርቤ እየተከራከርን እየተፋጨን፣ ግን ደግሞ በወንድማማችነት መንፈስ ተቀራርበን ሠርተናል። በኔ ግምት ጉባዔው የተሳካ ውጤት አስገኝቷል። ኮሚቴው ጋር በአስተባባሪነት ስሰራ ከጉባዔው በኋላ እኔ እንዴት አመራር ላይ እንደምወጣ ሳይሆን ይህ ጉባዔ እንዴት ከፍ ብዬ በጠቀስኩት ዘዴ ይካሄዳል የሚለው ጥያቄ ላይ ብቻ ክር ያተኰርኩት። በነዚህ ጥያቄዎች ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ነበሩ። ይህንን ወደፊት እንወያይበታለን።

በጉባዔው ዝግጅት ወቅት መድኅን ተወካይ ዘንድ ከተንጸባረቁትና ከተከሰቱት አንዳንድ የአሠራር ስልትና የአስተሳሰብ ልዩነቶች በስተቀር እስከዚህም ከባድ ልዩነቶች አልነበሩም። ኰሎኔል ጉሹን አላውቃቸውም። የፖለቲካ ልዩነት አለ ቢባል አንድ ጊዜ አንድ መጽሔት ላይ ያየሁት ቅንጅቱን ትቼ የወጣሁት መኢሶንና ኢህአፓ የግራ ድርጅቶች በመሆናቸው ነው ሲሉ አንብቢያለሁ። የዛሬን አያርገውና እግዜር በሚያውቀው ኢሠፓ ቀኝ አክራሪ ድርጅት አልነበረም። የሆነ ሆኖ እኔ ይኸንን ለትግል ህብረት እንቅፋት የሚሆን ልዩነት አድርጌ አላየውም። የምንፈልጋት ኢትዮጵያ ግራ ሆነ ቀኝ ሁሉም የመሰለውን አስተሳሰብ እየሰዘረ፣ በህዝብ ፊት እየተወዳደረ ሲቀናው አሸንፎ፣ ሳይሳካለት ደግሞ እስከሚቀጥለው ምርጫ በተቃዋሚነት ተከብሮ የሚኖርባት ኢትዮጵያን ነው። የግራና ቀኙ ጥያቄ ያኔ ይመጣል።

እዚህ ላይ ግን አንድ የሚገርመኝ ነገር አለ። ይህ ደግሞ ከኰሉኔል ጉሹ አባባል አልፎ የሚሄድ ነው። የዛሬ ሃያ ዓመት ገድም ሁሉም ከኔ ይበልጥ ኰሙኒስት ለአሳር ነው የሚልበት ጊዜ ነበር። ዛሬ ደግሞ ከኔ ይበልጥ ጸረ ተራማጅ እየተባለ ፉክክር የተያዘ ይመስላል። እነዚያ አልባንያ ሲሉ ከርመው እንኳን ለኛ ለአባሎቻቸውም ፍሬቻ ሳያሳዩ ተቀይረናል አሉን። ነገ እንኳን ለሶሻሊስት አብዮት የታገለና እንዲያው የሶሻሊዝም ስም ሲጠራ ፈገግ ያለ ሁሉ ይያዝ ይጠለፍ የሚባልበት ጊዜ ሳይመጣ አይቀርም። በዚህ አያያዝ እኔ በበኩሌ ከእንግዲህ ደሞ በዛ በኩል እሽቅድድም አልችልም። ግራ ነህ ብለው ሊገጥሙኝ የሚፈልጉ ከገዛ ጥላቸው ጋር ይታገሉ እንደሆን እንጂ እኔን አያገኙኝም። ለማንኛውም ግን ሀገሪቱን ግራ ናቸው ከሚባሉ ኃይሎች እናጸዳለን የሚሉ ኃይሎች ካሉ «እድግም ጡሃራ ከነጻሳ እኩል ነው» የሚለውን የወሉዎች ተረት ላስታውሳቸው። ለዲሞክራሲ አይበጅም።

ፕያቄ፣ እርስዎ ከደርግ ጋር ሥልጣን በተጋሩበት ወቅት ከተቃዋሚ ኃይሎች ጋር እርቅ ሳይፈጥሩ አሁን እንዴት እርቅ ይኑር ይላሉ?

መልስ፣ መጀመሪያ እርቅ በሚለው ሃሳብ መግባባት ያስፈልጋል። እርቅ ማለት ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ መልሶ ይፋቀር፣ ልዩነት የሚባል ነገር ሁሉ ከምድራችን ይጥፋ ማለት አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ የዋህነት ነው። እርቅ ሲባል በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ከፍተኛ ወንጀል የፈጸሙ፣ በተካሄዱት ጦርነቶች ሳቢያ በምርኮኞችም ላይ ሆነ በሲቪሉ ህዝብ ላይ አላስፈላጊ የሆኑ አሰቃቂ ግፎች የፈጸሙ ወይም አሁንም በመፈጸም ላይ ያሉ የመንግሥትም ሆነ የፖለቲካ ድርጅቶች ተጠሪዎች ለፍርድ አይቅረቡ ማለት አይደለም። ፍርድ መቅረብና በሕዝብ ላይ ስለፈጸሙት ግፍ ሕጋዊ በሆነ መድረክ «ሂሣብ ማወራረድ» ይኖርባቸዋል።

እርቅ የምለው ከእንግዲህ በቃ የፖለቲካ ልዩነቶች ደመኛ ጠላቶች አያድርጉን፤ እነዚህን ልዩነቶች ህዝቡ የሚዳኝበትን ዲሞክራሲያዊ መድረክ ተጋግዘን እናብጅ፤ ሁላችንም በዚህ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ክልል ውስጥ መታገልን እንማር:: በዚህም ተጋግዘን ለሁላችንም ለህዝቡም የሚበጅ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊት አገር ለመገንባት ተባብረን እንስራ ማለት ብቻ ነው::

«እርስዎ ከደርግ ጋር ሥልጣን በተጋሩበት ወቅት. . .» ለተባለው በእውነቱ መኢሶን ከደርግ ጋር የሰራበትን የ20 ወራት እድሜ ዋና መልኩ የሥልጣን መጋራት ጉዳይ አልነበረም:: ይህ ዋናው ነጥብ ቢሆን ኖሮ፤ ዓላማችን ሥልጣን መጋራት ቢሆን ኖሮ ተስማምተን፤ አጉብድደን እንደምንም የምንቆይበት ሁኔታ መፍጠር አያቅተንም ነበር:: ከመጀመሪያውም አብረን መስራት የጀመርነው ደርግ አርቅቀን የሰጠነውንና በጊዜው ያመንንበትን ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፐሮግራም በይፋ ስለተቀበለ ነበር:: አብረን የሠራንበት ወቀት እስከዚህም የሥልጣን መጋሪያ ወቅት ሳይሆን ሕዝቡን ከዳር እስከዳር ለማደራጀት የተዋደቅንበት ወቅት ነበር:: ደርግ ከዚህ ፐሮግራም ከተንሸራተተ፤ የኛም ከሱ ጋር መሥራት ለሀገሪቱ ጉዳት እንጂ ጥቅም የማያመጣበት ሁኔታ ላይ ከተደረሰ ለቀን እንሄዳለን ነበር በግልጽና በይፋ እንል የነበረው:: ብዙ ሰው ይህንን አባባላችንን እንደ ተራ ፐሮፓጋንዳ ይወስደው ነበር:: ለሀገራችን የጠቀመ እስከመሰለ ድረስ አብረን ሠራን:: ጉዳ ሲመስለን ደግሞ የሥልጣን ጥም ሳያታልለን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በገባነው ቃል መሠረት ህቡዕ ገባን::

ለምን አሁን እርቅ ትላላችሁ? ለተባለው ከሁለት አንጻር መመለስ ይቻላል:: አንደኛ እኛ ብቻ ሳንሆን ካለፈው መከራና የኢትዮጵያ ሕዝብ ካነባው የደም እንባ ቅንጣትም ትሁን ትምህርት ቀስሜያለሁ የሚል ዜጋ ዛሬ ችግሮቻችንን ሁሉ በሰላማዊና በዲሞክራሲያዊ ውይይት እንፍታ ቢል ምንም እንግዳ ነገር መሆን የለበትም:: ሁለተኛ ደግሞ ዛሬ ያለው የሀገሪቱም ሆነ ዓለም አቀፍ ሁኔታ ከዛሬ 20 ዓመቱ የተለየና ለሰላማዊ ትግልና ለውይይት ያመቸ ሁኔታ ነው ብዬ አምናለሁ::

ካለፈው ትግል የተቀሰመው ትምህርት አለ:: ስላመለጡ የታሪክ አጋጣሚዎች፤ የመወያያ ፋታ ስለነሱ መዋከቦች፤ ወደኋላም መለስ ብለን ታሪካችንን ለመመርመርም ሆነ ወደ ፊትም ወደት እንደምናመራ ሁኔታዎችን ለመቃኘት ስለገ-ደለን የፖለቲካ ብስለት . . . ስለነዚህ ሁሉ ወደፊት እገልፃለሁ:: ከረዥምም ጊዜ የትግል ልምድ ተምህርት ቀስሜያለሁ እያለ የሚገደረደር ሰው ያለፈውን ሂደትም ሆነ መጭውንም ወቅት ለመቃኘት የሚያስችለው ኩረብታ ላይ እንዓለ መቁጠር አለበት፤ ራሱን:: በዚህ መልክ ካለፈው ሂደት የቀሰመውን ትመህርት ለዛሬ ትግሉና ለመጭው ሂደት መቃናት ካላዋለው ከርሞ ጥጃ እንደተባለው ይሆናል፤ በየዕለቱ እንደ አዲስ የሚወለድ ህጻን:: እኔ ካለፈው ተምሬያለሁ:: ከሁሉ በላይ ደግሞ መጭው ጊዜ ያሰጋኛል::

የደርግንና የኢህአዴግን የመሸናነፍ ሁኔታ ሳየው አንዳንዱ እያደር የእህያ ውድቂያ እየሆነብኝ ተቸግሬያለሁ:: እርግጥ በጦሩ ጥያቄ ኢህአዴግ የደርግን ሠራዊት አሸንፏል:: ግን የፖለቲካ ሂደቱን ሳየው የደርግን ብቻ ሳይሆን ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ ገዥዎች የፈጸሟቸውን ስህተቶች ለመቶኛ ጊዜ፤ ለሺህኛ ጊዜ ኢህአዴግም እየደገማቸው ነው:: አሸንፈናል ዝም ብለህ ተገዛ ይለናል:: የአሸናፊዎች ሰላም ይሰብካል:: ለተጭበረበረ ምርጫ በመደረግ ላይ ያለው ቀና ደፋ ማለት፤ በልክ ለተሰፋ ህገመንግሥት የሚደረገው መሯሯጥ ይህንን መሠረታዊ ሃቅ አይሸፍነውም:: ከዚህም የሚከተለው አስቸጋሪ አዙሪት ግልጽ ይመስለኛል:: እንዳለፉት ገዥዎች ይህንን አገዛዝ የሚቃወሙ ትግላቸውን ያፋፍማሉ:: ለሰላምና እርቅ ጉባዔው በቀረበው ሰነድ ላይ እንደተቀመጠው ነው::ኢህአዴግ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ጸረ ዲሞክራሲያዊ ገጽታውን እያጉላ መሄዱ ለዲሞክራሲ የሚታገሉ ኃይሎችን እነሱም በበኩላቸው ትግላቸውን እንዲያፋፍሙ ያደርጋቸዋል:: ትግላቸው እየተፋፋመ ሲሄድ ደግሞ የኢህአዴግ ጸረ ዴሞክራሲያዊ ድርጊቶች እየተበራከቱ እንደሚሄዱ ሳይታለም የተፈታ ነው:: በዚህም ይበልጥኑ እየተጋለጠ፤ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እያጣ፤ ለሕልውናውም ከመሣሪያ ሌላ ምንም መመርኮዣ እየጠፋበት ነገ ከዛሬው ይልቅ የዲሞክራሲ ደብዛ የሚጠፋበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ይህም ደግሞ ለሀገሪቱ ሰላም፤ ለሕዝቦቿ እኩልነትና ዲሞክራሲ የቆሙ ኃይሎችን እነሱም መሣሪያ ወደማንሳት እንዲሄዱ ያደርጋቸዋል:: ኢህአዴግ ራሱ በደርግ ሥር ዲሞክራሲ ጠፋ፤ ሰላም ጠፋ ብሉ «ሰላም በትግል» ብሉ በቀየሰው መፈክር ሥር የመሣሪያ ትግል እንዳካሄደው መሆኑ ነው:: ባጭሩ ሀገሪቱ ወደሌላ አዙሪት ውስጥ የምትገባበት አደጋ አለ:: ለዚህ ነው የሀገሪቱ የዛሬው ሁኔታና በተለይ ደግሞ ከዚህ ሊከተል የሚችለውን የጥፋት ሂደት በመገንዘብ ነገሮች ከቁጥጥራችን ሳይወጡ በፊት ፋታ ወስዶ በርጋታ መወያየት የሚያስፈልገው::

ሁለተኛ ደግሞ ከዛሬ 20 ዓመት ይልቅ ዛሬ ያለው ሁኔታ ችግሮችን በውይይት ለመፍታት የሚያስችል ሁኔታ ነው:: የዛሬ 20 ዓመት በዚያ እጅግ ወደኋላ በቀረ ህብረተሰብ ውስጥ መሬት ላራሹን የመሰለ አብዮታዊ ለውጥ በሰላማዊ ውይይት ከሥራ ላይ የማዋል እድል ነበር ብዬ አላምንም:: የኢትዮጵያ ህዝቦች ከአብዮቱ መፈንዳት በኋላ ያገኟቸውን ድሎች ለማግኘት ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል:: ይህ ብቻ አይደለም:: በመጀመሪያዎቹ 2 እና ሦስት ዓመታት የተጎናጸፉቸውን ድሎች መልሰው ላለመነጠቅ ሲታገሉ ደግሞ እንደዚሁ ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል:: እንግዲህ ከሁሉም ወገን የፈሰሰው ደም ፈሶም ቢሆን ለመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች የጭቆና መሠረት የነበረው ፊውዳል የመሬት ስሪት ፈርሷል:: በዚሁ ትግልና ድል ሳቢያ ደግሞ ለሀገሪቱ እድል ወሳኝ የሆነው የብሔሮች ጥያቄ በዴሞክራሲያዊ ውይይት ሊፈታ የሚችልበት አመቺ ሁኔታ ተፈጥሯል:: የፖለቲካ ዲሞክራሲንም በሚመለከተው እንደዚሁ ነው:: ዛሬ የኢህአዴጉችን ለዚህ መብሰል እጠራጠራለሁ እንጂ የኢትዮጵያም ህዝቦች ሆኑ የፖለቲካ ኃይሎቻቸው ከረዥም ጊዜ የትግል ልምዳቸው በቀሰሙት ትምህርት ምክንያት ለዲሞክራሲያዊ አሠራር ብቁ ናቸው ብዬ እገምታለሁ::

እንግዲህ ከዛሬ 20 ዓመት ይልቅ ዛሬ ችግሮቻችንን በሰላም እንፍታ ስንል ካለፈው ልምዳችን ተነስተንና ከሱ ትምህርት ቀስመን ችግሮችን በተቻለ በሰላማዊ ውይይት መፍታት ያስፈልጋል ብቻ አይደለም የምንለው:: የዛሬውን የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመረምር ደግሞ በኢትዮጵያ ታሪክ ምናልባት ለመጀመሪያ ጊዜ ችግሮቻችንን በሰላማዊ ውይይት ለመፍታት የምንችልበት ሁኔታ አለ ብለን ስለምናምንም ነው::

<u>ጥያቄ</u>፤ የአዲስ አበባው የሰላምና እርቅ ጉባዔ ያሳለፈውን ውሣኔ እንዴት ይመለከቱታል?

<u>መልስ</u>፤ በዚህ ጉባዔ እኛ አልተሳተፍንም:: ግን የጉባዔውን አካሄድም ሆነ ውጤት በምንተችበት ጊዜ «እሷው ወልዳ አልመሰለም፤ እሷው ጋገረ አልበሰለም» የተባለው ነገር

እንዳይሆን መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡ በተለይ የአስተባባሪው ኩሚቴ አባል ድርጅቶች፡፡ ለየት ያለ አስተሳሰብ ሊኖረን ቢችል ከእንግዲህ ወዴት? በሚለው ጥያቄ ላይ እንጂ በጉባዔው አካሄድና ውጤት ላይ ብዙም ሂሳዊ አስተሳሰብ ሊኖረን አይችለም፡፡ ምክንያቱም በጣም ግልጽ ይመስለኛል፡፡ አንደኛ የተላለፉት ውሳኔዎች አስተባባሪው ኮሚቴ ቀደም ሲል ባሰናዳው ሰነድ የተመረኰዘ ብቻ ሳይሆኑ የፓሪሱንም ጉባዔ ውሳኔዎች ፈለግ የተከተሉ ናቸው፡፡ ሁለተኛ የተሳታፊዎችን ሁኔታ የሚመለከት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሕዝባዊ ማህበራት ማኅበራት፣ የሀገር ሽማግሌዎች እያልን የወሰንነው እኛው በሙሉ ድምጽ ሲሆን ከዚህ ውጭ የሆነ ነገር የለም፡፡ ውጤቱንም በሚመለከት ከዚህ ጉባዔ የሚፈልቁትን ውሳኔዎች ለመከታተልና ለማስፈጸም ብቃት ያለው፣ከተሳታፊዎች የተውጣጠ አካል እንዲመሠረት በቅድሚያ ተስማምተንበት ሃሳቡን በሰነዱ ላይ አቅርበነዋል፡፡ የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት ተቋቁሟል፡፡ ይህ ሁሉ የፈለግ ነውና የጠበቅነው ውጤት ስለሆነ በኔ ግምት የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤትን ያለአንዳች ማወላወል መደገፍ፣ እንዲጠናከርም በሃሳብም በሌላም በተገኘው ዘዴ ሁሉ መሞከር ያስፈልጋል፡፡

መጭውን ትግል በሚመለከት ይህ ምክር ቤት ከእለት እለት እየተጠናከረ፣ የኢትዮጵያ ህዝቦችንም ሆነ የዓለም አቀፍ ኩሙኒቲ እየጨመረ የሚሄድ ድጋፍ ለማግኘት በእውነቱ ስለሀገራችን የወደፊት እድል አንድ ዓይነት «ራዕይ» ያለው አካል መሆን ይገባዋል፡፡ ይህ አርቆ አስተዋይነት የዚህ አካል «አማራጭነት» ምን ላይ እንደሆነ ጠንቅቆ መረዳትን ይጠይቃል፡፡ እርግጥ አሁን ያለው መንግሥት ጸረ ዲሞክራቲክ በመሆኑ፣ ለኢትዮጵያ ህዝቦች የጋራ ጥቅም የማይበጅ መንግሥት በዲሞክራሲያዊ ምርጫ ከሥልጣን የሚወርድበትን ሁኔታ ማመቻቸትና ለዚህም መታገል ይኖርበታል፡፡ ግን አማራጭነትን ለኢ.ህአዴግ አማራጭነት ብቻ አድርጉ ማየት ትልቅ ስህተት ይመስለኛል፡፡ ከዚህ ባሻገር አማራጭነቱ ከታሪካችን ከወረስናቸው ጉዷ ከሆኑ የአመጽ፣ የጸረ-ዴሞክራሲ፣ በኃይል ላይ ብቻ የተመረኰዘ የሥልጣን ሽግግር ባህል . . . አማራጭነቱ ለነዚህ ሁሉ መሆን አለበት፡፡ አዲስ የሰላም፣ የዲሞክራሲ ባህል የምንገነባበት፣ የህግ የበላይነት የሚለውን ጽንሰ ሃሳብ የምናነግስበት፣ አማራጭነት መሆን አለበት፡፡ ሰነዱ ላይ እንዳልነው ሽግግሩን አንድ ኃይል ሌላውን ኃይል የሚተካበት ሂደት ብቻ አርጉ ማየት አይቻልም፡፡ ለሀገራችንም፣ ለሕዝቦቻችንም የሚያስፈልጋቸው ከአንድ ጸረ ዴሞክራቲክና ጸረ ሰላም ሥርዓት ወደተሻለ ዴሞክራሲያዊና ሰላም የሚያሸጋግር ሽግግር ነው፡፡ የአማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት በአሠራሩና በዓላማው የዚህ ዓይነቱ ሽግግር ዓይነተኛ መሣሪያ ሆኖ መቅረብ ያለበት ይመስለኛል፡፡

ዛሬ የሚያነሳቸው መፈክሮችና የሚተልማቸው የትግል አቅጣጫዎች ከዚህ አርቆ አስተዋይነት ጠባይ ውስጥ የሚካተቱ እንጂ እሱን የሚጻረሩ መሆን የለባቸውም፡፡ ዋና ዓላማው ህብረተሰባችን በሰላም ወደ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚሸጋገርበትን ዘዴ ቀይሶ የዚህ እውን መሆን መታገል ነው፡፡በዚህ ዓላማ ክልል ውስጥ በመጭው ጊዜ የሚያተኩርበትን የትግል አቅጣጫ በሚገባ መቀየስ ካልቻለ ከፓሪሱ ጉባዔ ወዲህ ለሰላምና ለዲሞክራሲ ትግላችን የታየው የአማራጭ ኃይሉች አንድነት እንዳይበረዝ፣ ለዚህ ትግል በአዲስ መንፈስም የተነሳሳው የሕዝቡ የትግል ወኔ ቅስሙ እንዳይሰበር እፈራለሁ፡፡ ለዚህ በኔ ግምት ምክር ቤቱ ቶሎ ቶሎ ሁሉንም የሚያሰባስብ፣ በኢትዮጵያ ህዝቦችም ዘንድ ሆነ በዓለም አቀፍ ኩሙኒቲ እየጨመረ የሚሄድ ድጋፍ የሚያስገኝ የትግል ዓርማ ይዞ መራመድ ይጠበቅበታል፡፡

በኔ ግምት በሚመጡት ወራት ሁሉም መንቀሳቀስ ያለበት በሰነዱ ላይ እንደ ተቀመጠው ነጻና ርትአዊ ምርጫ በሚለው ጥያቄ ላይ መሆን አለበት እላለሁ፡፡ እዛው ሰነዱ ላይ እንደ ተቀመጠው ለኛም ለኢህአዴግም ይህ ወሳኝ ጥያቄ ነው፣ ቀላል ጥያቄ ይመስላል እንጂ፡፡ ለኢህአዴግ ይህ ጥያቄ ልክ እንደሰላምና እርቁ ጉባዔ የማይዋጥ የማይተፋ ጥያቄ ነው፡፡ ዛሬ በውስጥም በውጭም ስለነጻ ምርጫ ምንነት የጋራ የሆኑ፣ እኛ ሙሉ በሙሉ የምንቀበላቸው ኢህአዴግ ግን በምንም ዓይነት በህዝብ ትግልና በውጭ ወዳጆች ተጽእና ካልሆነና ሥልጣን ለቆ በተቃዋሚነት ትግሉን በዴሞክራሲያዊ ዘዴ ለመቀጠል ካልወሰነ በስተቀር የማይቀበላቸው የነጻ ምርጫ መስፈርቶች አሉ፡፡ ግን ደግሞ አማራጭ ኃይሎች ግልጽ የሆነ አቋም ይዘው በዚህ ላይ ብቻ አተኩረው ከታገሉት ይህንን ድፍን ኢትዮጵያና ድፍን ዓለም የሚቀበለውን ዲሞክራሲያዊና ሰላማዊ አቋም በቀጥታ መቃወም በጣም ይቸግረዋል፡፡ ስለሆነም ክርክሩ፣ ልዩነቱ፣ ጠቡ በዚህ መሠረታዊ ጥያቄ ላይ ሳይሆን በሌሎች አጫፋሪ ጥያቄዎች ላይ እንዳይሆንለት ወይም እንዲመስልለት ይፈልጋል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ወጥመድ ውስጥ ገብተው እንዳይዳከሩ ነው፡፡ ለጉባዔው በቀረበው ሰነድ ላይ አማራጭ ኃይሉች በነጻና ርትአዊ ምርጫ ላይ ማተኩር አለባቸው፡፡

ሌላ የሽግግር መንግሥት እንዲቋቋም ውሳኔ ተላልፎአል፡፡ «እንደተፈራው» የኢህአዴግ ፕሮፓጋንዳ በጉባዔው ማግሥት ሌላውን ሁሉ ቁምነገር ትቶ ያተኩረው እዚህ ጥያቄ ላይ እንደነበረ አይተናል፡፡ የሰው ልጅ መብት ይከበር፣ ነጻና ርትአዊ ምርጫ ይካሄድ፣ መጭው ህገመንግሥት የሚረቅበትና የሚጸድቅበት ሂደት ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች ያካትት ብለው ወሰኑ አላለም፡፡ ሌላ የሽግግር መንግሥት ይቋቋም ተብሎ ለምን ተጠየቀ ማለቱ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ ነጻ ምርጫ እንዲደረግ ዋና ዓላማዎችን እስከሆነ ድረስ አስፈላጊ ከሆነ ለዚህ ምርጫ ሁኔታውን ለማመቻቸት ሌላ መንግሥት እንዲቋቋም መጠየቅ ተገቢ ሊሆን ይችላል፡፡ ኢ.ህአዴግ ዘላቂና የማያወላዳው ዴሞክራሲያዊ ጥያቄያችንን በዚህ በመንግሥት ጥያቄ አከላልሶና አድበስብሶ ለማለፍ መንገድ የማይሰጥ ሁኔታ እስከሆነ ድረስ፡፡

በተጨባጭ የ" የአማራጭ ኃይሎች መጭው ተግባር እንግዲህ ግልጽ ይመስለኛል፡፡ ከሁሉ አስቀድሞ የትኩረት ትኩረት መስጠት ያለብን ባስቸኳይ ነጻ ምርጫ ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ፣ ከዚህ አንጻር የኢህአዴግን የምርጫ ሂደት በምን በምን እንደምንቃወም፣ ነጻና ርትአዊ ምርጫ እንዲደረግ ምን ምን ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው የሚዘረዝር አንድ መግለጫ (ሚሞራንደም) መውጣት ይኖርበታል፡፡ ለዚህም ከሁሉም የተውጣጣ አንድ ኮሚሽኑ ማቋቋም አጣዳፊ ተግባር ይመስለኛል፡፡

ሁለተኛ ይህንን ሰነድ ህዝቡም ሆነ ዓለም አቀፉ ኮሙኒቲ በደንብ እንዲረዳው ማድረግና ድጋፉን እንዲሰጠው ከፍተኛ የቅስቀሳ ዘመቻ መካሄድ አለበት፡፡ ከኢህአዴግ ጋር የሚደረጉ ድርድሮች በዚህ ይፋ በሆነና የህዝብ ድጋፍ ባለው አቋም ላይ ተመርኩዞ ይሆናል፡፡አማራጭ ኃይሎች ከኢህአዴግ ጋር ሲደራደሩ ለዚህ ዓላማ፣ ይህንን አቋም ይዘው መሆኑ ከወዲሁ ግልጽ መሆን ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ በሚመጡት ወራት ባለፈው አንድ ዓመት እንዳዳረግነው በጋራ ህዝቡንም ሆነ ዓለም አቀፉን ኩሙኒቲ ከጉናችን አሰልፈን ወደፊት መጓዝ የምንችለው በዚህ መልክ ይመስለኛል፡፡

# ቀይ ሽብር

**ጥያቄ፡-**የሽግግሩ መንግሥት የቀይ ሽብር ወንጀለኛ ነዎት ይላል፡፡ ይቀበሉታል?

**■.ዐስ፡-**ይህንን ወንጀላ እኔም ድርጅቴም መኢሶን ጨርሶ አንቀበለውም፡፡ ባለፉት 20 ዓመታት በኢትዮጵያ ብዙ እጅግ ብዙ ደም፣ ብዙ ለጅግ ብዙ እንባ ፈሷል፣ በተለያዩ ምክንያቶችና በተለያዩ ኃይሎች አማካኝነት፡፡ በዚህ ወቅት ወንድም፣ እህት፣ እናት፣ አባት፣ ዘመድና ወዳጅ ያላጣ ቤተሰብ ያለ አይመስለኝም፡፡ አሁንም በፖለቲካ ጉዳይ ዜጎች ይታሰራሉ፣ ይሞታሉ፣ እንባ ይፈሳል፡፡ ከሁሉም ወገን የሞቱትና አሁንም የሚሞቱት ሰላሳ ይሁኑ አርባ፣ ሺህ ይሁኑ አስር ሺህ እንዲሁ ዝምብለው ስታቲስቲክስ አይደሉም፡፡ እያንዳንዱ ለማእት እህት፣ ወንድም፣ እናት፣ አባት፣ ዘመድ ወዳጅ ያለው ዜጋ ነው፡፡ ለተራዎቹ ሃዘንና እንባ እየተወ የሚያልፍ፡፡ እንዴት እናት ልጇ በጦር ሜዳ ሞተ በከተማ፣ ከእስር ቤት ተጉትቶ ተረሸነ፣ ከመንገድ ላይ ተደፍቶ ይቅር፣ የኢትዮጵያን አንድነት ለማስከበር ከህወሃትና ከሻዕቢያ ሲተናነቅ አለፈ፣ ወይስ ኤርትራን ለማስገንጠል ከአጼ ኃይለ ስላሴና ከደርግ ወታደር ሲዋጋ ተሰዋ፣ በቀይ ሽብር ተሰሰበ በነጭ ሽብር፣ ለሷ ይኸ ሁሉ በሁለተኛ ደረጃ የሚመጣ ጉዳይ ነሁ፡፡ ልጇን አጥታለች፡፡ እሷ የምታየው ይኸንን ነው፡፡

ባለፉት 20 ዓመታት ስለደረሰው እልቂት ሲነሳ ለተሰውትም ለቀሩትም ክብሬታን በማይነሳ ጥሞና መሆን አለበት፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አስከፊ ዘመን በታሪካችን እንደገና እንዳይመጣ ምን እናድርግ? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ መሆን አለበት፡፡ ካለፈው ትምህርት ለመቅሰም መሆን አለበት፡፡ የፖለቲካ ግጉድ ማካሄጃ ማድረግ ግን እጅግ አስጠያፊና የሚዘገንን ተግባር ሆኖ ነው የማየው፡፡ የተሰውትን ሁለተኛ እንደመግደል፡፡ ቀሪውን ዘመድ አዝማድ እንደገና ለሐዘንና ለሰቆቃ መጋበዝ ነው፡፡

ከፍ ብዬ እንዳልኩት ባለፉት ዘመናት ሕይወታቸው ያለፈው ዜጎች እናቶች ልጆቻቸው በዚህ ዓላማ ይሙቱ በዚያኛው ደንታቸው አይደለም፡፡ አንድ እናት ልጇ በመኢሶን ሥር ተሰልፎ ተሰዋ ግሩም ነው፣ በኢህአፓ ባንዲራ ስር ተሰዋ ጀግና ነው፣ ለአልባንያ ኮሙኒዝም ዓይነት ተዋደቀልኝ ቆራጥ አብዮታዊ ነው፣ በደርግ ባንዲራ ስር ሞተ ያበለው ከሃዲ ነው አትልም፡፡ ያለፉትንም የቀሩትንም ማክበር ማለት ሁሉንም በአንድ ዓይን ማየት ማለት ነው፡፡ ቀሪሉም ይህ ሁሉ ዜጋ መሰዋቱ አስፈላጊ ነበር ወይ? ብሎ መጠየቅ ይገባል፡፡ ይህ ሰማዕትነት ደግሞ የትም ባክና እንዳይቀር ትምህርት መቅሰም ያስፈልጋል፡፡



በኢትዮጵያ ካሉ የፖለቲካ ኃይሎች ሁሉ እንደዚህ ዓይነቱን የራስ ምርምር ሂደት መጀመርና ማካሄድ ያለበት አንድ ኃይል ቢኖር ህወሃት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ከጅምሩ በአመጽ የተጸነሰ ኃይል ነው፡፡ ጦር ሜዳ ሆነ በከተሞች በጅምላ ሆነ በግለሰብ ግድያ ሌሎች ዜጎችን እየገደለ፣ የራሱንም ታጋዮች እየሰዋ እዚህ የደረሰ ኃይል ነው፣ ከሱም ሆነ ከ«ጠላት» ወገን በመቶ ሺህ የሚቆጠር ዘመድ አዝማድ እንባ ባህር እየዋኘ፡፡ ያውም እንግዲህ ለዚህ እጅግ አጠራጣሪ ለሆነ ውጤት፡፡ የህወሃት የአመጽ ሂደት የጦር ሜዳ የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ሂደት ብቻ አይደለም፡፡ እንደደርግ ወታደሮች እሱም ከተሞችንና መንደሮችን ሲይዝ «የጠላት ተባባሪ» እያለ እያሌ ሰዎችን ረሽኗል፡፡ የህወሃት መሪዎች ገና ወደፊት ዝርዝሩ ሲወጣ የሚያፍሩበት ታሪክ አላቸው፡፡ በዛው በድርጅታቸው ውስጥ እንኳ ተቃዋሚዎቻቸውን እያሰሩ፣ እየረሸኑ ነው የመጡት፡፡ ከጥቂት ዓመታት በፊት የቀድሞ የህወሃት መሥራች አባል የነበረ አቶ ገብረመድህን የተባለ ታጋይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የዛሬዎቹን የመንግሥት ተንኳኝ ባለሥልጣናት ስም እየጠራ እንዴት «የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር ተብሎ ይታወቅ የነበረውን የህወሃት ጣውንት ድርጅት «የእርቅ ድርድር» በሚል ሰበብ ጋብዘው በተኙበት . . . እንደጨረሷቸው የሰጠውን ሐተታ ተመልከቻለሁ፡፡ ይህ የጦር ሜዳ የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ድርጊት አልነበረም፡፡ ተራ የነፍስ ግድያ ወንጀል ነበር፡፡ ዛሬ እነሱ የበላይነት ይዘው ያውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከነሱ በተሻለ የሚያውቀውንና እንባ እስኪያልቅበት ያለቀሰበትን የደርግ ግፍ እንደ አዲስ ነገር በጋዜጣም በቴሌቪዥንም ሊነግሩበት ሲሞክሩ ታዝበናል፡፡ ነገ ደግሞ ሌላ ኃይል የበላይነትን ሲያገኝ በድርጅትነት ብቻ ሳይሆን አብዛኞቹ የህወሃትና ኢህአዴግ መሪዎች በነፍስ ወከፍ የፈጸሙት ግፍ ይፋ እንደሚወጣ ትንጣት አልጠራጠርም፡፡

ለዚህ ነው በዚህ ጉዳይ እነ አቶ መለስ ዜናዊ እፍ አለን ብለው ሌሎችን ለመወንጀል ሲሞክሩ ለነሱ አፍራለሁ የምለው፡፡ ዛሬ በሀገራችን ከኩለኔል መንግሥቱ አገዛዝ ቀጥሎ በምንም ምክንያት ይሁን በምንም ለዚህ የአመጽ ሂደት ዋና ተጠያቂ የሆነው ኃይል፣ እንደ ድርጅት ከሁሉ ባነሰ በአመጽ ውስጥ የተሳተፈውን ድርጅታችንን በሀገራችን ለተካሄደው አመጽ ተጠያቂ አድርጎ ለማቅረብ ሲሞክር በጣም ይዘገንነኛል፡፡

እርግጥ መኢሶንን በቀይ ሽብር የሚወነጅለው ኢህአዴግ ብቻ አይደለም፡፡ ብዙ ዜጎች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ባለማወቅ፣ በመመጣበድ፣ በቅንነት፣ ሌሎቹ ሆን ብለው፣ ነገሩን በሚገባ እያወቁት፡፡ ሌሎች ደግሞ ኃላፊነትን ከራስ ለማውረድ፡፡ የኢህአዴግ ከዚህ ሁሉ የሚለይበት አለ፡፡ መጀመሪያ ከሁሉ አመጸኛና ገፊኛ የሆነው ድርጅት፣ ያለፈው አልበቃ ብሎት አሁንም በዚሁ በአመጽ የተሰማራ ድርጅት፣ ከሁሉ ካነሰ በአመጽ ሂደት የተሳተፈውን መኢሶንን፣ ዛሬ የሚካሄድ ሁኔታ ሳይሆን የዛሬ አሥራ ሰባት ዓመት ተፈጸመ በተባለ ወንጀል እፋረዳለሁ ሲል ቢያንስ ቢያንስ አስቀድሞ ራሱን መገምገም ነበረበት፡፡ ሁለተኛ እነዚህ ሰዎች ሥልጣን ሊይዙ ጥቂት ወራት እስኪቀራቸው ድረስ ከመኢሶን ጋር የሚገናኙና የሚደራደሩ ሰዎች ከመሆን አልፈው አቶ መለስ ዜናዊ በአንድ ውይይት ላይ በኢትዮጵያ ምድር ካሉ ድርጅቶች አብረን ልንሰራ የምንችለው ከመኢሶን ጋር ነው ማለታቸው ተመዝግቦላቸዋል፡፡ ዛሬ በዚህ

አባባል እንፈርበት፣ እንኩራራበት ሊላ ጥያቄ ነው:: አቶ አበራ የማነአብን የቢኒመሪ አንድ የመኢሶን ልዑካን ቡድን «በትግሉ ዘመን» እዛው ትግራይ ድረስ ሄዶ ከህወሃት አመራር ጋር ተወያይቶ ተመልሷል:: ታዲያ ይኸንን ሁሉ ጊዜ ከዚህ ወንጀለኛ ድርጅት ጋር እንዴት እንደዚያ ተዳሩ? እነሱ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ መኢሶን አይንህን ላፈር የተባለበት ምክንያት በፖለቲካ ልዩነት ሳይሆን በቀይ ሽብር ምክንያት ነው ቢሉ ማን ያምናቸዋል? ሦስተኛ ልዩነቱ ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ከተራ አሉባልታና ውንጀላ አልፎ በመኢሶን ላይ የሚሰነዘረው ክስ ወደመገናኛ ብዙሃን ተላልፎ አል:: በጉባዔው መጨረሻ ላይ የእርቅና ሰላሙ ጉባዔ ዋና አስተባባሪ የቀይ ሽብሩ ተዋናይ ነገደ ጎበዜ መሆኑ ተደረሰበት የሚል መግለጫ አንብቤያለሁ::

በዚህ በሽብር ጉዳይ ለአመጽና ለግድያ በሺህ የሚቆጠሩ ጓደኞቻችንን እንዳልሰዋን፣ ከኢትዮጵያ ገበሬዎች ጎን ተሰልፈን ስንት ለጋ ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ለባለመሬቶች ጥይት እንዳልዳረግን፣ በ1970 ዓ.ም በመላ ኢትዮጵያ በየከተማውና በየመንደሩ ከአስራ ሰባት ሺህ በላይ መሪዎቻችን፣ አባሎቻችን፣ ደጋፊዎቻችንና ከኛ ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው ዜጎች በኛ ስም በደርግ እስር ቤቶች እንዳልታጎረብን፣ በአዲስ አበባ ብቻ በየሳምንቱ ስንትና ስንት ታጋዮቻችን በየመንገዱ እንዳልተደፉብን፣ መሪዎቻችን ከየእስር ቤቱ እየተጎተቱ እንዳልተረሸኑብን፣ በዚሁ በ1970 ዓ.ም ስንት የመኢሶን አባላት የሆኑ የቀበሌ ተመራጮች በግድያ አንሳተፍም በማለታቸው ብቻ በሰበብ አስባብ በሰደድ መሪዎች እንዳልተረሸኑብን፣ በጥቅምት፣ ኅዳርና ታህሣሥ ወራት ወላጆች ልጆቻቸውን ለማትረፍ በአንዳንድ ገና በኛ ቁጥጥር ሥር ለቀሩ ቀበሌዎች ልጆቻችንን ጠብቁልን እያሉ እያመጡ እንዳላስረከቡን፣ አንዳንድ የታሪክ ደንቆሮዎችና የተጨባጭ ሃቅ እውራን እኛን በቀይ ሽብር መወንጀላቸውን ሳይ አንዳንዴ «ይበለን» ለማለት ይቃጣኛል:: የመኢሶን ሰዎች፣ በተለይ በአመራር ዙሪያ ያለነው አብዛኞቻችን «ብዕር ገፊ» ከሚባለው ክፍል ሆነን እንዴት ይህንን ጉዳይ ማብራራት አቃተን እያልን መቆጨታችን አልቀረም:: ግን ደግሞ ነገሩ ቀላልም ውስብስብም ነው::

ቀላል ነው የምልበት ምክንያት ባለፉት 20 ዓመታት በኢትዮጵያ በተካሄደው የአመጽ ሂደት እንደድርጅት ከሁሉ ባነሰ የተሳተፈ ድርጅት መኢሶን እንደሆነ ለማስቀመጥ የነገሮችን ቅደም ተከተል ማሳየት ብቻ ይበቃል:: መኢሶን የዚህ አመጽ ሂደት ተዋናይ ለመሆን ጊዜውም፣ ፍላጎቱም፣ አቅሙም እንዳልነበረው ማሳየቱ ምንም ችግር የለውም::

ግን ደግሞ ጥያቄው ውስብስብ ነው:: የፖለቲካና የሞራል ተጠያቂነት፣ የፖለቲካና የሞራል ኃላፊነት የለብንም ወይ? ካለብንስ ምን ያህል ነው የኛ ድርሻ? በጊዜው የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ ሕዝብ ትግል ብለን አስተምረናል፣ ቀስቅሰናል:: ሕዝቡ በተቻለ እንዲታጠቅ ሞክረናል:: በተለይ የኢትዮጵያ ገበሬዎች ራሳቸውን ከመከላከል አልፈው መሬታቸውንም እጃቸው እንዲያስገቡ ለማድረግ ሞክረናል:: የኢትዮጵያችን ባህል አመጽ የተሞላበት ባህል እንደሆነ እንገነዘባለን:: የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ታሪክ የአመጽ ታሪክ እንደሆነ እናውቃለን:: ዛሬ ይህንን ባህል ለአንዴም ለዘላለምም ለመስበር እንጀምር ብለን የሰላምና እርቅ ጉባዔ እያልን ሳይ ታች እንሳለን:: ግን ደግሞ እኛም፣ ትውልዳችንም እንዳለ በዚያን ጊዜ ያራመደው የመደቦች ትግል፣ አብዮታዊና ቅዱስ አመጽ፣. . . የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ለዚህ አመጸኛ ህብረተሰብ እንደ እብድ ገላጋይ ዘመናዊ ሾተል ማቀበል ነበር ወይስ ለጊዜው ሁኔታ ተገቢ ምላሽ ነበር? እነዚህ ሁሉ እጅግ ውስብስብ ጥያቄዎች ናቸው:: ይህ ወይም ያ ድርጅት ሳይባል ሁሉም ጊዜ፣ ፋታና አመቺ ዲሞክራሲያዊ ሁኔታ ሲገኝ ሊወያይባቸው የሚገቡ ጥያቄዎች እንጂ መኢሶንንም ሆነ ኢህአፓን ወይም ሌላ ድርጅት በመወንጀል ብቻ የምንሰናበታቸው አይደሉም::

ግን ደግሞ አሁን በመገናኛ ብዙሃን ጭምር መወንጀል ጀምረናልና ቢያንስ በአስተሳሰብ፣ በፖለቲካና በሞራል ኃላፊነት ደረጃ የኛንም፣ የሌሎችንም ድርሻ ለመጭው ሰፊና ትምህርታዊ ውይይት እየተውን ተጨባጩን ሃቅ ለመጠቆም እንገደዳለን::

የኢህአዴግ ውንጀላ መኢሶን በ1969 እና 1970 ዓ.ም የቀይ ሽብር አራማጅ ኃይል ነበር የሚል ነው:: እኔንም በግሌ ወንጀል ከሶኛል:: በ1969 ዓ.ም ስለነበረው ሽብርና ስለመኢሶን ሚና ገዘቅ ብየ እመጣበታለሁ:: ከወዲሁ ግን 1970 ዓ.ም መኢሶን ቀይ ሽብር አራመደ፣ ሰው ጨረሰ የሚውን በሬ ወለደ ታሪክ ማራገፍ ይቻላል:: እኔ አገር ለቅቄ የሄድኩት በሐምሌ ወር 1969 ዓ.ም ነው:: በ1970 ዓ.ም በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተካሄደውን፣ የመኢሶን ጓዶች በገፍ የቀመሱትን አረመኔያዊ ግፍ የተከታተልኩት በውጭ ጋዜጦችና እየተጠናቀሩ ይደርሱኝ በነበሩ የመርዶ ሪፖርቶች አማካኝነት ነበር:: በዚህ ጊዜ ፓሪስ ሆኜ አዲስ አበባ ከድርጅቱ አመራር ጋር ግንኙነት ሳደርግ ለግንኙነት የሚለየሙልን ታጋዮች ተራ በተራ የቀይ ሽብር ለሰባ እየሆኑ በአራት ወር ውስጥ እውጭ ላለነው አገናኝ እየተባሉ አምስት ሰዎች ተፈራርቀዋል:: የሚደርሱት ሪፖርቶች አንዳንዴ በዚህ ሳምንት አዲስ አበባ 20 ጓዶች ተሰውተዋል፣ ጉንደር በዛሬው ዕለት ስድስት ጓዶቻችንን ተረሸኑ፣ ሀረርጌ ይኸንን ያህል ወዛደሮችና የሕዝብ ድርጅት ካድሬዎች የሱማሊ ሠርጎ ገብ ተብለው ተረሽነዋል፣ ዛሬ ዶ/ር ከድር መሀመድና ዶ/ር ዮሃንስ መስፍን ከታሰሩበት ተወስደው ተረሽነዋል፣ በጥቅምት ወር መጨረሻ ላይ አድር ባይ የቀበሌ መሪዎች ስብሰባ አድርገው «ነጻ ርምጃ» ብለው በሰፊ ግድያ ለማስማራት ውሳኔ ተወስዷል፣ ብርሃኑ ገመዳ እጅን ለደርግ አልሰጥም ብሉ ራሱን ሰዋ፣ እነ ዶ/ር ተፈራ ወልደጻድቅና ባለቤቱ አጥናፍ ከሌሎች አስራ አንድ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ጋር አምቦ አጠገብ ተይዘው እጅ ከሰጡ በኋላ እዛው የተያዙበት ቦታ ከትላንት ወዲያ ተረሽነዋል፣ ከኢህአፓም ከመኢሶንም፣ ከየትም የሌለበት ወጣት ጭምር በገፍ እየረገፈ ነው. . . የሚል ነበር:: በነዚያ አስከፊ ወራት እያንዳንዱን ሪፖርትም ሆነ ቴሌግራም ስከፍት እየሰቀጠጠኝ፣ ሳነብ እንባ እየተናነቀኝ ነበር:: ታዲያ ይህንን ሁሉ ሕይወት የኖርኩ ሰው መኢሶን በ1970 ሽብር አራመደ፣ ሰው ጨረሰ ሲባል፣ ለመኢሶን ሳይሆን ይህንን የተገላቢጦሽ ታሪክ ሆን ብለው ለሚያራምዱት፣ እያዩ አውቀው የሃቅ እውራን ለሆኑ ኃይሎች አፍርላቸዋለሁ::

ያኔ ደግሞ ይህ እልቂት እንዲቆም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለይ በጊዜው የደርግ ወዳጆች በነበሩ ሀገሮች አካባቢ የተቻለኝን እንድንሰራ ከመኢሶን አመራር በተላለፈኝ መመሪያ መሠረት የተቻለኝን ተሯሩጫለሁ:: በ1970 ዓ.ም እኔ የኢትዮጵያን ምድር የረገጥሁት ቀይ ሽብር ለማራመድ ሳይሆን በሚያዝያ ወር በኩባዎች አማካኝነት ከኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ጋር ለመደራደር ሽብር እንዲቆም ለመሟገት ነበር:: የሰው ነፍስ እንደዚያ በረከሰበትና ከጤፍ በማይቆጠርበት ወቅት ነፍሴን ሸጬ አዲስ አበባ ተመልሼ ነበር:: በዚያን ጊዜ ኩባ፣ የመን፣ ቤሩት ፍልስጤሞች ጋር ላይ እታች እያልኩ ድርድር የሞከርኩት በመኢሶን ለመራር ትእዛዝ ይህ ሽብር የሚቆምበትን ሁኔታ ለመፍጠር ነበር::

የ1970 ዓ.ም ጉዳይ ቀላል ነው ያልኩት ትክክለኛ አእምሮ ላለው ሰው፣

ሐቁን ልመልከት ካለ እንደዚህ ግልጽ በመሆናቸው ነው፡፡ ውስብስብነቱም እንደዚያው ነው፡፡ በዚያ አሳዛኝና አስከፊ ሁኔታ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ ወጥተው እንደነበረና ሀገሪቱ አስቸጋሪ የአመጽ አዙሪት ውስጥ ገብታ እንደነበረ ግልጽ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር ያገዙትና አስተዋጽኦ ያደረጉት የመኢሶን የፖለቲካ፣ የአስተሳሰብ፣ የድርጅታዊ አሠራር ስህተቶች ምንድን ናቸው? የኢህአፓስ? የህወሃትስ? በጠቅላላው የዚያ ታጋይ ትውልድ ምን ምን ስሁተቶች ናቸው ያንኑ ትውልድ እንደዚህ ለመከራ የዳረጉት? እነዚህ ሁሉ ረዥምና ትምህርታዊ ውይይት የሚጠይቁ ጉዳዮች እንጂ. ነገሮችን በዚ.ህ ወይም በዚያ ድርጅት ላይ በመለጠፍና የፖለቲካ ንግድ በማካሄድ የምንገላገላቸውና የምንስነባበታቸው ጥያቄዎች አይደሉም፡፡

መኢ.ሶን በበኩሉ ያቅሙን ትምህርት ቀስሟል፡፡ ፋታ ወስዶ የመወያየት ያህል ነገሮችን ከቁጥጥር ውጭ እንዳይወጡ የሚያስችል መፍትሄ የለም የሚል ቀላል ትምህርት ቀስሟል፡፡ ከዚ.ህ ቀደም እንደገለጽሁት ከቅንጅቱ አመራር ጋር እነ አበራ የማነአብ የሰላምና እርቅ ጉባዔ አያሱ የታገሉትና ከፓሪስ እስከ አዲ.ስ አበባ ያደረገነው ጉዞ የኛም የኢህአፓም ታጋዮች ካለፈው ትግላችን ያገኘነው ግንዛቤ ውጤት ነው፡፡

እንግዲህ መኢሶን በቀይ ሽብር ከሚከሰስባቸው ሁለት ዓመታት አንዱን ከነመከራው፣ ከነግፉ፣ ከነእንባው፣ ገና ለሀገርና ላሕዝብ ደህንነት ሲባል ከሚጠይቀው ትምህርታዊ ብሔራዊ ውይይት ጋር ለጊዜው እዚሁ ላይ ልንተወው እንችላለን፡፡ በደፈናው ሳይሆን በዚ.ህ ወቅት መኢሶን በዚህ በዚህ ተጨባጭ ወንጀል ይከሰሳል የሚሉ ከሆነ ሦስት ዓመት ሙሉ የደርግንም የመኢሶንንም ፋይል በቁጥጥራቸው ሥር አድርገው ሲመረምሩ የቆዩት ኢህአዶጉች እስቲ ያገኙትን መረጃ ያውጡ፡፡

የ1969 ዓመትም ቢ.ሆን ከነተጨባጭ ቀኖቹ፣ ከነተጨባጭ ሃቆቹ፣ ከነውስብስብ የፖለቲካ ሂደቱ የሚመረመር እንጂ እንደዚሁ «መኢሶን ቀይ ሽብር አራመደ» በሚል አሉባልታ የምንሰናበተው አይደለም፡፡ ያ ዓመት እጅግ ውስብስብና በተከታዮቹ ዓመታት ለኢትዮጵያ የወደፊት እድል ወሳኝ የሆነ ዓመት ነበር፡፡ በገጠር ቀደም ሲል ተፈጥሮ የነበረው የዘማቾችና የአርሶ አደሩ ህብረት አሁን ደግሞ ከአባላቱ 70 ከመቶ በላይ የቀድሞ ዘማቾችን ባሰማራው የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ታጋዮችና በገበሬው ህብረት ተተክቶ አብዮቱ ከሚጠይቀው መስዋዕትነት፣ ከሚያስከትለው ውጣ ውረድ ጋር ወደፊት እየገሰገሰ ነበር፡፡ ገበሬዎች መሬታቸውንም ነጻነታቸውንም ያው ዘማቾችን ሲያስቸግሩ ከነበሩት ከደርግና ከቢሮክራሲው አባላት፣ ከየክፍለ ሀገሩ ፖሊስ፣ ከአጥቢያ ዳኞችና ምስለኔዎች፣ ከታጠቀ ባለመሬት ጋር እየተናነቁ የነበሩበት ወቅት ነበር፡፡

በከተማ ያለው ሁኔታ ይበልጥ አስቸጋሪና ውስብስብ ነበር፡፡ ኰሎኔል መንግሥቱ መኢሶንን ከቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ ያደረጉት ሙከራ ሁሉ አልሳካ ·ብሏቸው የራሳቸውን ድርጅት «ሰደድ» ብለው በግንቦት ወር 1968 አቋቋሙ፡፡ በዚያ ወቅት እነሙቶ አለቃ ዓለማየሁና ሻምበል ሞገስ ሰደድን አብረው ከመሰረቱ በኋላ ከኰሎኔሉ ጋር ቅራኔ ውስጥ ገብተው ሙቶ አለቃ ዓለማየሁ የኰሎኔሉ «ደንቆሮ አሽከሮች» በሚሏቸው እየተተኩ ድርጅቱን ለቀው ሄደዋል፡፡ ኰሎኔሉንና ሰደድን ለመዋጋት ድርጅታዊ መሠረት ለማግኘት ከኢህአፓ ጋር ተቀራርበዋል፡፡ በኋላ እንደሰማሁት በዚሁ በ1968 ዓ.ም በነሐሴ ወር ዓለማየሁ የኢህአፓ አባል ሆኖ ነበር ይባላል፡፡ ኰሎኔል ይኸን ሲጠረጥሩ እነዓለማየሁን ህገ ወጥ ለማድረግ ኢ.ህአፓን በመንግሥት ደረጃ ለማውገዝ ይነሳሉ፡፡ ከኢህአፓ ገጥሟል ብለው የገመቱትን ሁሉ ጸረ መንግሥት ብለው በመወንጀልና በማስወንጀል ለመምታት እንዲያመቻቸው ነው፡፡ በዚህን ጊዜ እኛ እዛው እስራቸው ቁጭ ብለን ሰዎቹ ትንሽ ተቀያይመዋል ከማለት አልፈን የሞት ሽረት ትግል ውስጥ እንደገቡ ልብ አላልንም፡፡ በኋላ ነው የሚገባን፡፡

እንግዲህ የነሱ የሞት ሽረት ትግል በዚህ አኳኋን ውስጥ ውስጡን ተጀምሯል፡፡ እኛስ? መኢሶን በገጠር በአጠቃላይ መተከሉና በየጊው በየቦታው በሚፈጠሩት ግጭቶች ልክ እንደዘማቾች የገበሬው ወገን እየሆነ «አስቸግሯል» በማለት ቢሮክራሲው ይጠላዋል፡፡ ኰሎኔሉ ነጻ ድርጅት መሆኑን አልወደዱትም፡፡ ግን ደግሞ ገጠሩን እየያዘ ነውና ምናልባት አንድ ቀን አዲስ አበባ በኩዴታ ብገለበጥ የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ያስፈልገኛል ብለው ያምናሉ፡፡ ይህንን ጉዳይ ከኔ ከራሴ ጋር ብዙ ተወያይተዋል፡፡ «ችግር ቢፈጠር አዲስ አበባ የእናንተ ታጋዮች ገበሬውን የያዙትን ያህል ተዋግተው ሊያዋጉ የሚችሉ ናቸው ወይ? ይህ ነበር የጥያቄዎቻቸው ተደጋጋሚ ይዘት፣ ደርግ ቡና ቤት አብረን ስናመሽ፡፡ ይህ ደግሞ ትክክለኛና ከኃላፊነት የመነጨ ውይይት ነበር፡፡ አዲስ አበባ ሁኔታው ጨርሶ አያስኬማምንም፡፡ የኛ የመኢሶኖች ኃይል ደግሞ በርግጥም ገጠር ነበር፡፡

መኢሶን ከኰሎኔሉ ነጻ የሆነ ድርጅት ቢሆንም እነዓለማየሁ እሳቸውን መልምለን የጨረስን አድርገው ገምተዋል፡፡ እርግጠኛም ነበሩ፡፡ ስለሆነም ቀስ በቀስ ከኰሎኔሉ ጋር ያላቸው ትግል ከኛም ጋር እየመሰላቸው እነሱ ደግሞ በበኩላቸው ኢ.ህአፓን የመያዙን ጥረት ገፉበት፡፡ በዚህ ላይ ዶ/ር ሰናይ ልኬና «ወዝ» አሉ፡፡ ዶክተር ሠናይ ቀደም ሲል ጀምሮ «ወደ ሶሻሊዝም በወታደራዊ ጉዳና» ብሎ የሚያምን ሰው ነበር፡፡ ሠራዊቱም ውስጥ በግልጽና በገፍ ይመለምል ነበር፡፡ እሱም የመኢሶን ነገር አስግቶታል፡፡ ያኔ በተለይ ወጣቱ የሚያውቀው «ሁለት መስመር» ብቻ ነው፡፡ ወዝ እምብዛም አይታወቅም ነበር፡፡ በተለይ ደግሞ ከ1968 ዓ.ም አጋማሽ ጀምሮ በጋዜጦች የተካሄደው ክርክር ለመኢሶን እጅግ እንደጠቀመ ይታያል፡፡ ከኢህአፓ ወገን በሌላው መስመር እየተማረከ የሚፈልሰው ወጣት በአዲስ ዘመን ላይ ያን ክርክር ሲያነብ ማን ጻፈው? አይልም፡፡ የመኢ.ሶን ይመስለዋል፣ ሁሉም፡፡ ስለዚህ ከኢህአፓ ሲፈልስ የሚመጣው ወደ መኢሶን እንጂ ወደ ወዝም ወደሰደድም አልነበረም፡፡ «መኢሶን በገጠር አየለ፣ በከተማ አበጠ» ተባለ፡፡ ሰደድም ወዝም የመኢሶንን እድገት ለመግታት ሞከሩ፡፡ ሰደዶች ምንም ቢሆን አንድ የምሁር ክንፍ ስለሚያስፈልጋቸው፣ ወዞች ደግሞ የወታደርም ሆነ የቢሮክራሲ ጡንቻ ያስፈልገናል ብለው ስላመኑ ከሞላ ጎደል በነሐሴ ወር 1969 አካባቢ ወደሰደድ እንዲደባለቁ ስምምነት ተደረሰ፡፡ ድርብ አባልነት እንደያዙ፡፡ እነፍቅረስላሴ ድርብ አባላት ነበሩ፡፡ በኋላ ድሮውንም በስምምነት የወዝም የሰደድም የሆኑት መኰንኖች ከነለገሠ ጋር ሲጣሉ «የወዝ ሰርጉገቦች» ተብለው እየተለቀሙ ተረሸኑ፡፡ ይኸ ግን ቆይቶ ነው፡፡

እንግዲህ 1969 ዓ.ም መግቢያ ላይ መኢሶን በገጠር «ውሃ ውስጥ እንዳለ ዓሣ» ቢሆንም በከተሞች በተለይ በአዲስ አበባ ወዝና ሰደድ እድገቱን በሆነው መንገድ ለመግታት የተነሱበት፣ ኰሎኔሉ ለጊዜው ከነአለማየሁና ከኢህአፓ ጋር ለገጠሙት ትግል፣ ለወደፊቱ ደግሞ ምናልባት አንድ ቀን ሊመጣ ለሚችል የገጠር ትግል ሲሉ የታገሱት ቢሆንም የማይዋጥ የማይተፋ ጉድ ሆነባቸው፡፡ ለነገሩ ግን እነዓለማየሁን ለማስደንገጥ የመኢሶን ምልምል እስከመምሰል የሚሄዱበት ወቅት ነበር፡፡ ይኸ ሁሉ ዛሬ ከነገሮች ራቅ ብዬ ሳስበውና ስተነትነው የሚታይ፣ ጥርት ያለ ነገር እንጂ ያኔማ በየትኛው ፋታ ነገሮችን ማሰላሰል ይቻል ነበር?

የኢህአፓን በአዋጅ በደርግ መጠገዝና ህገወጥ መሆን ምክንያት ምን እንደሆነ ወደፊት በሰፊው የማያውቁ ኅሉ ይጽፉታል:: ገን እዚህ ላይ በኋላ ለተከተለው ችግር ትልቅ ሚና ያለው ስለሆነና በዚያ የተወሳሰቡ ቅራኔዎች ከልል ዓላማ የነበረው ኢህአፓ ብቻ ሳይሆን መኢሶንም እንደነበረ ለማሳየት ትንሽ ማተት ያስፈልጋል:: ኢህአዴጉች የዚህን ውይይት ፋይልና በዚያን ጊዜ የእኛ አቋም ምን እንደሆነ የጊዜውን ታሪክ ገባኙ በመረምሩ ያገኙታል::

ነሐሴ 1968 አጋማሽ ላይ ነው:: ኩሉኔል መንግሥቱ አንድ ቀን ቢሮዬ ደውለው «አሥራ አንድ ሰዓት ላይ ብቻ በል ጥብቅ ጉዳይ አለኝ» አሉኝ:: በተጠሮ ሰዓት ስሄድ እንዲሁ እንደኔው የተጋበዙ ከኛ አባላት ፍትሬ መርዕድንና ተስፋዬ ኃይለን አገኘሁ:: ሁላችንም ለምስጢርና ጥብቅ ስብሰባ ተጠርተን ነው የመጣነው:: ስብሰባው ላይ ሰናይ ልኬ፣ ሙሉ አለታ ግርማ ነዋይ፣ ኩሉኔል ተስፋዬ ወልደሥላሴ ነበሩ:: ኩሉኔሉ ኢህአፓን እየወረፉ ውርጅብኝ ሲደረድሩ ነገሩ አልገባኝም:: ቀስ ብለው ወደ ፍሬ ነገሩ ሲገቡ «ዛሬ እዚህ የሰበሰብኳችሁ ስኢህአፓ ላይ በመንግሥት ደረጃ የማጋለጥ ዘመቻ ስለምንጀምርበት ሁኔታ እንድንወያይ ነበሩ» አሉ:: እኔም ፍትሬም ተስፋዬም ቀደም ብለን ባንመካከርም እንደ አንድ ሰው ተቃወምናቸው:: «መንግሥት እዚህ ውስጥ አይገባበት:: ውይይት በጋዜጣ እየተካሄደ ነው፣ ኢህአፓን ቀስ በቀስ በውይይት መርታት ይቻላል፣ ቀስ በቀስ ወጣቱን ከሱ ማላቀቅ ይቻላል:: መንግሥት ከገባበት ለኢህአፓ ይበልጥ ገዘናና በተለይ በወጣቱ ዘንድ ይበልጥ ተቀባይነት ለማስገኘት ይረዳዋል::» የሚል መከራከሪያ ስናቀርብ ስለመንግሥትና የመደቦች ትግል ሰፊ ገለጣ ተደረገልን:: በተለይ በሰናይና በግርማ:: አስበንበት እንምጣ ብለን ተለያየን::

ወዲያው ወጥቼ ከበደ መንገሻ ዘንድ ሄጀ የሆነውን ሪፖርት አረገሁ:: እብድ ነው ያሆነው:: መጀመሪያ ያለኝ «ሰማ ነገደ፣ ይኸ ጸረ ኢህአፓ ርምጃ አይደለም:: ጸረ መኢሶን ሴራ ነው:: በጋዜጦች ውይይት እነሰናይ ምንም ጥቅም ስላላገኙና በነሱ ሳቢያ መኢሶን በወጣቱ ዘንድ እያየለ ስለመጣ ይህንን ሂደት ለማደናቀፍ ነው:: ለመሆኑ ኢህአፓን እንደዚህ በመንግሥት ደረጃ እናውግዝ፣ ሕገወጥ እናድርግ ሲሉ በሚከተለው የግድያ ዘመቻ ወጣቱ ምን ሊሆን ነው? ትጥቅ ይሰጡታል? ይህንን እብደት መቃወም አለባችሁ» የሚል መመሪያ ነው የሰጠኝ:: እንደገና ተሰበሰብን:: ብዙ ተጨቃጨቅን:: ኩሉኔሉ በድምፅ ብልጫ አሉና ተሸነፍን:: ይህንን ውሳኔ እንደምቃወም ይመዝገብልኝ አልኩ:: ተስፋዬ ኃይለም እንደዚሁ አስመዘገበ:: ከወር ተኩል በኋላ የግድያ ሰለባ ከሆኑት ከመጀመሪያዎቹ አንዱ ፍትሬ መርዕድ ከመብሸቁ የተነሳ እንደኛ ይመዝገብልኝ እንኳ አላለም::

እዚህ ላይ መግባባት ያስፈልጋል:: ኢህአፓና መስዐሩ ለምን ተወገዘ አይደለም ክርክሩ:: «መንግሥት አይግባበት፣ ጉዳቱ ያመዝናል» የሚል ነው:: «አደገኛ ነው:: ሰበብ መስጠት ነው::» የሚል ነበር ክርክራችን::

እንደተፈራው እነንለማየሁ የዚህ ሴራ ዒላማ መሆናቸው ግልጽ ስለነበረ አበዱ:: መጀመሪያ እኛ ላይ:: ወደዚህ ርምጃ ኩሉኔሉን የመራነው እኛ መስለናቸዋል:: በዚያን ጊዜ ከንለማየሁ ጋር እንተራረብ ስለነበረ ከበደ የሆነውን ሁሉ እንዳስረዳ፣ ደጋግሞም ከኢህአፓዎች ጋር ግንኙነት እንደጀመረ ያጫውተኝ ስለነበረ ለነሱም መልእክት እንዳስተላልፍ በሱ በኩል ተላኩኝ:: ገና ስንገናኝ ወረደብኝ:: «በኛው ገንዘብ እንደዚህ አበጣችሁ፣ አሁን ደግሞ በመሃከላችን ገብታችሁ ታበጣብጡን ጀመር! የኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋረዳችኋል፣ ወዘተ::»

ነገሩን ለማብረድና በጥሞና ለመወያየት የሚያስችል ሁኔታ ለመፍጠር የእኩል ሰዓት እድሜም አልወሰደ:: ለኛ የለንበትም ማለት ብቻ አይደለም:: እንዲህ ዓይነቱ ርምጃ ለምን፣ ከፖለቲካ አንጻር ለእኛ እንደማይጠቅመን፣ ለምንስ ይህንን ጉዳይ ለኢህአፓ አመራር ማስተላለፍ እንዳለበት፣ ለምንስ እነሱ እንዲህ ዓይነቱ ተንኰሣ ውስጥ መውደቅ እንደሌለባቸው . . . መልእክት እንዲያስተላልፍ ጠየቅሁት ተስማማ:: ከበደ በሰጠኝ ተልእኮ መሠረት አስፈላጊ ከመሰላቸው ተገናኝተን ልንወያይ ፈቃደኛ መሆናችንን እንዲነግራቸው ጠየቅሁት:: ንለማየሁ እሺ እንዳለው፣ መልእክቱን ያስተላልፍ፣ አያስተላልፍ አላውቅም:: የሆነ ሆኖ አገሪቱን ከብዙ ጥፋት ሊያድን የሚችል የውይይት አጋጣሚ አመለጠን:: ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ ብዙ እንደዚህ ውሳኝ እድሎች እንዳመለጡን ሳስብ አንዳንዴ ለራሴ «ይቺ አገር ያመለጡ የታሪክ አጋጣሚዎች አገር ሆና እስከመቼ?» እያልኩ እጠይቃለሁ:: እነ ኢህአዴግ የፖለቲካ ስልጣን ሽሚያ ይመስላቸዋል ወይም ደግሞ ስለዚች አገር የወደፊት እድል ደንታ ቢስ ሆነው ነው እንጂ አሁንም እንወያይ፣ ይህ የሽግግር ዘመን የሚሰጠን የታሪክ አጋጣሚ እንዳያመልጠን ስንል ከዚህም ከፉ ልምድ ተነስተን እንደሆነ የገባቸው አይመስኝም::

የሆነ ሆና 1969 ዓ.ም በዚህ የፖለቲካ አካባቢ ተጀመረ:: ሽብርን በሚመለከት እኔ ሦስት የተለያዩ ወቅቶችና የተለዋወጡ የፖለቲካ ኃይል ሚዛኖች ይታዩኛል::

የመጀመሪያው ወቅት ከመስከረም አጋማሽ እስከ ኩሉኔል መንግሥቱ መፈንቅለ መንግሥት ማለትም እስከ ጥር መጨረሻ ድረስ ያለው ወቅት ነው:: ይህ ወቅት ራሱ የፖለቲካ ኃይል ሚዛን ተቀያይሮበታል:: እስከ ታህሣሥ 1969 ዓ.ም ድረስ በነመንግሥቱ ቡድንና በነንለማየሁ ቡድን ጨርሶ ያልለየለት የፖለቲካ ትግል፣ ከዚያ በኋላ የደርግን መዋቅር በማሻሻል ስም የኩሉኔል መንግሥቱ መሸነፍና የነንለማየሁ የማየል ወቅት:: ይህ ወቅት ነበር:: ለመኢሶንና ለቀበሌ ተመራጮች ምንም ለውጥ አልነበረውም:: እነዚህ አምስት ወራት ራሳቸውን ለመከላከል ምንም መሣሪያ ስላልነበራቸው፣ እነ ንለማየሁ በደርግ ውስጥ እያየሉ በሄዱ ቁጥር ይበልጥ እየተጠቁ የሄዱበት ወቅት ነው:: መኢሶን በዚህን ወቅት ምንም የታጠቀ ኃይል አልነበረውም:: ተበሊዎችም በነንለማየሁ አሻፈረኝ ባይነት ትጥቅ ተነፍጓቸው፣ የወዛደር መሪዎችም እንዲሁ ባዶ እጃቸውን የሚጠቁበት ወቅት ነበር::

በዚህ ወቅት በኢህአፓ አመራር የመጀመሪያው የግድያ ሙከራ የተደረገው መስከረም 13 ቀን ሐሙስ በኩሉኔል መንግሥቱ ላይ ነበር:: ይህ ሳይሳካ ከቀረ በኋላ ነው የግድያው ዘመቻ በተለይ በወጣቶች፣ በቀበሌ ተመራጮችና በሕዝብ ድርጅት ካድሬዎች ላይ ማተኩር የጀመረው:: የመጀመሪያው ግድያ እሁድ [illegible]ከረም 16 ቀን አንድ የመኢሶን ወጣቶች የጥናት ቡድን ስብሰባ ላይ እንዳለ በድንገት የኢህአፓ ወጣቶች ደርሰው በውይይት ላይ ባሉት ስድስት ልጆች ላይ ተኩስ ሲከፍቱ ከስድስቱ ልጆች ሦስቱ ወዲያው ሲሞቱ የተካሄደ

ነው:: ከዚህ በኋላ መስከረም 21 ቀን ፍቅሬ መርእድ ይገደላል:: ከዚያ ምንም ማቆሚያ አልነበረውም:: በአዲስ አበባም በከፍለ --- ሀገር ከተሞችም፣ በየትምህርት ቤቶችም፣ በየቀበሌው፣ በየፋብሪካው፣ በየመንገዱ ያልታጠቁ ታጋዮች መርገፍ ይጀምራሉ:: ይህንን ግድያ አስመልክቶ የኢህአፓ አመራር ያወጣው ዲሞክራሲያ እስካሁን ይገርመኛል:: በሦስተኛው ዓለም አገሮች አብዮት ማራመድ የሚቻለው በገጠር የትጥቅ ትግል ቢሆንም በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ የከተማ የትጥቅ ትግል አስፈላጊ መሆኑን ብቻ ሳይሆን የሚቻል ነው ብለን ጀምረነዋል የሚል መግለጫ ነው:: ግን የጦሩ ትግል ምኑ ላይ እንደሆነ እስካሁን አይገባኝም:: ከደርግ አባላት፣ ከታጠቀው ሠራዊትና ፖሊስ ጋር ሳይሆን ግድያው የሚካሄደው ባልታጠቁ ታጋዮች ላይ ነበርና:: መኢሶን አባላቱንና ደጋፊዎቹን ለመጠበቅ እስከ ጥር መጨረሻ ድረስ ምንም አጸፋ ርምጃ አልወሰደም:: ለምን?

ዋናውና የመጀመሪያው ምክንያት በተለይ ያ ሁላችንም እንደ ታላቅ ወንድማችንና ብዙ ለጋ ታጋዮቻችን «ጋሼ» እያሉ የሚጠሩት መሪያችን ዶክተር ከበደ መንገሻ በዚህ ጉዳይ የወሰደው የፖለቲካ አቋም ነበር:: ሁለት አስተያየቶች ነበሩ:: በአንድ በኩል ስሜታዊ የሆነና (እኔም ራሴም ይኸው የነበረ) «ሰዎቹን እናውቃቸዋለን:: ለምንድን ነው እኛስ የ20 የ30 ሰው ኮማንዶ አቋቁመን ራሳችንን የማንከላከለው? ታጋይ ቢሞት ትግል አይሞትም እያልን እስከመቼ?» የሚለው አቋም ሲሆን «ትግሉ እስከዚህ ድረስ በኢህአፓ መሀከል አይደለም:: ኢህአፓዎች ርግጥ የራሳቸው ዓላማ ይኖራቸዋል:: ግን ለዚህ የግድያ ሂደት ከጀርባቸው ሆና አንዳንዴ፣ እንዲያውም በነሱ ስም በራሱ ኃይል የሚንቀሳቀስና በግድያ የተሰማራ የፖሊሱ፣ የሕዝብ ደህንነቱ፣ የቢሮክራሲው ስውር ኃይል አለ:: በዛሬው ወቅት ይህንን የማይናቅ ስውር ኃይል አስተባብሮ አመራር መስጠት የሚፈልግና የቻለ በየዕለቱ በደርግ ውስጥ እየተጠናከረ የመጣ የነዓለማየሁ/ሞገስ ክሊክ አለ:: በገጠር ከገበሬው ጐን ቆመን ይህንን ግንባር ድል አርገነዋል:: በከተማ ብቻችንን እንግጠመው፣ እዚህም እዚያም አንዳንድ ኮማንዶዎች አቋቁመን የኢህአፓን መሪዎች በማደን እንሰማራ ማለት «ስዊሳይዳል» ነው:: አንደኛ ነገር አንችላቸውም:: ሁለተኛ ነገር ዋናውን ባለጉዳይ የከተማውን ሕዝብ ተመልካች ብቻ ማድረግ ነው:: ስለሆነም የኛ ዋናው ትግል በሁለት የተያያዙ ጥያቄዎች ዙሪያ ማለትም በዲሞክራሲና በትጥቅ ጥያቄ መሆን አለበት እንጂ በግለሰብ ግድያ መሰማራት ትልቅ ስህተት ነው» የሚል ክርክር ነበር:: ለዚህ ነው በዚያን ጊዜ ባለን በሌለን ኃይል የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች በየፋብሪካውና በየቀበሌው እንዲቋቋሙና እንዲታጠቁ የታገልነው::

ሁለተኛው ምክንያት በዚያን ጊዜ እንኳን ይህንን ከባድ ስውር ኃይል ቀርቶ ኢህአፓ ብቻውንም ቢገጥመን እሱን የምንቋቋምበት አቅሙም አልነበረንም:: መሣሪያ የለንም:: ከስንት ጭቅጭቅ በኋላ ከሐምሌ/ነሐሴ 1968 ጀምሮ የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ዋና ዋና መሪዎች ለራሳችን መከላከያ መሣሪያ ተሰጥቶናል:: ጥቅምትና ኅዳር ላይ በጣም ለተጋለጡ አንዳንድ የሕዝብ ድርጅት ካድሬዎች ፊሉሸር መሳይ ሽጉጥ ተሰጥቷል:: ሌላው በየቀበሌው፣ በየፋብሪካው፣ በየት/ቤቱ ያለው ታጋይ ባዶ እጁን ነው:: የዚያን ጊዜ ትዝ ይለኛል፣ ባይሆን ኢህአፓዎችን በፕሮፓጋንዳ እናስደንግጥ ተብሎ በሌላ ነገር ዝም ብለን «ባንዳዎች ከእግር እስከራሳቸው እየታጠቁ ነው» ብለን ወሬው በሰፊው እንዲናፈስ ስናደርግ::

የሆነ ሆኖ የዚያን ጊዜ በተደጋጋሚ የአዲስ አበባ ህዝብ በመቶ ሺህ እየተቆጠረ ሰልፍ ሲወጣ ይይዛቸው የነበሩት መፈክሮች የዚህ ችግርና የዚህ የመኢሶን የፖለቲካ አቋም ነጸብራቆች ነበሩ:: «አስታጥቁን አስታስጨርሱን፣ ልምጫችን አስጠቃችን!» ወደኋላ ላይ ደግሞ ቢቸገረን «ወይ አስታጥቁን፣ ወይ ትጥቅ አስፈቷቸው» ወደሚለው ጥያቄ ዞረን ነበር:: «አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ይሸጋገር» የሚለውም የጊዜው የሰልፎች መፈክር የዚህ የተከላካይነታችን ውጤት ነበር::

በዚያን ጊዜ የነበረው የፖለቲካ ሁኔታና በተለይ በደርግ ውስጥ በአንድ በኩል በኰሎኔል መንግሥቱ በሌላ በኩል ደግሞ በነዓለማየሁና ሞገስ ቡድን ይካሄድ የነበረው ፍልሚያ ይህንን የግድያ ሂደት የሚያግዝ እንጂ የሚያበርድ አልነበረም:: የኢህአፓ አመራር በዚህ ዘመቻው የፈለገውን ዓላማ ሊይዝ ይችላል:: ግን እኛ በዚያን ጊዜ የታየን እነዓለማየሁ የሚያንቀሳቅሱት ስውር ኃይል በግድያው መቀጠል የፖለቲካ ጥቅም ነበረው:: በመሆኑም በአንድ በኩል የመኢሶን ታጋዮችም ሆኑ ቀበሌዎች የሚጠይቁትን ትጥቅ እንዳያገኙ እያከላከለ በኢህአፓ አመራርም ሆነ በእሱ ስም የሚካሄደው የግድያ ዘመቻ እንዲቀጥልና እንዲፋፋም ይሠራ ነበር::

ከላይ እንዳልኩት እነዓለማየሁ ሰደድን ለቀው ከወጡ በኋላ ኰሎኔሉ መኢሶንን ከያዙ ~~እና ደግሞ ኢህአፓን~~ እንጠጋ ብለው ወስነዋል:: ኰሎኔሉ ተሽቀዳድመው ኢህአፓን ህገወጥ ድርጅት አደረጉባቸው:: ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የነሱ ጸረ መንግሥቱ ትግል የሚንጸባረቀው የያዙት ከሚመስላቸው ከኢህአፓ ጋር ደርግ ተደራድሮ እነሱ የዚህ ኃይል መሪዎች ሆነው ኰሎኔሉን፣ ሰደድን፣ መኢሶንንና ይኸው ድርጅት የሚመራቸውን ቀበሌዎችንና የወዛደር የሞያ ማኅበራትን በሌላ ሰፊ መሠረት ባለው ኃይል ለመቋቋም ነበር:: ለዚህ ደግሞ ኢህአፓ ታላቅ ድርጅት ነው:: ያም ሆና በሁለት የምሁራን ቡድኖች የስልጣን ሽሚያ ትግል ሀገሪቱን ወደአላስፈላጊ ትርምስ መጨመሪያቸውን ለማጠናከር እንደነበረ ያኔም ለኛ ግልጽ ነበር::

የኢህአፓ አመራር እነ ዓለማየሁን ወደራሱ ያድርግ እነሱ ይቅረቡት በእውነቱ መናገር ያስቸግረኛል:: በጊዜው የምናውቃቸው የኢህአፓ መሪዎች እነዶክተር ተስፋየ ደበሳይ፣ እነክፍሉ ታደሰ፣ እነብርሃነ መስቀል ረዳ በተዘዋዋሪ በዓለማየሁ በኩል ልናስተላልፍላቸው እንሞክረው የነበረው መልእክት ይድረሳቸው አይድረሳቸው በርግጥ ለመናገር አልችልም:: ምናልባት ክፍሉ ታደሰ በህይወት አለና እሱ ይኸንን ምስጢር ሊያብራራልን ይችላል:: ግን አንድ መናገር የምችለው ነገር ቢኖር ዓለማየሁ በራሱ እምነትና ስሌት ይሁን በሌሎች ጸረ መኢሶን ኃይሎች ገፊት እኛን ጨርሶ የማጥፋት አዝማሚያ ማሳየት እስከጀመረበት እስከ ጥር ወር 1969 አጋማሽ ድረስ ከበደ ገፋበት እያለኝ ተከታታይ ግንኙነት ነበረኝ:: በይፋ በደርግ ቡና ቤትና በኔም በሱም ቢሮ:: ብዙውን ጊዜ ግን በሱ መኪና ከአዲስ አበባ በኵተቤም፣ በገፈርሳም በኩል ወጣ እያልን እንወያይ ነበር::

በእነዚህ ውይይቶች እሱ ደጋግሞ የሚለው «ከኢህአፓ ገራ ክንፍ ጋር ግንኙነት አለኝ:: ከነሱ ጋር እኛም እናንተም መሥራት እንችላለን:: ኢሕአፓዎች አንድ ግለሰብ/ ማለትም ኰሎኔሉን/ ስለተቃወሙ ዓይናችሁን ላፈር መባል የለባቸውም::» የሚል አነጋገር ነበር:: በኛ በኩል ደግሞ ኢህአፓን በማግለል ምንም ጥቅም የለንም:: ሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ሲቋቋም እነሱም እንዲገቡበት እንጂ ብቻችንን ለመያዝ ምንም እቅድ እንዳልነበረን፣ አሁንም በኛ በኩል ከነሱ ጋር ለመደራደር ምንም ችግር እንደሌለብን፣ ግን በቅድሚያ የግድያ ዘመቻቸውን ማቆም እንዳለባቸው፣ ይህም አቋማችን ለአመራሩ እንዲነገር የኛ አመራር

ፈታደኛ እንደሆነ አብራራለት ነበር። ልድገሙውና ይህ አቋማችን ለኢህአፓ አመራር ደርሶት በንቀት ችላ ይበለው ወይስ ባለማየሁ ሆነ ብሎ ለነሱ ከማስተላለፍ ይቆጠብ አላውትም።

የነበረ አቋም እንደሆነ ግን ለመጠቆም አንዲት አጋጣሚ መጥቀስ እችላለሁ፣ የደርግ አባላት ሁሉ ያውቁታልና። በኀዳር/ታህሣሥ ወር እነ ገለማየሁ የደርግን መዋቅርና ፖሊሲ በማሻሻል ስም የኩለኔል መንግሥቱን ስልጣን ለመቀነስ በጣም ይታገሉ ነበር። ከፍ ብየ እንዳልኩት በደርግ ስብሰባዎች እየደጋገሙ የሚያነሱት ነጥብ ከኢህአፓም ጋር አብረን እንስራ የሚል ኩለኔል መንግሥቱና ደጋፊዎቻቸው የሚታወሙት ነጥብ ነበር። በአንዱ ስብሰባ ላይ ኩለኔል መንግሥቱን «ይህንን በጋራ የመሥራት አቋም የምትታወመው አንተ ብቻ እኮ ነህ። እነነገደ ጋር ተነጋገረን እነሱ እንኳን ከኢህአፓ ጋር አብረን መሥራት እንችላለን ብለዋል» ብሎ እንደተናገረ አውቃለሁ። ወዲያው ከስብሰባ እንደወጡ ኩለኔል መንግሥቱ ኃይሌን ቢሮአቸው ጠርተው «ነገደ ከነገለማየሁ ጋር ይሠራል ወይ? መጠቀሚያ እያደረገው ነው። ዛሬ በስብሰባ ላይ በእናንተም ተጠቅሞ ሊከራከረን ሞከሯል» ብለውታል።

የሆነው ሆኖ በታህሳስ ወር ኩለኔል መንግሥቱ በደርግ ውስጥ በድምጽ ብልጫ ተሸንፈው እነገለማየሁ ሥልጣን ያዙ። እንዳልኩት ገለማየሁ አምናበት ይሁን ሌሎች አይለውበት ባላውቅም የኛን አቋም እያወቀ በመኢሶን፣ በሕዘብ ድርጅት፣ በቀበሌና በፋብሪካዎች ላይ የተያዘው ዘመቻ እያየለ መጣ። የተከተለው ጥር ወር በተለይ ለኛ ወጣቶች እጅግ አስከፊ ወር ነበር። የመኢሶን አመራር ወይ ተደራድሮ የግድያውን ዘመቻ አላቆመላቸው፣ ወይ ደግሞ ራሳቸውን የሚከላከሉበት መሣሪያ አላስታጠቃቸው። በዚህ ላይ ደርግ በጸረ መኢሶን ኃይሎች ቁጥጥር ስር ወደቀ። ሕዝብ ድርጅትም፣ ቀበሌዎችም፣ ወዛደሮችም በጸረ ደርግ አቋም ተሰለፉ። ይህ ሰፈር በኢህአፓና በነገለማየሁ ላይ ያለው ጥላቻ ሰማይ ነካ። ሁኔታውን ለድርድር ለማመቻቸት እነገለማየሁ ቢያንስ የግድያውን ዘመቻ ጋብ እንዲያደርጉ መሞከር ሲችሉ ይባስ ብለው እንዲፋፋም አደረጉ። በዚህ ሁኔታ እኛም ደጋፊዎቻችንም ከኢህአፓ ጋር የመደራደር ሃሳብ ጨርሶ ሊኖረን አልቻለም። ትጥቅና ዲሞክራሲን አፍነው ግድያውን በሚያግዙት በነገለማየሁና በደርግ ላይ ተቃውሟችው ተጠናከረ። ይህ ደግሞ ተሸንፈው ተስፋ ቆርጠው ለነበሩት ኩለኔል መንግሥቱ ረዳ። ጥር 22 ቀን በተደረገው ግማሽ ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ የተገኘበት ሰልፍ ላይ ሕዝቡ «አስታጥቁን!» ከሚለው ጩኸት ሌላ መፈክርም አልነበረውም። በዚህ ሁኔታ ጄኔራል ተፈሪ በንቲ ከኢህአፓ ጋር ደርግ መቀራረቡን የሚጠቁም ንግግር ሲያደርጉና በእውነቱ ከልባቸው «ልጆቼ ለዚች አገር ስትሉ ተባበሩ» በሚል መንፈስ ያደረጉትን ንግግር ሰው እስከመጨረሻውም አላዳመጠላቸው። ገና ሳይጨርሱ አደባባዩን እየለቀቀ መውጣት ጀመረ።

በዚያን ሰሞን በነበረው ሁኔታ ከነገለማየሁና ከደርግ ጋር ብሎም ከኢህአፓ ጋር የመቀራረብ ፖለቲካ መከተል ይቻል አይቻል እንደነበረ በእውነቱ አሁንም መናገር ያችተኛል። ግን ደግሞ አንድ የምገነዘበው ነገር አለ። ይህ ደግሞ አንድ ያመለጠ የታሪክ አጋጣሚ እንደሆነ ይሰማኛል። እስካሁን የምንከራከርበት ነጥብ ነው። እንዳንዶቻችን ያን ጊዜ በደፋ ለኢህአፓ የድርድር ጥሪ ማድረግ፣ የጄኔራሉን ጥሪ በደፋ ተቀብሎ መንቀሳቀስ ይቻል ነበር እንላለን። ሌሎቻችን ይህንን ጥሪ ያኔ ብናስተላልፍ ኢህአፓ ሆነ እነ ገለማየሁ የድካም ምልክት አድርገው ከመቁጠርና ንቆ ችላ ከማለት አይመለሱም የሚል ነበር። ዞሮ ዞሮ በኛ ወገን የተሰለፈው ኃይል አይገባውም ነበር። ከሁሉም በላይ ደግሞ በጥር 22ቱ ሰልፍ በነገለማየሁ ላይ የነበረውን ጥላቻ በማየት ምራላቸው እጅግ ከፍ ያለው ኩለኔል መንግሥቱ እናለማየሁን ተሸቀዳድሙው ከመገልበጥ አይታገዱም ነበር እንላለን። ይህ ክርክር የተከሰተው ግን በኋላ ነው። ያኔ ያሰበውም የለ።

ለማንኛውም ከዚያ በኋላ የመኢሶን አመራር አንድ የተገነዘበው ጉዳይ ቢኖር ይህንን የግድያ ዘመቻ ከማቆም አንጻር ከደርግ ምንም ነገር መጠበቅ እንደማይቻል ነው። የጄኔራል ተፈሪ በንቲ ንግግር እንኳን ዝም ብሎ ታሪክ ከማለት ይልቅ በደፋ ኢህአፓ የግድያ ዘመቻውን በማውገዝ እንዲያቆም በጠይቅ ኖሮ ምናልባት ትንሽ ተስፋ ያለው ሁኔታ ይኖር ነበር። ግን ይህንን አላሉም። ሁኔታዎች ግልጽ ከሆኑ በኋላ መኢሶን ባለችው አቅም ቢያንስ በኃይል የተጋለጡትን አባላቱን ለመከላከል ውሳኔ አደረገ። መሣሪያ በተቻለ ማስታጠቅ። ግን ደግሞ ያን ሁሉ የተጋለጠ ታጋይ ለማስታጠቅ አቅሙ የለም። በመኪና የምንሄደውና ከሁሉም በላይ ደግሞ አልታጠቁም ተብለን የማንጠረጠረው ሰዎች ያለንን ሻል ያለ መሣሪያ እንድንፈታና በርግጥ አደጋ ላይ ያሉት ወጣቶች እንዲታጠቁ ከመወሰን ሌላ አማራጭ አለነበረንም። ዘግናኝ ወር የተደረገውም ይኸው ነው።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጥር 25 ቀን ተካሄደ የተባለው «እልቂት» የተፈጸመው በዚህ የፖለቲካ ሁኔታ ነበር። ነገደ ጉበዜ የመኢሶን ኩማንደ እየመራ ተማሪዎች የተሰበሰቡበት አዳራሽ በድንገት ደርሶ ሰው ፈጀ የተባለበት ተረት ነው። ተረት የምለው ሆን ብየ ነው። የዚያን ለት እኔ በቦታውም አልነበርኩም። እኔ ሪፖርቱን ባላይም በኋላ እስከሰማሁት «አለቀ» የተባለው ፈጠራ ነው። አንድም ተማሪ የሞተ አልነበረም። የቆሰለው አራት ተማሪ ነው። የዚያን ለት የሞተ ተማሪ አለ ከተባለ ለመታረም ዝግጁ ነኝ። ከሁሉም በላይ ደግሞ እዛ የነበረ ሁሉ እንደሚያስታውሰው ተኩሱ መጀመሪያ ረድፍ ተቀምጠው በነበሩ በኛው ልጆች ተጀመረ እንጂ ባቢሊ ቶላ የተባለ «ቱ ኪል ኤ ጄኔሬሽን» የተባለውን ተረት የጻፈ ሰው እንዳለው ከውጭ በድንገት ደርሶ ተኩስ የከፈተ ኩማንዶ አልነበረም። ለዚያውም እንግዲህ በዚህ ቀን የመኢሶን አመራር ይህ ርምጃ እንዲወሰድ ሰጠስን ግልጽ የሆነ የፖለቲካ መልእክት ለነገለማየሁም ለኢህአፓዎችም ለማስተላለፍ እንጂ «ሰው ለመጨረስ» አልነበረም።

ተኩሱ ቢያንስ አስር ደቂቃ ያህል ቆይቷል። አራት ሰው ሲቆስል ሰው ያላለቀበት ምክንያት ግልጽ ነው። የተሰጠው መመሪያ ወደሰማይ ብቻ እንዲተኩሱ ነበር። ሰዎች የመቁሰላቸው ምክንያት አንዳንድ የኛ ወጣቶች ከመመሪያ ውጭ በሰው ላይ ተኩሰው ይሆን ወይስ ከኢህአፓዎች በኩል የመጣ ተኩስ ይሁን መናገር ይቸግረኛል። ለኛ ግን ዋናው ነገር በዚያን እለት ያ ሁሉ ተኩስ ተካሂዶ ሰው አለመሞቱ ነው። የዚህ ርምጃ የፖለቲካ መልዕክት ግልጽ ነበር። ለአምስት ወር ያህል መኢሶን ከፍ ብየ በጠቀስኳቸው የአቅምና የፖለቲካ ምክንያቶች የራሱን ኩማንዶ አቋቁሞ በግለሰብ ግድያ አልተሰማራም ነበር። ጥር 25 ቀን ያንን ርምጃ የወሰደው ከእንግዲህ በየትምህርት ቤቱ በዚሁ ሰሞን የተስፋፋው ግድያ ማቆም እንዳለበት፣ ካለቆመ ደግሞ መኢሶን ምንም እንኳን ደርግ ትጥቅ ቢነሳውም፣ ባለው አቅም ከእንግዲህ ራሱን ለመከላከል እንደወሰነ ለሚመለከታቸው ሁሉ ለማስጨበጥ ነበር።

ለማንኛውም በማግሥቱ ጥር 26 ቀን ኩለኔል መንግሥቱ በነገለማየሁ ላይ መፈንቅለ መንግሥት አደረጉ። ይህ ደግሞ ራሱን የቻለ ሌላ ታሪክ ነው። የዚያን ለት የተገለበጡት እነገለማየሁ ብቻ አይደሉም። ደርግም ነው·

ያከተመለት፡፡ ከአንድ ወር በፊት ኰሎኔል መንግሥቱን ከሥልጣን አውርደው፣ ለነገለማየሁ አስረክበው እየተሾሙ በየክፍለ ሀገራት የተሰማሩትን የደርግ አባላት ማየት ነበር ያኔ፡፡ ለመግለጽ ቃል አላገኘለትም፡፡ በልዩ አውሮፕላንም፣ በመኪናም እየተሽቀዳደሙ የእለቱ ዕለትም በማግስቱም እየመጡ እጃቸውን ለኰሎኔሉ ሰጡ፡፡ የሚያሳዝንም፣ የሚያሳርፍም፣ የሚያስቅም ትርዒት ነበር፡፡ የዚያኑ ያህል ደግሞ በመኢሶንና በህዝብ ድርጅት እንዲሁም በህዝባዊ ድርጅቶች ላይ ያላቸው ጥላቻ ሰማይ ነካ ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ደግሞ ለሚመጡት ወራት ሁኔታዎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው ወዲያውኑ መስመር ያለበት ክስተት ነበር፡፡

ይህ መፈንቅለ መንግሥት በ1969 ዓ.ም የሽብር ሂደት ሌላ አጭር ምዕራፍ ከፍቷል፡፡ ሁለተኛው ወቅት መሆኑ ነው፣ የካቲትና መጋቢት 1969 ዓ.ም፡፡ መኢሶንና ቀበሌዎች በዚያን ጊዜ በነበረው አባባል «ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት» የተሸጋገሩባቸው ወራት ናቸው፡፡ ቀደም ሲል መቋቋም የጀመሩትና የፖለቲካ ንቃት ሲሰጣቸው፣ በጠመንጃ ሳይሆን በዱላ ትጥቅ የውትድርና ልምምድ ያደርጉ የነበሩት በየቀበሌውና ፋብሪካው የተቋቋሙት የአብዮት ጥበቃ ኰሚቴዎች ትጥቅ ተሰጣቸው፡፡ ያውም ደግሞ ሁሉም አይደሉም፡፡ እኔ እስከማስታውሰው ድረስ ለምሳሌ አዲስ አበባ ከነበሩት 291 ቀበሌዎች መጀመሪያ ላይ ትጥቅ የተሰጣቸው 44ቱ ብቻ ነበሩ፡፡

ካለፉት አምስት ወራትና ከሚቀጥለው ወቅት በተለይ ደግሞ ከ1970ው አስቃቂ ሁኔታ ጋር ሲነጻጸሩ እነዚህ የመኢሶንና የሱ ደጋፊ የሆኑት የአብዮት ጥበቃ ኰሚቴዎች የአጥቂነት የሁለት ወራት ወቅት ብዙ ደም ፈሰሰባቸው የሚባልላቸው ወራት አይደሉም፡፡ «አብዮታችን ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ይሸጋገር» ስንል ለዚህ መፈክራችን ሰጥተነው የነበረው ትርጉም ራሱ የአብዮት ጥበቃ ኰሚቴ በምሳሌነት ከተወሰደበት ከኩባ አብዮት ሁኔታ ትምህርት ቀስመን ነበር፡፡ በየቀበሌው፣ በየፋብሪካው፣ በየትምህርት ቤቱ ያሉና በግድያ ሊሰማሩ ይችላሉ ተብለው የሚጠረጠሩ ለጊዜው በቁጥጥር ስር ይዋሉ የሚል ጥያቄ ነበር፡፡ በዚህ መሠረት በያለበት የሚጠረጠሩ ሁሉ እየተያዙ ለፖሊስ ተሰጥተዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በተኩስ ልውውጥ ሌላ ጊዜ ደግሞ አላስፈላጊ የሆኑ ግድያዎች በዚህ ወቅት ተፈጽመዋል፡፡ ዋናው ነገር ግን በዚህ ወቅት እነዚህን ወራት በእውነቱ «ደም የጠማቸው ወራቶች» ማለት አይቻልም፡፡

እርግጥ በዚህ ወቅት የገርማ ከበደ በጊዜው ሀገሪቱን እጅግ ያስቆቆ ግፍ ተፈጽሟል፡፡ 9 ሰዎች፣ ከነሱም መሀል አንዲት የስምንት ወር እርጉዝ የነበረች የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሠራተኛ በግፍ ረሽና ሬሳቸውን መንገድ ላይ እንዲጣሉ አድርጓል፡፡ ይህ ሰው የነሰገሠ አስፈሪ ምልምል እንጂ በምንም ዓይነት የመኢሶን አባል ሆኖም አያውቅም፡፡ ተይዞ ሲመረመር በማን ገፊት እንደሆነ ሳላውቅም መጀመሪያ የመኢሶን አባል ነኝ ብሎ ነበር፡፡ ኰሎኔል መንግሥቱ ጠርተው እንዲህ ይላል ብለውኝ ጨርሶ አስተባብዬ እንደነበረ ትዝ ይለኛል፡፡ የሆነ ሆኖ በኋላ ገርማ ከበደ ራሱ ደጋፊ እንጂ አባል አይደለሁም ብሏል፣ በምርመራው ጊዜ፡፡ ግን ይኸ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ነው፣ የመኢሶን አባል መሆን አለመሆኑ፡፡ የፈጸመው ግፍ ወደር የማይገኝለት ነበር፡፡

ሰው እንዴት ልብ እንዳላለው ጨርሶ ሊገባኝ ባይችልም ከዚህ እኮ ማንም የማያመልጠውና በ1969 ዓ.ም የነበረውን ሁኔታ ለመገንዘብ የሚያስችል መደምደሚያ አለ፡፡ ገርማ ከበደ በዚያን ጊዜ የፈጸመው ወንጀል በጊዜው ከነበረው ሁኔታ ጋር ጨርሶ የማይሄድ ወንጀል ነበር፡፡ አስቃቂና የተለየ ድርጊት ነበር፡፡ ለዚህም ነው ወዲያው በሞት ፍርድ የተቀጣው፡፡ በኋላ በ1970 ዓ.ም በሺ የሚቆጠሩ ገርማ ከበደዎች ፈልተው ነበር፣ በደርግና በሰደድ አይዟችሁ እየተባሉ፡፡ መኢሶን የበላይነትን ይዞ በነበረባቸው በየካቲትና መጋቢት 1969 ዓ.ም ግን እንኳን ለሺህ ገርማ ከበደዎች ለሁለትም ቦታ አልነበረም፡፡ የመኢሶን ጠላቶች በኋላ ደግሞ ገርማ ከበደ በመረሸኑ የመኢሶን አመራር ለደርግ ተቃውሞውን አሰምቷል ብለዋል፡፡ ነገሩ በደንብ ስለማውቀው ይህንን ላብራራ እችላለሁ፡፡ ዶክተር ከበደ ልኩኝ ለኰሎኔል መንግሥቱ ተቃውሞና ቅሬታ አሰምቻለሁ፡፡ ግን ይህ ተቃውሞና ቅሬታ የሚመለከተው በገርማ ከበደ ላይ የተወሰደውን ርምጃ ሳይሆን ይህንን እርምጃ አስታኩ በወጣውና በገርማ ከበደ ሳቢያ በጠቅላላው ቀበሌዎችን የደም ጥመኞች አድርጐ ያቀረበውን የደርግ መግለጫ ይዘት ነበር፡፡

የሆነ ሆኖ ይህ የአጥቂነት ዘመን የብዙ እሥራት እንጂ የደም ጉርፍ ዘመን አልነበረም፡፡ የዚህ አጥቂነት አንዱ መልኩ የትጥቅ ማስፈታት ዘመቻ ነበር፡፡ ሁለት አሰሳዎች ተካሂደዋል፡፡ የተካሄዱትም በሥነሥርዓት ነው፡፡ ዶክተር ተሰፋዬ ደበሳይና ከኢህአፓ መሪዎች ማርቆስ ሐጐስ በነዚህ አሰሳዎች ጊዜ ሞተዋል፡፡ ሌሎችም ~~ቀጥተው 3~~ ይሁን ሰባት አላስታውስም፣ የኢህአፓ ወጣቶች ከቀበሌዎችና ከሌሎች በአሰሳው ከተሰማሩ ወታደሮችና የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጽ/ቤት ታጋዮች ጋር ባደረጉት የተኩስ ልውውጥ ህይወታቸው አልፏል፡፡

ይህም ወቅት ብዙ አልቆየም፣ የሁለት ወር እድሜ ነበረው፡፡ ከመጋቢት መጨረሻ ጀምሮ የኛ ሰፈር እንደገና ወደተከላካይነት ገባ፡፡ በሚቀጥሉት ወራት የሚወጡትን የጋዜጣችንን «የሰፊው ህዝብ ድምጽ» ቁጥሮችን ማየት ይበቃል፡፡ በተከተሉት ወራት ስለነበረው የኛ የተከላካይነት ሁኔታ በመብሸቅና በመመረር የህዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትን «የተብር አደራጅ ጽ/ቤት» እያልን መጥራት የጀመርንበት ወቅት ነበር፡፡ መጋቢት መጨረሻ ለኛ ሌላ ምእራፍ የከፈትንበት ወቅት ነበር፡፡ ከደርግ ጋር የነበረን ግንኙነት እንዳለቀ ገምግመን፣ ከየክፍለ ሀገራቱ የድርጅቱ መሪዎች በተገኙበት ምስጢራዊ ብሔራዊ ጉባዔ በመጥራት ህቡዕ ለመግባት ዝግጅት እንዲደረግ የወሰንንበት ጊዜ ነው፡፡

የመኢሶንና የህዝብ ድርጅት እንዲሁም የቀበሌዎችና የወዛደር ኰሚቴዎች ወደተከላከይነት መውረድና የታጋዮቻችን እንደገና ማለት የመጣው የፖለቲካው ሁኔታና የኃይሎች አሰላለፍ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ በመቀየሩ ነበር፡፡ የዚህ ታሪክ ረዥምም ቢሆን ይዘቱ ቀላል ነው፡፡ የአብዮት ጥበቃ ኰሚቴዎች እየተባሉ በቀበሌም፣ በየፋብሪካውም ትጥቅ በመታደል ላይ ያሉት አበዛኞቹ የመኢሶን አባላትና ደጋፊዎች እንደሆኑ ለመረዳት ኰሎኔል መንግሥቱም ሆኑ ሰደዶች ምንም ጊዜ አልወሰደባቸው በገጠርም ሆነ በከተማ ህዝብን በማደራጀት ከሁሉም በላይ የተሰማራው ድርጅት በዚያን ወቅት መኢሶን ነበርና፡፡ መኢሶንን መቆጣጠር ስለማይችሉ የነበራቸው ምርጫ እምብዛም አልነበረም፡፡ በ'ገለማየሁ ወገን የነበረውንና በነሱ መወገድ ትስሙ የተሰበረውን ቢሮክራሲ፣ ፖሊስ፣ የደርግ አባል መወዳጀትና መኢሶን ህዝብ ድርጅትንና ህዝባዊ ድርጅቶችን መዋጋት ነበር፡፡ ከመጋቢት ጀምሮ መታየት የጀመረው ይህ ጸረ መኢሶን ህብረት ነበር፡፡ አብዮታችንንም ይዞ ገደል የገባው ይህ ጸረ አብዮትና ጸረ ዲሞክራሲ ሽርክና ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ እንገለው በነበረው አባባል በዚህ ወቅት «አዲስ የቀኖች አልያንስ» የሚባለው ተጀመረ፡፡ ከዚያስ ምን ሆነ? በሚቀጥለው እትም እናየዋለን፡፡

□

# መኢሶን፣ ሶቭዬቶችና ኢትዮጵያ በ1969

ዶ/ር ነገደ ጐበዜ (ካለፈው የቀጠለ)

ሶቭየቶች ወደ ኢትዮጵያ የገቡት በመጋቢት ወር 1969 አካባቢ እየተጠናከረ የመጣውን ፀረ-አብዮትና ፀረ-ዲሞክራሲ ህብረትና ሴሎችንም የአገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታዎች ጠለላ በማድረግ ነበር። በመሠረቱ የመንግሥቱና የሶቭየቶች መጣመር ጨርሶ ያልተጠበቀ ጉዳይ ነበር።ይህም ረዥም ታሪክ አለው፣ ወደፊት ይወጣል።ባጭሩ ግን መኢሶን የሶቭየቶች አፍቃሪ ድርጅት፣ ከዚያም አልፎ የሶቭየቶች ፍጡር የሚባለው ተረት ነው። ያን ጊዜ መኢሶን ብቻ ሳይሆን አብዮታዊ ትውልድ ከሁሉ የሚቀርበው ወደ ማኦ ፍልስፍናዎችና እምነቶች ነበር። ሶቭዬቶች መኢሶንን የማኦ ተከታይ ስለሚሉት በጥርጣሬ ሳይሆን በጥላቻ የሚመለከቱት ድርጅት ነበር። መንግሥቱ ኃይለማርያምን ደግሞ እንደ መአሶን አባል ስለቆጠሩአቸው በሳቸውም ላይ ጥላቻ ነበራቸው። በሳቸው ሥር የተረጋጋ ሁኔታ እንዳይፈጠር ብዙ ያደረጉት ሸር አለ።ያኔ እኛ ከአሜሪካም ከሶቭየቶችም የራቀ ፖለቲካ እንደግፍ ነበር። ከቻይና ጋር መቀራረብ እንዲኖር ሞክረናል።በ1968 ዓ.ም በክረምት ወራት ኮሎኔል መንግሥቱ ጋር በምስጢር ቻይና ሄደን ከነሱ ለአብዮቱ ድጋፍ ለማስገኘት ሞክረናል።ከዚያ ስንመለስ የሶቭየት አምባሳደር በዚህ ጉዞ ያልተደሰቱ መሆኑን ለመግለጽ ኮሎኔሉ ዘንድ በቀጠሮ ገብተው«ምንድን ነው የምንሰማው? ፔኪንግ በምስጢር ደርሰው መጡ የሚባለው?» የሚል የንቀት ጥያቄ አቀረቡላቸው። ኮሎኔል መንግሥቱ «ብሬዥኔቭ የፈለጉበት አገር ሲሄዱ እኔ ጠርቼ እርስዎን እጠይቃለሁ ወይ?» በሚል አነጋገር ከፍ ገዞ አድርገው ሰድበው እንደመለሷቸው ትዝ ይለኛል።ባጭሩ ሶቭዬቶች ጸረ-መንግሥቱ ነበሩ።በታህሣሥ ወሩ የነዓለማየሁ ሥልጣን መያዝ ጊዜ ምን እንደሚያስቡ ለማወቅ አምባሳደሩ ዘንድ አንድ ሰው ልከን ነበር። «የኮሎኔሉ ከስልጣን መውረድ ለዲሞክራሲ ጥሩ ነው።» የሚል ነበር የአምባሳደሩ ግምገማ።

ጥር 26 በደርግ ውስጥ የነዓለማየሁ አንጃ ሲሸነፍ ከሁሉ መጀመሪያ መንግሥቱ ኃይለማርያምን «እንኳን ደስ ያለዎት» ለማለት ቤተመንግሥት የደረሱት ግን ሶቭዬቶች ነበሩ።እርግጥ ከዚያ ቀደም ብሎ አብዮታችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚገኝበት ብቸኝነት እንዲወጣ መኢሶን ብዙ ጥረት አርጓል። ከኩባዎች፣ ከየመኖች፣ ከፍልስጤሞች ጋር ጥብቅ ግንኙነት ነበረን። ሁሉም በሶቭየት ህብረት ላይ ያለንን ጥርጣሬ ያውቃሉ። ትዝ ይለኛል ከኩባው አምባሳደር ጋር ማለቂያ ባልነበራቸው ውይይቶቻችን መጨረሻ የተውን «እኛም አብዮታችን መጀመሪያ ላይ እንዲህ ነበርን። ወደፊት እየገባችሁ ይሄዳል»በሚል መንፈስ ነበር።

የሆነ ሆኖ በዚህ ጊዜ ውስጥ ቀደም ሲል በነዓለማየሁ ዙሪያ ተሰብስቦ የነበረው ኃይል አሁን ደግሞ በሰደዶች ዙሪያ እየተደራጀ መጣ።በአዲስ ያኔ «የቀኝ ኃይሎች ሽርክና»እያልን መጥራት በጀመርነው ኃይል ውስጥ ግን ኢህአፓ የለበትም። ኢሕአፓም እንደኛው የዚህ ግንባር ኢላማ ነበር። በውጭ ደረጃ ደግሞ ሶቭዬቶች ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ ከኮሎኔል መንግሥቱ ጋር ተሰለፉ። በዚህ ጊዜ መኢሶን መቋቋም የማይችለው ኃይልና ጸረ ዲሞክራሲና ጸረ ብሄራዊ ነፃነት ግንባር በሃገራችን ተተከለ። በዚህ ወቅት ነው ከደርጉች ጋር ብዙ ያጨቃጨቀንን የሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥር 53 ያወጣነው። ፊደል ካስትሮ ኢትዮጵያን ጐብኝተው በተመለሱ በሳምንቱ መጋቢት ወር አጋማሽ ላይ ማለት ነው።

የሰፊው ሕዝብ ድምፅ፣ ቁ..53 አንዳንድ ዲፕሎማሲያዊ አነጋገሮች ይኑርበት እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለአገር ወዳድ ኃይሎች በሙሉ የሚያስተላልፈው መልእክት መጨረሻው ላይ በግልጽ ተቀምጧል ነበር። በውጭ ኃይሎች ላይ ሳይሆን እምነታችን በኢትዮጵያ ሕዝብና በምድራችን ሃብት ላይ ይሁን፣ ከዚህ እምነት መዛነፍና የሃገሪቱን እድል በውጭ ኃይሎች ላይ መተው የመጣ ዕለት አብዮታችንንም እናስቀለብሳለን፣«በነጻነቷ ኩርታ ለዘላለም ትኑር» የተባለላት አገራችንን ወደ አዲስ ባርነት የምንጨምርበት አደጋ ይመጣል» የሚል ነበር። ትዝ ይለኛል በዚህ እትም ሳቢያ ፍቅረ ስላሴ «ሃገሪቱን ያለጠዳጅ ለማስቀረት የተጠነሰሰ ሴራ» በማለት ኃይሌ ፊዳን ቢሮው ጠርቶ ተጨቃጭቀዋል።

ወረቀት በማውጣትም አልተወሰነም። የመኢሶን አመራር ባስተላለፈው መመሪያ መሠረት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሚደረጉ ሕዝባዊ ሰልፎች ሁሉ የብሄራዊ ነፃነታችንን መከበር ያጧጧፉ መፈክሮች ቁልፍ መፈክሮች ነበሩ። በነገራችን ላይ በዚህ ወቅት በውስጥም ሆነ በውጭ ስለተደረገው የኃይሎች አሰላለፍ ለውጥ «መንሸራተት መንሸራተትን እየወለደ» የሚለውን የሰፊው ሕዝብ ድምፅ ቁ.68 እና «መኢሶንና የብሄራዊ ነጻነት ትግል» የሚለውን ቁ.73-74 ማየት ይጠቅማል።



በ1969 ዓ.ም ከሚያዝያ እስከ ነሐሴ የሚሄደው ሶስተኛ ወቅት፣ ብዙ ውዥንብር የነበረበት ወቅት ነበር። ግን አንዳንድ ግልጽ ነገሮች አሉ። በመኢሶን፣ በህዝብ ድርጅት፣ በወዛደሮችና በቀበሌዎች መሪዎች ላይ ጥቃት የተሰነዘረበትና ከመጀመሪያው ወቅት ይልቅ ብዙ ጓዶቻችን የረገፉበት ወቅት ነበር። የዚህ ምክንያቱም ከግንቦት ወር ጀምሮ ግልጽ እየሆነልን መጥቷል።በገድያ የተሰማሩት ኢህአፓዎች ብቻ አልነበሩም።በአዲስ አበባና በክፍለ ሃገራት ሰደድና ወዝ እንዲሁም በነዓለማየሁ በኩል የነበሩት በየክፍለ ሀገራቱ የተመደቡት የደርግ አባላት በኛ ላይ በስውር ተሰማርተዋል። በሰሜን የኢዲዩ ጦር እንደዚሁ የሕዝብ ድርጅት ካድሬዎችን ኢላማ አድርጓል። ሰኔ ላይ ኢዲዩ ሰቲት ሁመራን ሲይዝ በአካባቢው የነበሩ ሁለት የሕዝብ ድርጅት ካድሬዎችን ይዞ«ኮ ካርቱም ሂዱና ደርግን በራዲዮ አውግዙ ቢላቸው እምቢ ብለው እዛው ተረሽነዋል።ወያኔም ቢሆን አልሰነፈልንም። በዚያም ወቅት የሕዝብ ድርጅት ካድሬዎችን ከዛፍ ጋር እያሰረ ረሽኗል።

በጊዜው ይወጡ የነበሩትን የህዝብ ድርጅት መግለጫዎች ማየት ነው። እንደተደመው ወቅት አንድ ታጋይ ሲሞት «በኢህአፓ ነፍሰ ገዳዮች ተገደለ ወይም ተገደለች» ማለትን ትተን «ባልታወቁ ሰዎች»ማለት የጀመርንበት ወቅት ነበር።

በዚህ ወቅት የታየው አዲስ ክስተት የፖሊሱ ሚና ነው፡፡ በጣም ያዋከበን ነበር፡፡ብዙ ታጋዮች በየጊዜው ይታሰራሉ፣ ተሯሩጠን እናስፈታለን፡፡ ግን እስከዚያው ድረስ ባላቸው የ24ትም የ48 ሰዓትም እድሜ እነዚህ የመኢሶን ታጋዮች ሆን ተብለው የሚወረወሩት ብዙ ኢህአፓዎች የታሰሩበት ክፍል ውስጥ ነበር፡፡ነገሩ ተጣርቶ እስኪፈቱ ልባቸው እስኪጠፋ ይደበደባሉ፡፡ ብሄራዊ ሸንጎ አንድ የወዛደርና የቀበሌ መሪዎች ስብሰባ ተደርጎ ስለዚህ ችግር ውይይት ሲደረግ አንዱ ተነስቶ «የታጋዮችን መታሰር መንግሥት መከላከል ቢያቅተው ቢያንስ ቢያንስ የአብዮታውያን መቃብር እንዳለ ሁሉ የተራማጆች እስር ቤት ተለይቶ ይደረግልን፡፡» ብሎ ምርር ብሎ ሲናገር ትዝ ይለኛል፡፡

ሌላው የፖሊሱ ሚና ቀበሌዎችም ወዛደሮችም አንዳንዴ ከነመሳሪያቸው የሚይዟቸውን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በግድያ ተጠርጥረው የሚያዙትን ኢህአፓዎች ለፖሊስ ወስደው ያስረክባሉ፡፡ ፖሊስ ወዲያውኑ ይለቃቸዋል፡፡እንዲያውም በግድያ ተጠርጥረው ለፖሊስ ከተሰጡ በኋላ ፖሊስ ወዲያው ለቋቸው ብዙም ሳይቆዩ በነፍስ ግድያ እጅ ከፍንጅ የተያዙ ኢህአፓዎች ያጋጠሙበት ሁኔታዎች ነበሩ፡፡ ይህ ሁኔታ ነው ነጻ ርምጃ የሚለውን ጥያቄ እንድናነሳ ያደረገን፡፡

«ነጻ ርምጃ» በኋላ እነሰደድ እንደተጠቀሙበት የመግደል ነጻነት ጥያቄ አልነበረም፡፡ እጃችን ታስረን ማለቃችን እንዲቆም የተነሳ ጥያቄ ነበር፡፡ እኛ የሰጠነው ትርጉም ደግሞ በጊዜው ግልጽ ከመሆኑ የተነሳ በምንም ዓይነት ሌላ ትርጉም ይሰጠዋል ብለን አላሰብንም፡፡ የዚህ ጥያቄ ይዘት ምናልባት ከእንግሊዝኛው ባላነሰ አሻሚ ነው፡፡ ያለተጽዕኖ ተግባርን ማከናወን **(Independent Action)** ማለት ነበር፡፡ ከፖሊሱ ነጻ በሆነ ሁኔታ የአብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች በነፍስ ግድያ የሚጠረጠሩም ሆነ እጅ ከፍንጅ የተያዙ ሰዎችን ራሳቸው የመያዝ፣ ይዞም በፖሊስ ሳያልፉ በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት የመውሰድ መብት ይኑራቸው ማለት ብቻ ነበር፡፡ በጊዜው የሆነውም ይኸ ነው እንጂ በነጻ ርምጃ ስም በገፍና በነጻ ግድያ አልተካሄደም፡፡

ይህንን ወቅት ሌላ ዓይነተኛ የሚያደርገው ከግለሰብ ግድያዎች በተጨማሪ በገፍ በመንግሥት ባለሥልጣናት ውሳኔ ግድያዎች መካሄዳቸው ነው፡፡ ሚያዝያ 22 ቀን ማምሻውን ላይ የኢህአፓ አመራር ባዘጋጀው ሰላማዊ ሰልፍ ምክንያት ብዙ ወጣት በገፍ አልቋል፡፡ ምክንያት የምለው እውቁ ነው፡፡ ሰልፉ ላይ እንኳን ብዙ ሰው አልሞተም፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ ሰልፈኞች በወታደርና በፖሊስ እየታፈሱ ታሰሩ፡፡ ሌሊቱን በልዩ ትእዛዝ ቢያንስ ሶስት መቶ ወጣቶች እንዲረሸኑ ተደርጓል፡፡ እውነቱ እየወጣ የሄደው በተከተሉት ቀናት እንጂ ወዲያው አልነበረም፡፡ በዚህ ግድያ የቀበሌ አብዮት ጥበቃ ኮሚቴዎች የተጫወቱት ሚና አልነበረም፡፡ መኢሶንን በሚመለከት እንደዚህ ዓይነቶቹ የገፍ ግድያዎች እየተስፋፉ የመጡት ከሱማሌ ወረራ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሲሆን ከሰኔ ሐምሌ 1969 ዓ.ም በኋላ ነው፣ በተለይ በሐረር፣ በባሌና በሲዳሞ፡፡ በነሃሴ ወር ህቡእ እንድንገባ በጣም ከገፋፉን ምክንያቶች አንዱ ይህ በክፍለ ሃገራት በአባሎቻችን ላይ እየተስፋፋ የመጣው ዘመቻ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ግንባር ቀደም የሆኑ ገበሬና ወዛደር አባሎቻችን የሱማሌ ሰርጎ ገብ እየተባሉ የሚያልቁበት ወቅት ነው፡፡ ለምሳሌ ሰኔ መጨረሻ ላይ በሐረርጌ በአንድ ቀን 27 ወዛደሮች በኮሎኔል ዘለቀ ትእዛዝ ተረሽነውብናል፡፡

በኛ ታጋዮች ላይ ከሱማሌ ወረራ ሂደት ጋር ግድያው እየተስፋፋ ሄደ ስል በሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛ፣ ወረራው የፈጠረው የግርግር ሁኔታ የደርግ ተጠሪዎችን፣ በክፍለ ሃገር ያለውን ቢሮክራሲና ከፍተኛ የጦር መኮንኖችን ኃይል አጠናክረው በዚህ በተጠናከረ ኃይል እነዚህ ኃይሎች ቀደም ሲል ከመኢሶን ጋር የተያያዙትን ትግል በአመቺ ሁኔታ እንዲቀጥሉት አደረጋቸው፡፡ ሁለተኛውና ዋናው፣ ምክንያት ግን በዚህ በወረራው ጉዳይ ከሰኔ መጀመሪያ ጀምሮ በኛና «በአዲሱ የቀኞች ኅብረት» መሃከል ከፍተኛ የትንተና ልዩነቶች ነበሩ፡፡

በሐረር፣ በሲዳሞና በባሌ ክፍላተ ሀገር የሚገኙት የሕዝብ ድርጅት ኃላፊዎች የሚልኩልን መልእክቶች፣ ገና ከግንቦት መጨረሻ ጀምሮ ከታጋይ ገበሬዎች የምናገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው «ሱማሊያ ሃገሪቱን ለመውረር እየተዘጋጀች ነው፡፡በኦጋዴን አካባቢ ጦሩን በማጠናከር እንደዚሁም ደግሞ የየአካባቢውን ገበሬዎች በሚገባ በማስታጠቅ ይህንን ወረራ መቋቋም ያስፈልጋል» የሚሉ መልእክቶች ነበሩ፡፡ የደርግ ቢሮክራሲም ሆነ ሰሸየቶች በዚያን ጊዜ ይህንን የመኢሶንን ማስጠንቀቂያ እንደ ሽብር ፈጣሪ (Alarm) አሉባልታ ለመቆጣጠር የየራሳቸው ምክንያቶች ነበራቸው፡፡

ሚሊታሪ ቢሮክራሲው ሶማሊያ ዞር ዞር የትም አትደርስም፣ ግን በዚህ ወረራ ሳቢያ «አብዮት፣ አብዮት እየተባለ አገራችን ተዳከማ ተደፈረች» ብሎ ከቻለ እነ ኮሎኔል መንግሥቱንም ሆነ በአብዮት ስም እየተጠናከረ የመጣውን መኢሶንን ለመውጋት የሚያስችል ሁኔታ ይመቻልኛል ብሎ ያምናል፡፡ ሌላው የመኢሶን ጩኸት አጉል አሉባልታ ነው የሚሉበት ምክንያት ለኛ ያን ጊዜም በጣም ግልጽ ነበር፡፡ መኢሶን ያን ጊዜ የሚለው በጠረፍ አካባቢ ሠራዊቱ ይጠናከር የሚል ብቻ አልነበረም፡፡ ገበሬዎችም ይታጠቁና ወረራውን ይከላከሉ የሚል ጥያቄ ነበር፡፡ «መኢሶን በግርግር ገበሬዎቹን አስታጥቆ መንግሥት ሊገለብጥ ነው» ተባለ፡፡ እንዲያውም ዋናው የተፈራው ይኸ ነበር፡፡ ትዝ ይለኛል በዚያን ሰሞን አንድ ስብሰባ ላይ እነኮሎኔል መንግሥቱ ባሉበት «ቢሮክራሲው ስለ ሰርጎ ገቦች ነው የሚያወራው፡፡ እኛ ግን ጉርፍ ገቦች ነው የምንላቸው»ብየ የተናገርኩት፡፡ ያኔ የሱማሌዎችን በገፍ ወደ ኢትዮጵያ መግባት ለመጠቆም ነበር፡፡ በዚህ አካባቢ ነው በደርግ ቢሮክራሲ ግፊት አብዱላሂ ዩሱፍ ከሐረር ሕዝብ ድርጅት ኃላፊነት እንዲነሳ የተደረገውና አዲስ አበባ መጥቶ ሃምሌ መጨረሻ ላይ በሰደድ ኮማንዶዎች የተገደለው፡፡ የሲዳሞው ኃላፊ እሸቱ አራርሶም ይህንኑ የመኢሶንን አቋም ይዞ ነበር የሚከራከረው፡፡ እሱም እንደዚሁ አዋሳ በስድስት ጥይት ተመትቶ ቆስሎ በተአምር ነው የተረፈው፡፡

በኦጋዴንና በዚያ ጠረፍ አካባቢ ጦሩ ይጠናከር የሚለውን የመኢሶንን አቋም ሶሸየቶችም አይደግፉትም ነበር፡፡ የነሱ ስትራቴጂያዊ ዓላማ በነሱ ቁጥጥር ሥር የአፍሪካ ቀንድ ኮንፌዴሬሽን መፍጠር ነበር፡፡ እዚያድ ባሬን ለማረጋጋት በዚህ ኮንፌደሬሽን ስር ለኦጋዴን አንድ ራሱን የቻለ የራስ ገዝ አስተዳደር እንዲሰጥ ይፈልጉ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ይህንን እንድትቀበል ከደካማ ሁኔታ (defensive position) የምትደራደርበት ሁኔታ ቢፈጠር ለዚህ ዓላማ ያግዛል የሚል እምነት ነበራቸው፡፡ እቅዳቸው በእውነቱ ማከያቬሊያዊ ነበር፡፡ ይህንንም ለማሳካት ሱማሊያ በቀላሉ ኦጋዴንን የምትቆጣጠርበት ወታደራዊ ሁኔታ መፍጠር፡፡ኦጋዴን ከተያዘ በኋላ ተደራደሩ ብለው ሁለቱን መንግሥታት ሞስኮ መጋበዝና አንድ ዓይነት«አማካይ የመፍትሄ»ሃሳብ ማቅረብ፡፡ የሆነውም ልክ እንደዚሁ ነው፡፡ ይህንን ከሥራ ላይ ለማዋል ምን ሴራ ጠነሰሱ?

የኦጋዴን ግንባር ለሱማሊያ ክፍት እንዲሆን በጊዜው እዛ የነበረው «ገስጥ» የተባለው ጦር እንዲነሳ ለኮሎኔል መንግሥቱ አንድ አሸባሪ የሆነ «መረጃ» ይዘው ቀረቡ፡፡ «ኢዲዩ በሱዳንና በግብጽ ታግዞ፣ ከኤርትራ ግንባሮች ተባብሮ፣ በሰሜን ኢትዮጵያ ከፍተኛ ወረራ እያዘጋጀ ነው፡፡ ወዲያውኑ አዲስ አበባ ባይደርስም ጉንደርን ተቆጣጥሮ በዚያ ሕዝባዊ መንግሥት ብሎ ለማቋቋም እቅድ እንዳለው ደርሰንበታል፡፡ በሱማሊዎች በኩል ግን

ሙሉ በሙሉ ርግጠኛ ነን የወረራ አደጋ የለም:: ገስጥን ጦር ከኦጋዴን አንስታችሁ ሰቲት ሁመራን አስለቅቁ የሚል ሃሳብ አቀረቡ::ነገሩን ይበልጥ የሚታመን ለማድረግ ነው ግንቦት መጨረሻ ላይ (ጁን 5 ተን ይመስለኛል) ታስ የሚባለው የሶቪየት ዜና አገልግሎት ይህንኑ ዜና አሠራጭቶ ሶቨየት ህብረት ይህንን ወረራ የምትቃወምና ከኢትዮጵያ ጐን የምትቆም መሆኑን ያስታወቀው::

በዚህ ጉዳይ ላይ ከኮሎኔል መንግሥቱ ጋር ስንወያይ ትዝ ይለኛል:: ኮ/መንግሥቱ «መረጃ ከታመነ ምንጭ ደርሶናል:: ለሚኒንን ማጠናከር አለብን» አሉ:: እኛ ደግሞ «ይህ አጠራጣሪ መረጃ እውነት ቢሆን እንኳን በጉንደር ለሚሆነው ሁኔታ ኦጋዴን ክፍት መሆን የለበትም» አልን::ለማንኛውም ሶቭዬቶች ባቀረቡት ሃሳብ መሠረት ገስጥ ጦር ከኦጋዴን ተነስቶ ሰቲት ሁመራን ከኢዲዩ አስለቀቀ:: ,ዘሩ በነቀለ በሶስት ሳምንት ውስጥ የሱማሊያ ጦር ሐረርና ድሬዳዋ ዙሪያ ነበር የሚዋጋው::ሐምሌ መጨረሻ ላይ እኔ በሥራ ጉዳይ ሰበብ አገር ለቅቄ ስወጣ ለመጨረሻ ጊዜ ኮሎኔል መንግሥቱ ጋርስሰናበት ያነሱልኝ ነጥብ ይህንን የሶቨየቶችን ሴራ በሚመለከት ነበር::«በተሳሳተ መረጃ ጦር እንድናነሳ ተደርገን:: ይኸው በኦጋዴንና በሐረርጌ በተከላካይነት ደረጃ እንገኛለን::»ነበር ያሉኝ::

ሐምሌና ነሐሴ ወራት እጅግ ብዙ የመኢሶን አባላት ያለቁባቸው ወራት ናቸው:: በከተሞች በሰደድና በደርግ ኰማንዶዎች የሚካሄደው ግድያ ተጧጧፈ:: ሌላው ምናልባት ሰው ልብ ያላለው በግንባር ከፍላተ ሃገራት የተካሄደው እልቂት ነው:: ለምሳሌ መጀመሪያ ላይ ድሬዳዋና ሐረርን በቀራጥነት የተከላከሉት ሕዝባዊ ድርጅቶች፣ የወዛደርና የተበሊ አብዮት ጥበቃ ኰሚቴዎችና ከየአካባቢው በኛ ጓዶች አስተባባሪነት የተሰበሰቡት ገበሬዎች ነበሩ::ትዝ ይለኛል አንድ ተን ወደማታ ላይ ድሬደዋ ሕዝብ ድርጅት ጽ/ቤት ደውዬ የተጧጧፈ የተኩስ ድምጽ ስሰማና ስልኩን ያነሳው ልጅ«ጓድ ትንሽ ቆይተህ እንደገና ደውል:: ከሱማሌ ኰማንዶዎች ጋር እየተታኩስን ነው::» ብሎኝ ስልኩን ስዘጋ:: በዚህ ወቅት ከሱማሌ ጦር ጋር እየተዋጉ ህይወታቸው ያለፈው የመኢሶን ገበሬዎች፣ ወዛደሮች፣ የተበሊ ተመራጮችና የህዝብ ድርጅት ካድሬዎች ስፍር ቁጥር የላቸውም::ያውም ደግሞ ከጀርባችን በነ ኰሎኔል ዘለቀ በሰርጉ ገብነት እየታፈሱ መዓት ታጋዮች እያለቁ:: በዚህ የተነሳ የሱማሌ መንግሥት እንደጠላት ነበር መኢሶንን የሚቆጥረው:: በ1970 እነአበራ የማነአብ ወደ ስደት ሲወጡ በሱማሊያ ለማለፍ ቢገደዱም የመኢሶን አባልነታቸውን ሸሽገው ነበር:: ያ ቆራጥ ታጋይ እሸቱ አራርሶም ሞቃዲሾ በሱማሊዎች ታስር በኋላም የተረሸነው የመኢሶን መሪ መሆኑ ስለተደረሰበት ነበር::

እንግዲህ በዚህ በ1969 ዓ.ም እኔ ስወጣ እንዲህ ዓይነት ከየአቅጣጫው የምንዋከብበት፣ ከኛም ይልቅ ደግሞ በግንባር ከፍላተ ሃገር ታጋዮቻችን እንደቅጠል የሚረግፉበት ወቅት ነበር:: በ1970 ዓ.ም ደግሞ የባሰ መጣ:: በዚህ ወይም በዚያ ድርጅት ላይ ሳይባል በአንድ ታጋይ ትውልድ ላይ መዓት ወረደበት:: ይህን አሰቃቂ ታሪክ ገና ወደፊት በሰፊው የምንመለስበት ነው::ከፍ ብየ እንዳልኩት ለመወነጃጀል ሳይሆን እንዲህ ዓይነቱ ወቅት ተመልሶ እንዳይመጣ ምን ማድረግ እንዳለብን ለማየት ነው::ያን ሁሉ እንደጉርፍ የፈሰሰ ደም እንደተራ ሽቀጥ ሊነግዱበት የሚሹ አንዳንድ የታሪክ ድንኩች ሊኖሩ ይችላሉ:: የራሳቸው ጉዳይ ነው::

ይህንን ጥያቄ እንደዚህ በሰፊው ለመመለስ የሞከርኩት ራሴንም ሆነ ድርጅቴን ነፃ ለማውጣት አይደለም:: በሃቅ ላይ የተመሠረተ የጥሞና ውይይት ለማገዝ ነው:: መኢሶን በኢትጵያ አብዮት በተለይ ደግሞ በፊውዳሉ ሥርዓት መደምሰስ ስለተጫወተው ሚናም ይቅርታ ለመጠየቅ አይደለም:: መሬት ላራሹ ለሚለው የአንድ ትውልድ መፈክር ከገበሬው ጐን ተሰልፈን በመዋደቃችን ምን ጊዜም ይቅር የማይሉን ኃይሎች አሉ:: የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ብለን ስለታገልን ይህ አቋማችን ምን ጊዜም የማይዋጥላቸው ወገኖች ይኖራሉ:: የኢትዮጵያ አንድነት ስላልንና ከየብሄሮች የተውጣጡ ታጋዮችን በአንድነት አሰልፈን በመዋደቃችን እንደጣውንት የሚያዩን ብዙዎች ይኖራሉ:: የነዚህ ሁሉ ኃይሎች አንዱ የትግል መሣሪያ በሆነ ባልሆነ የታጋዮችን ስም ማጥፋት ነው::ያ ታላቅ ታጋይ ኃይሌ ፊዳ የእንደዚህ ዓይነቱ ዘመቻ ሰለባ እንደሆነ ነው የተገደለው:: በኔም ላይ ብዙ የሆኑ ያልሆኑ ውንጀላቸው ተሰንዝረዋል:: ሌላው ቀርቶ የአጼ ኃይለሥላሴ መንግሥት ባለሥልጣናት የነበሩት 60 ሰዎች በደርግ ሲገደሉ በነነገደ ምክር ነበር የሚል ውንጀላ ሁሉ አጋጥሞናል:: እኔ ያኔ ፈረንሳይ አገር ገና ተማሪ ነበርኩ:: ኢትዮጵያ የገባሁት አብዮቱ በጀመረ በዓመቱ ነው:: የስልሳዎቹን ባለሥልጣናት በግፍ መረሸን መኢሶን በማያሻማ ሁኔታ በጋዜጣው በሰፊው ሕዝብ ድምጽ በወቅቱ አውግዟል:: (ለመሆኑ ለመኢሶን ሽንፈት ምክንያቱ ምንድን ነው? ዶ/ር ነገደ በዚህ ጽሑፍ የመጨረሻ ክፍል ለጥያቄው ምላሽ ይሰጣሉ:: ጦቢያ መጽሔት ቅጽ 3 ቁ. 3 ላይ እናቀርባለን::)

## መኢሶን ተሸንፏል? ከኢሕአፓ በምን ይለያል?

መኢሶንን ሙሉ በሙሉ ተሸንፏል ወይ? ለማይ ወጥተን መሬት ገብተን ለሥልጣን እንብቃ የሚል ትግል አካሂደን ቢሆን ኖሮ ሙሉ በሙሉ ተሸንፈናል ማለት ይቻላል:: መሬት ላራሹ፣ ዲሞክራሲ፣ በብሔር/ብሔረሰቦች እኩልነት የተገነባች ኢትዮጵያ ብለን ነው የተነሳነው:: ለኛ የኢትዮጵያ አብዮት ቁልፍ ጥያቄ ነበር ግፈኛ ሥርዓትና የለውጥን ርምጃ አፍኖ የያዘ ስለነበረ:: ከሕዝቡ 90 በመቶ በላይ ኑሮ በመሬት ጥያቄ ላይ የተንጠለጠለ ስለነበረ:: የመሬቱ ስሪት ለብሄሮች ጭቆና የኢኮኖሚ ጉዝጓዝ ስለነበረና የዚህ ጭቆና ምልክትም ስለነበረ:: መኢሶን ከደርግ አንጻር «ሂሳዊ ድጋፍ» የሚለውን አቋም የያዘው ከመጀመሪያው አልነበረም:: እርግጥ በውጭ የነበርነው ይህ አቋም ነበረን:: ድርጅቱ ግን ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ ይህንን አቋም የያዘው ከመሬት አዋጅ በኋላ ነው:: ማለትም ከየካቲት 1967 ዓ.ም በኋላ:: የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት እንዲቋቋም የገፋውና እዚህ ጽ/ቤት ውስጥ በሰፊው የተሳተፈው በዚህ ሳቢያ በከተሞች ከደርግ ሥልጣን ለመካፈል አልነበረም:: በዚህ ተቋም አማካኝነት በመንግሥት የተደገፈና የሚረዳ ሥራ በገጠር ለመስራት ነበር::

የሆነውም ይኸው ነው:: ሕዝብ ድርጅት ሲቋቋም የኛ የዘመቻው መቀጠል ነበር:: በገጠር በ1968 እና በ1969 ዓ.ም የኛ ታጋዮች ያካሄዱት ትግልና የተዋጓቸው ኃይሎች እነዛው ዘመቻውን ሲዋጉ የነበሩ ኃይሎች ናቸው:: ለዚህ ትግል ከሕዝብ ድርጅት አባላት ከ80 ከመቶ በላይ የሚሆኑትን በገጠር ከገበሬው ጐን አሰልፈናል:: በነዚህም ኃይሎች አማካኝነት በየከፍለ ሃገሩ በሺህ የሚቆጠሩ የገበሬ መሪዎች በመኢሶን ባንዲራ ሥር አሰልፈን ታግለናል:: የኛ አባላትና ደጋፊዎች ከገበሬዎች ጐን ተሰለፈው ያደረጉት መስዋዕትነት ፍሬቢስ አልነበረም:: የፊውዳሊዝም ሥርዓት በማያዳግም ሁኔታ ከሃገራችን በየመንደሩ በገበሬዎች ትግል ሲደመሰስ የመኢሶን ታጋዮች ከገበሬው ጐን ቆመው እየተሰው ነበር:: በነዚህ ሰማዕታት ለኢትዮጵያ ገበሬዎች ደህንነት በደማቸው በከፈሉት ዓዶች አስተዋጽኦ የሚሰማንን ኩራት ማንም ምን ጊዜም ሊነጥቀን አይችልም:: ያኔ ከአገራችን የፊውዳሊዝም ቀንበር ሲደመሰስስ እኛም ነበርንበት እንላለን:: ምናልባት እንደ ፖለቲካ ድርጅት ለፊውዳሊዝም መደምሰስ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ በአካል ተገኝቶ ከሁሉም

ድርጅቶች ይበልጥ አስተዋጽኦ ያደረገ ድርጅት ቢኖር መኢሶን ነው ለማለት እደፍራለሁ።

በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች አምነውበት የተሰለፉበት አብዮት ሙሉ በሙሉ ግቡን አልመታም እንጂ ሙሉ በሙሉ ውድቅ ሆኗል አልልም። ከዚህም አልፌ እሄዳለሁ። የፊውዳሊዝም መደምሰስ ብቻ አይደለም። በዚህ ምክንያት ሌሎቹም ያልተሟሉት የየካቲት አብዮት ጥያቄዎች እንዲፈቱ መንገድ ከፍቷል። ለታህሣሡ ጉባኤ በቀረበው መንደርደሪያ ሰነድ ላይ ይህ ጉዳይ በግልጽ ተቀምጧል። አብዮታዊ ትግላችን ሙሉ በሙሉ ፍሬ ቢስ አልነበረም። የተድሞው የመሬት ስሪት መወገድ የብሄሮችን ጥያቄ በውይይትና በዲሞክራሲ ለመፍታት አመቺ ሁኔታ ፈጥሯል ብለን አስቀምጠነዋል።

በዚህ አመቺ ሁኔታ ተጠቅሞ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ደህንነት በጋራና በውይይት ይህንን ጥያቄ መፍታት የዛሬ ፖለቲካ ታጋዮች አንዱ ትልቅ አደራ ነው። ከሁሉም ወገን መልካም ፈቃድ ካለ በግማሽ ተሰናከሉ ቢቀርም ያ አብዮት በዚህ በብሄሮች ጥያቄ አንጻር አመቻችቶልን የሄደው የእኩልነት፣ የወንድማማችነት ጉዝጓዝ አለ። ሌላም በዛሬው ግርግርና የብሄር/ ብሄረሰብ ድርጅቶች ማየል የተነሳ ብዙ ሰው ልብ የማይለው ቁም ነገርና እኛ መኢሶናች የቀሰምነው ትምህርት አለ። መሬት ላራሹ ብለን ያኔ ስንዋደቅ ለመላው ኢትዮጵያ ሕዝቦች ደህንነት በአንድ ላይ ታግለን ነው። የደርግ መንግሥት የመኢሶን ቀንደኛ መሪዎች ብሎ በአንድ ቀን አምስት ታጋዮቻችንን ማለትም ኃይሌ ፊዳን፣ ዶክተር ንግሥት አዳነን፣ ቆንጂት ከበደን፣ደስታ ታደሰንና ኃይሉ ገርባባን ወስዶ ሲረሽን እነዚህ መሪዎቻችን ከኦሮሞ፣ ከትግራይ፣ ከአማራና ከጉራጌ ብሄረሰብ የተውጣጡ ዜጎች ነበሩ። ለዚህ ወይም ለዚያ ብሄር ሳንል በአንድ መንፈስ፣ በአንድ ዓላማ በወንድማማችነት መንፈስ ታግለናል። ፊውዳሊዝምን የመደምሰስ ያህል ቁም ነገር የተሠራው በዚህ ወይም በዚያ ብሄር ስም በተደራጁ ኃይሎች ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሕዝቦች የጋራ ጥቅም፣ ለእኩልነታቸውና ለጋራ ብልጽግናቸው አብረው በተሰውት ጓዶቻችን ትግልም ነው። ለኔ አብዮቱ ትቶልኝ ያለፈው አንድ ትምህርት ይኸ ነው። ለዚህ ነው ለምሳሌ ምን ቢመጣ አማራ እንደመሆኔ መጠን የአማራ ድርጅት አባል ለመሆን እንኳን በውኔ በህልሜም የማይመጣብኝም። ይህ ማለት ግን በብሄር መደራጀትን መቃወም አይደለም። ይሁንና በብሔር/ብሔረሰብ መደራጀት አሉታዊ ልምድ አለው። እሱን አሽቀንጥረን እንጣለው፣ እንመርምረው፣ ትምህርት እንቅሰምበት ለማለት ያህል ነው።

የተሰናከለው አብዮት በዚህ በብሄሮች ጥያቄ ብቻ ሳይሆን በዚያም ባልተሳካለት የዲሞክራሲ ጥቂም ላይ የማይናቅ ትምህርት ትቶ ነው ያለፈው። ዛሬ ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ያስፈልጋል ብቻ ሳይሆን ይቻላል የምንለው በዚህም ጥያቄ ላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይ ደግሞ ገበሬው«አይቶ የተነሳው» እጁን ካስገባ በኋላ የተነጠቀው የራሱን ጉዳይ በራሱ የማስተዳደር ልምድ በአበዮቱ መጀመሪያ አመታት አግኝቶ ስለነበረ ነው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዛሬ ዲሞክራሲ ብንላቸው ተጨባጭ ነገር ነው ለነሱ። ለአጭር ጊዜም ቢሆን የዲሞክራሲን ጸጋ ቀምሰነዋልና። ይህንን ከተነጠቁ በኋላ ደግሞ በከፈሉት የገፍ ግርያ፣ የገፍ ረሃብ፣ የገፍ ስደት መከራ ጸረ ዲሞክራሲ ማለት ምን እንደሆነ በተጨባጭ ያዩትና አሁንም የሚያዩት ሃቅ ነው።

ሙሉ በሙሉ አልተሸነፍንም ስል ራሴን ለማጽናናት ሳይሆን በዚህ በአብዮቱ ትግልና ባስከተለው መስዋዕትነት ሳቢያ የመሬቱን ስሪት ደምስሰናል፣ በዚህም የተነሳ ለቀሩት ቁልፍ ጥያቄዎች ማለትም ለብሄሮች ጥያቄና ለዲሞክራሲ ጥያቄ መፈታት የተመቻቸ ሁኔታ ተፈጥሯል ለማለት ነው።

ግን ደግሞ ሽንፈት የለም ማለት አይደለም። ትዉልዳችን ከሰላሳ ዓመት ጀምሮ ያነሳውና የተዋደቀለት የእኩልነት፣ የነጻነት፣ የብልጽግናና የፍትህ ዓላማ አጃችን መግባት ከጀመረ በኋላ አምልጦልናል። እንዲያውም ይህንን ሽንፈት የገላ የሚያደርገውና ይበልጥ እንዲሰማን የሚያደርገው ከማይናቁ ታሪካዊ ድሎች በኋላ የደረሰ ከስተት መሆኑ ነው። የኛ ትውልድ መሬት ላራሹ ብሎ ሲነሳ ይህንን ከሥራ ላይ ለማዋል እንደቀደሙት አብዮቶች፣ በባሌም በቦሌም እየገባን፣ የሃያም የሰላሳም ዓመታት ረዥምም ትግልን አድርገን የምናመጣው ነገር አርገን ነበር የምንጠብቀው። ሃያና ሰላሳ ዓመታት እኛና የኢትዮጵያ ጤሰኞች በሕገወጥነት የምንታገልበት። ፊውዳሉቹ ደግሞ በህግና በመንግሥት በኩል ሆነው የተከላከሉበት ረዥም ትግል ነበር የጠበቅነው። ይህ አብዮታዊ ትውልድ ከተጸነሰበት ከተማሪ ንቅናቄ ባወነ ገና ሳይላቀቅ አብዮቱ ደረሰበት።

በመሬት ላራሹ ጥያቄ ምላሽ ህጋዊ ፊውዳሉቹ ህገወጥ የሚሆኑበት ሁኔታ ተፈጠረ። ብዙ ድሎች ተገኙ። ከነዚህ አብዛኞቹ መልሰው ተነጠቁ። እነዚህ ድሎች እንዲገኙ ብዙ ደምና እንባ ፈሰሰ። እንዳይነጠቁም እንዲሁ ብዙ ደምና እንባ ፈሰሰ። ስለዚህ ነው ሽንፈት አለ ብቻ ሳይሆን በጣም የሚያንገበግበን ሽንፈት ነው የምለው።

ይህ ሽንፈት እንዲደርስ ያደረጉት ብዙ ስህተቶች ናቸው። አንዳንዶቹን ልናመልጣቸው እንችል እንደነበረ እጠራጠራለሁ። ያኔ በነበረው አነጋገር አብዮት የመጣላቸውና አብዮት የመጣባቸው እንል ነበር፣ እኛን ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር ከመጀመሪያው ከፍል ያለአንዳች ማመንታት እያካተትን። አንዳንዴ ሳስበው ግን ይኸ አብዮት እዛ ታጋይ ትውልድ ላይ «አልደረሰበትም ወይ?» እያልኩ እጠይቃለሁ። ለሃገር ፍቅርና ለሕዝብ ለመሰዋት ካለው የጋለ ስሜት በስተቀር የትኛው ድርጅታዊ አቅሙ፣ የትኛው የአብዮታዊ ትግል ልምዱ፣ የትኛው ዘመር ብሎ የሚያየውና የሚመክበት የማህበራዊ ለውጥ የትግል ትርስ ነበር እንዲህ ዓይነቱን መሬት አንቀጥቅጥ የለውጥ ሃይት ለመምራት ብቁ የሚያደርገት? እያልኩ ራሴን እጠይቃለሁ። ለዚህ ነው ይህ አብዮት ለኢትዮጵያ ሕዝብ መጣለት እንጂ እኛስ ገና በቅጡ ሳንደራጅ ነው የደረሰብን ለማለት የምደፍረው። ሁሉም ሰው የሚለው ነገር አለ። አብዮቱ በግብታዊነት ነው የፈነዳው። አመራሩም እስከተወሰነ ደረጃም ቢሆን ግብታዊ ነበር ማለት ይቻላል። ትዝ ይለኛል አንድ ጊዜ ሕዝብ ድርጅት ፃ/ቤት «ለመሆኑ ይህንን አብዮት የ ሚመራው ማነው»? የሚል ከባድ የንድፈ ሃሳብ (ቲዎሪ) ጥያቄ ተነስቶ አንድ ጧት ሙሉ ክርክር ሲካድ። ወዛደሩ? ንዑስ ከበርቴው? የንዑስ ከበርቴው ግራ ክንፍ? . . . . ጥያቄው በቅጡ ሳይመለስ ለምሳ ልንበተን ስንል ጧቱን ሙሉ ዝም ብየ ስታዘብ ከውይይቱ አለመሳተፌን የተመለከተ ዶ/ር ሰናይ «ነገደ፣ ምነው ዝም አልክ? ያንተስ አስተያየት ምንድነው፣ ይህንን አብዮት ማነው የሚመራው?» ብሉ ቢጠይቀኝ «ዝም ብላችሁ ነው እኮ የምትለፉት። ይህ አብዮት መሪ አለው ማለት አልችልም። አድሃሪዎች ከኋላችን እያባረሩን እኮ ነው ከፊት ከፊት የምንሮጠው።»ብየ ስመልስ። እርግጥ የተጋነነ አባባል ነው። ግን ከነበረው ተጨባጭ ሁኔታ ብዙም እሩቅ አልነበረም። እንግዲህ በዚህ ባልተዘጋጀንበት ሁኔታ፣ በዚያ ነገሮች በአስደናቂ ፍጥነት በሚቀያየሩበት ማዕበል ውስጥ እየተዋከብን እያለን ብዙ ከባድ ስህተቶች ማድረጋችን ልናመልጥ የማንችለው የታሪክ እጣ ነበር ማለት እደፍራለሁ።

ይህንን የምለው ከኃላፊነት ለማምለጥ አይደለም። መኢሶን ያን ጊዜ ለደረሰው ሽንፈት የተጠያቂነት ድርሻ አለው። በተከፈለው መስዋዕትነትና በተገኘው ድል ብቻ አይኩራራም። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎች አምነውት ከሥሩ ተሰልፈው፣ በመቶ ሺ የሚቆጠሩ ወዛደሮች «ድርጅታችን፣ መሪያችን»

ብለውት፣ አርማውን አንስተው፣ በሺ የሚቆጠሩ ወጣት አብዮታውያን አመራሩን ተቀብለው፣ ይህንን ሁሉ ኃይል አሰልፎ እያለ መርቶ ለሙሉ ድል አለመብቃቱ ለዚህ የህዝብ ድጋፍና አመኔታ ተመጣጣኝ የሆነ የፖለቲካ ብስለትና ድርጅታዊ ብቃት እንዳልነበረው ለኔም ለመኢሶን አባላትም ግልጽ ነገር ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ በኛና ከኛ ውጭ ሆነው መኢሶንን በሚተቹ ሰዎች መሃከል መሠረታዊ ልዩነት አለ።

አንዳንድ ድርጅቶችም ጋር ሆነ ግለሰቦች ጋር ስንወያይ ሂስ አርጉ ሲሉን እነሱ ከኛ የሚጠብቁት በአብዮቱ ዘመን የተከተልነውን የፖለቲካ መስመር ስህተት ነበር እንድንልላቸው ነው። ለ20 ወራት ያህል ከደርግ ጋር አብረን መስራታችንን፣ ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት የሚለውን ጥያቄ መቃወማችንን፣ ዘመቻው እንዲቀጥል እንጂ እንዳይቋረጥ መታገላችንን፣ ከኢትዮጵያ ገበሬዎች ጉን ለመሰለፍና ለመዋደቅ በር የከፈተልንን የሕዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤት ማቋቋማችንን፣ ከደርግ ጋር አብረን በመሥራታችን ብቻ ሳይሆን በኋላ ደግሞ ነሐሴ 1969 ላይ ማቋረጣችንን ... እነዚህና ሌሉች ዋና ዋና የሆኑት መኢሶን የተከተላቸው የፖለቲካ አቋሞች ምን ጊዜም ስህተት ናቸው ወይም ነበሩ አንልም።

እንዲያውም እኛ የምንለው ፖለቲካችን ስህተት ነበር ሳይሆን ይህንን ሥራ ላይ ለማዋል ብቃት ያለው ድርጅታዊ አሠራርና አቅጣጫ አልነበርንም ነው። ከዚህ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ይህንን የፖለቲካ መስመር ሥራ ላይ ለማዋል ያኒ በቂ የፖለቲካ ታክቲክ ብስለት አልነበረንም እንላለን። ለደረሰው ሽንፈት የመኢሶን የተጠያቂነት ድርሻ የሚፈልቀው ከነዚህ ከተያያዙ ስህተቶች ነው።

በድርጅታዊ አሠራርና አቅጣጫ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ስህተቶችና ዝርክርክነቶች ነበሩብን። አንዳንዱ ሳስበው አደረጃጀታችን መጽሐፉ እንደሚያዘው አልነበረም ወይ እላለሁ። «በወዛደሩ መሪነት በአርሶ አደሩ ተባባሪነት . . .» ተባለ። እዚህ ላይ እጅግ ከማተኩራችን የተነሳ የአደረጃጀት አቅጣጫችን ከሁለት አንጻር የተዛባ ነበር። አንደኛው ጂኦግራፊን ይመለከታል። የኢትዮጵያን ፊውዳሊዝም በአገር አቀፍ ደረጃ ለመዋጋት ታጋዮችን በአገር አቀፍ ደረጃ በየአውራጃው፣ በየወረዳው፣ በየመንደሩ መሠማራት አለባቸው ብለን ሃገሪቱን «ለማልበስ» ኃይላችንን በያለበት በታተንን። ለተከታዩና ተድሞውንም እንደማይቀር ላወቅነው ከደርግ ጋር ለሚካሄደው ፍልሚያ አንዳንድ አካባቢዎች ላይ ማተኮር አለብን ብለን የተገነዘብነውና በዚህ አቅጣጫ ቦታና ክፍለ ሃገር እየመረጥን ልዩ ትኩረት መስጠት የጀመርነው ዘግይተን ነበር።

ሁለተኛው መዛባት ከህብረተሰብ ክፍሎች አንጻር ባለን አመለካከት ነበር። ወዛደሩና በተለይም ደግሞ ገበሬው ላይ ማተኩራችን ሳይከፋ ለሌሎች ክፍሎች እምብዛም ደንታ አልነበረንም። የከተማውን ንዑስ ከበርቴ፣ ነጋዴውን፣ የመንግሥት ሠራተኛውን፣ ብሄራዊ ከበርቴውን፣ ወታደሩን . . . ይህን ሁሉ ክፍል ለማደራጀት በቂ ጥረት አላደረግንም። በእምነትና በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ይህንን ሁሉ ኃይል ማሰባሰብ ያስፈልጋል እያልን ግን መለፈፋችን አልቀረም። በተለይ በ1967 እና 1968 ዓ.ም ይወጡ የነበሩትን የሰፊው ሕዝብ ድምጽ ቁጥሮች ማየት ነው። ግን ይህንን በተግባር ማዋል ትተን አንዳንዴ የምናካሂዳቸው ቅስቀሳዎች «ግራ ተደም» ነበሩ። ይህ ደግሞ እነዚህ ክፍሎች መኢሶንን በጥርጣሬ ዓይን ብቻ ሳይሆን በጥላቻም ዓይን እንዲመለከቱት አረጋቸው። ለአብዮቱ ሊሰለፉ የሚችሉትን ኃይሎች በሙሉ ማሰለፉ ቀርቶ አታታቸው። ይህ ደግሞ ለደረሰው ሽንፈት የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። የፖለቲካ ብስለት ማነስ የምለው ይህንን ነው። መኢሶን ግንባር ቀደም ድርጅት ነኝ ካለ አይቀር እነዚህንም ኃይሎች አረጋግቶ፣ ጥቅማቸውን አረጋግጦ መያዝ ነበረበት።

ይህ መዛባትና በከተሞች ያሉትን ኃይሎች ችላ የማለት አዝማሚያ ደግሞ ዝም ብሎ ከሰማይ የወረደ ነገር አልነበረም። መኢሶን ስለ ኢትዮጵያ አብዮት ምንነትና በዚህ አብዮት መፈታት ስለነበረበት መሠረታ ቅራኔ ከነበረው ትንተና የፈለቀ ይመስለኛል። ደጋግመን እንለው የነበረና ኃይሌ ፊዳ በትክክል በጽሁፍ ያስቀመጡው አቋም ነበረን። የኢትዮጵያ አብዮት ዋናና ቁልፍ ጥያቄ የመሬት ጥያቄ ነው። ዋናና ቁልፍ ቅራኔ በጢሰኛና ባለርስት መሃከል ያለው ቅራኔ ነው። በዚህም የተነሳ ዋናው የአብዮቱ ኃይል ገበሬው፣ ዋና የአብዮታዊው ትግል መፋለሚያ መድረክ ገጠሩ ነው የሚል አቋም ነበረን። ከዚህ አንጻር ሲታይ ኃይሌ በትክክል እንዳስቀመጠው በከተሞች የነበረው ቅራኔ በወዝአደሩና በከበርቴው መሃከል የነበረው ቅራኔ ነው። በዚህም የተነሳ ዋናው የአብዮቱ ኃይል ገበሬው፣ ዋናው የአብዮታዊው ትግል መፋለሚያ መድረክ ገጠሩ ነው የሚል አቋም ነበረን። ከዚህ አንጻር ሲታይ ኃይሌ በትክክል እንዳስቀመጠው በከተሞች የነበረው ቅራኔ ነው። በወዝአደሩና በከበርቴው መሃከል የነበረው ቅራኔ በሁለተኛ ደረጃ የሚታይ ቅራኔ ነበር እንላለን። ለዚህ ነው ይህንን ዋና ጥያቄ ለመፍታትና ጸረ ፊውዳሉን ትግል ለማራመድ እየወላወለም ቢሆን የመሬት አዋጅን ካወጀውና በዚህ ምክንያት ከባለመሬቶች ጋር ቅራኔ ውስጥ ከወደቀው ከደርግ ጋር ተባብሮ መስራት አስፈላጊ መሆኑን አምነን የገባንበት ነው። የኢህአፓ አስተሳሰብ የኛ ተቃራኒ ነበር። እኛ ገጠሩን የአብዮታዊው ትግል እምብርት አርገን በመውሰዳችን ለምሳሌ ዘመቻው እንዲቀጥል እንታገል ነበር። ኢህአፓ ደግሞ ደጋግሞ እንደጻፈው የአብዮታዊው ትግል «እምብርት» ከተማ ነው ብሎ የሚከራከር ኃይል ነበር። ዘማቾችም ገጠሩን ለቀው ወደ ከተማ እንዲመለሱና ትግሉን እንዲያፋፍሙ ደጋግሞ ጥሪ ያደረገው ከዚህ አቋሙ ተነስቶ ነበር። የሆነ ሆና እኛ ከተሞችንና የከተማ ኃይሎችን ችላ እንድንልና በዚህም የፖለቲካ ስህተት እንድናደርግ የገፋፋን ትንተና ይህ ገጠርን እንደ አብዮቱ እምብርት አድርጉ የመውሰዱ አቋም ሲሆን በገጠርና በከተሞች ላይ ሚዛናዊ የሆነ ትኩረት እንዳናደርግ የገፋን ይመስለኛል።

ይህ የአደረጃጀት ስልት ጉድለትና በከተሞችና በገጠር ሚዛናዊ ትኩረት ያለመስጠት ችግራችን ብቻውን ሽንፈት አላመጣም። ሌሎች ስህተቶች ባይጨመሩባቸው ኖሮና ገበሬውንና ወዛደሩን እንዳደራጀን ሁሉ አብዮቱ ችግር ሲገጥመው ብቁ የሆነ የፖለቲካና ወታደራዊ አመራር መስጠት ብንችል ኖሮ የደርሰውን ጉዳት መቀነስ ይቻል ነበር። ግን ደግሞ እዚህ ላይ ዘርዝሬ የማልዘልቃቸው የአደረጃጀት ስህተቶች ፈጽመናል።

ሌላው ጉድለት የፖለቲካ ታክቲክ ብስለት ማጣት ነበር። ደጋግመው ብዙ ጓዶች የሚሉት ነው። እንዲያው በደፈናው የአብዮት «ቦይስካውቶች» ነበርን ማለት ይቻላል። ትግላችን በመላ ሃገሪቱ ላይ ታች እያልን ሕዝቡን ለማስተማር፣ ለማደራጀት፣ ለማስታጠቅ፡ ታግሎና አታግሎ ለሥልጣን ማብቃት ነበር። ይህ መቸም ጥሩ አባባል ነው። ግን በኋላ ሳየው ከአንድ የተወሰነ የመንቃት፣ የመደራጀትና የሕዝብ መታጠቅ ደረጃ ከተደረሰ በኋላ በሕዝብ ስም ሥልጣን ይዘን አብዮቱን ከጥፋት የምናድንበት ደረጃ በፖለቲካ የዋህነት አላመለጠንም ወይ? ህቡእ ልንገባ ሰሞን አንዳንድ ከኛ ቅርብ የነበሩ መኮንኖች «ነገሩ ሁሉ እየተበላሸ ነው። እነዚህ ሰዎች መገልበጥ አለባቸው። ኩዴታ ማድረግ ያስፈልጋል። ይቻላል።» ብለው ለመኢሶን አመራር

እቅድ አቅርበው ነበር፡፡ «በሕዝብ ትግል እንጂ በኩዴታ አናምናንም፡፡» የሚል መልስ ነው የተሰጣቸው፡፡ ያኔ አዲስ አበባ ዙሪያ የነበሩ የታጠቁ ገበሬ ማህበራት በኛ ሥር ነበሩ፡፡ የሸዋ ክፍለ ሃገር አስተዳዳሪ መኩንን ጆቴ ነበር፡፡ በየክፍለሃገሩ ገና በደርግ ቁጥጥር ሥር ያልወደቁ በሺህ የሚቆጠሩ የገበሬ ሚሊሽያዎች በኛ ሥር ነበሩ፡፡ ትዝ ይለኛል ከፋ ክፍለ ሃገር ብቻ 20 ሺ አባላት ያለው ሚሊሽያ ተደራጅቶ ዩኒፎርም ሲያሰፋ የመኢሶን አርማ ተጨምሮበትና በ፡ሊያ ሰልፍ አሳይቶ በኛና በነፍቅረሥላሴ መሃል ከፍተኛ ግጭት ሲፈጠር፣ ከሃገር ልወጣ ጥቂት ቀናት እንደቀረኝ፡፡ በርግጥም በዚያን ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ ርምጃ ለመሳካት እድል ነበረው፡፡

እንዲህ ዓይነቶቹ የፖለቲካ ታክቲክ ስህተቶች በጣም ብዙ ናቸው፡፡ እነዚህንም እዚህ ላይ መዘርዘሩ ለጊዜው አስፈላጊ አይመስለኝም፡፡ ወደፊት የመኢሶን ታሪክ ይፋ ሲወጣ ሕዝቡ ይገነዘባቸዋል፡፡ እኛ በበኩላችን ግን በየአጋጣሚው በቃል ውይይትም፣ በክርክርም፣ በውስጥ ጽሁፎችም፣ አውጥተን አውርደን ተንትነናቸዋል፡፡ ዛሬ በምንም ዓይነት የማንሠራቸው ስሁተቶች መዝግበናል፡፡ ከዚህ ሁሉ ትምህርት ቀስመናል፡፡ የፖለቲካ የዋሆች ነበርንና አሁን ደግሞ የአራዳ ሙሌዎች እንሁን የሚል ትምህርት አይደለም የምንለው ፡፡እነዛ እምነውን በኛ ሥር የተሰለፉት በሚሊዮን የሚቆጠሩት ዜጐች ከኛ ጋር የተሰለፉት መኢ.ሶን ጥቅማቸውን የሚያንጸባርቅ፣ ህልማቸውን እውን ሊያደርግ የሚችል፣ የፖለቲካ አቋም ይዞ በመንቀሳቀሱና ለህዝብና ለሃገር ያለውን ፍቅር ከጐናቸው ሆና በመሰዋት ስላረጋገጠላቸው ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን እኛ መኢሶናች ለሥልጣን ተስገብግበን ይህንን የህዝብ አመኔታ የሚበርዝ አቋም አይኖረንም፡፡ የቀሰምነው ትምህርት ቢኖር ለዚህ የህዝብና የሃገር ፍቅራችን ተመጣጣኝ የሚሆን ድርጅታዊ አሠራር፣ ይህንን ህዝባዊ አቋምና ፖለቲካ ከሥራ ላይ ለማዋል ከሚፈልጉ ሁሉ ጋር ተባብረን ለሃገራችን አንድ ቁም ነገር የሚያስገኝ ሥራ ለመስራት የሚያስችለን የፖለቲካ ታክቲክ መቀየስ እንዳለብን ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ባለን አቅም በሥራ ለማዋል ትግሉን እንቀጥላለን፡፡